

የአልጋ ኪራይ-
ከኬሻ በጠረባ
እስከ G+8

ገጽ 16



አህጉራቱን የማስተሳሰር
ተስፋ የተጣለበት
የአፍሪካ መሰረተ ልማት
ፕሮግራም

ገጽ 14





# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 168 የካቲት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ባለፉት ስድስት ወራት ከ400 ሺህ በላይ የግብርና ማሽነሪዎች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተዋል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- የግብርና ሚኒስቴር ባለፉት ስድስት ወራት 400 ሺህ 962 የተለያዩ የግብርና መካናይዜሽን ማሽነሪዎችን ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ወደ ሀገር ማስገባቱ ተገለጸ። ሚኒስቴሩ ሰባ ሺህ 718 መለዋወጫዎችም ወደ ሀገር ገብተው ስራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ ማድረጉም ተገልጿል።

በግብርና ሚኒስቴር የግብርና መካናይዜሽን ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ በረከት ፎርሲዶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት

ባለፉት ስድስት ወራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# በቦረና ዞን

## በተከሰተው ድርቅ ተጎጂ ለሆኑ ዜጎች የተሟላ ድጋፍ ለማድረግ በቅንጅት እየተሰራ ነው

- እስካሁን ከ204 ሺህ በላይ ኩንታል እህል ተሰራጭቷል

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- በቦረና ዞን በተከሰተው ድርቅ ተጎጂ ለሆኑ ዜጎች በሚፈለገው ደረጃ ድጋፍ ማሰራጨት የሚያስችል የቅንጅት ሥራ እየተሰራ መሆኑን የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ። እስካሁን ከ204ሺህ በላይ ኩንታል እህል ለተጎጂ ዜጎች መሰራጨቱም ተጠቁሟል።

በቦረና ዞን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በቢሾፍቱ ከተማ በ108 ሚሊዮን ዶላር ወጪ የኢንዱስትሪ ፓርክ ሊገነባ ነው

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡-ኢስት አፍሪካን ሆልዲንግ ማህበር በ108 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በቢሾፍቱ ከተማ የኢንዱስትሪ ፓርክ ለመገንባት ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በትናንትናው እለት ስምምነት ተፈራረመ።

በስምምነቱ ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ዳንኤል ተሬሳ፤ ኢትዮጵያ ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ዘርፈ ብዙ ፖለቲካና የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን እያደረገች እንደምትገኝ ጠቁመው፤ ማሻሻያዎቹ አዳዲስ እና ያሉትንም ኢንቨስትመንቶች አቅም ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ ብለዋል።

በቢሾፍቱ ከተማ በ108 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ፎቶ፡- ሔዱ አብርሃ

# በኦሮሚያ ከሚያስፈልጉት 25 ሚሊዮን መጽሐፍት የታተመው ሰባት ሚሊዮን ብቻ ነው

- የ2ኛ፣4ኛ እና 6ኛ ክፍል መጽሐፍት ህትመት ለቀጣዩ ዓመት ተሸጋግሯል

ገጽ 4






የአውሮፓ ህብረት ፓርላማ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ትብብር እንደሚያጠናክር አስታወቀ

ገጽ 3



አቶ ሀጂ ኢብሳ

## የኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ስርዓት ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ የመንግስትን በጀት መቆጠብ ያስችላል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ስርዓት በዓመት በትንሹ ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ የመንግስትን በጀት መቆጠብ እንደሚያስችል የግዥና ንብረት ባለሥልጣን አስታወቀ። በተለምዷዊ ግዥ የአንድ ሺ ብር እቃ ለመግዛት እስከ ሁለት ሺህ ብር ነዳጅ እንደሚባክንም ተጠቁሟል።

የግዥና ንብረት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀጂ ኢብሳ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በግዥ ስርዓቱ ላይ ያለውን ብልሹ አሰራር በማረም የጊዜና የገንዘብ ብክነትን ለማስቀረት ካለፈው ሶስት ዓመት ጀምሮ ስርዓቱን የማዘመን ስራ ሲሰራ ቆይቷል። በዚህም የመንግስት የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓትን (EGP) ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል። ይህ ግዥ ስርዓትም በዓመት በትንሹ ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ የመንግስትን በጀት መቆጠብ ያስችላል።

ዕቃ አቅራቢዎች የጨረታ ሰነድ ለመግዛት ከየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ገንዘባቸውን እንዳያበክኑ የሚያደርግ አሰራር ለመዘርጋት መሰራቱን የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የመንግስት የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ስርዓት ዕቃ የአቅራቢዎችና ገዥዎችን ወጪ የሚቆጥብ ዘመናዊ አሰራር መሆኑን ገልጸዋል።

ዛሬ በአዲስ አበባ ከተማ አንድ ሊትር ነዳጅ 67 ብር በገባበት ወቅት በውስን ጨረታ ግዥ ለመፈጸም በእያንዳንዱ ሱቅ በር ላይ ኮድ-4 መኪኖች ቁመው እንደሚታዩ የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለምሳሌ አንድ የመንግስት ተቋም የቢሮ ዕቃዎች ለመግዛት ሶስትና አምስት ሱቅ ሲዞር ሲደራደር፣ ጉቦ ሲበላና ሌሎች ተዛማጅ ነገሮች ሲደረጉ ከፍተኛ ወጪ የሚወጣ መሆኑን ጠቅሰዋል። ለአብነትም የአንድ ሺህ ብር እቃ ለመግዛት የሁለት ሺ ብር ነዳጅ የሚወጣበት ሁኔታ እንደሚኖር አመልክተዋል።

በአሁኑ ጊዜ እየተተገበረ ያለው የመንግስት የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ስርዓት ሱቃችን በስልካችን ነው በሚል መርህ በቀላሉ በድረ ገጽ በሚለቀቀው መስፈርት መሰረት በስልክ በመሙላት መጫረትና መግዛት የሚያስችል ነው። በዚህም የሚባክን ጊዜ፣ ነዳጅና ገንዘብ አይኖርም ብለዋል።

እንደ አቶ ሀጂ ገለጻ፤ በመንግስት የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ስርዓት አሸናፊው የሚታወቀው ጨረታ ወጥቶ ለመረከብ ሲመጣ ብቻ ነው። ከዚህ ውጪ ተጫራቹ ሀበሻ ይሁን ፈረንጅ አይታወቅም። የግዥ ስርዓቱን በአንዳንድ ተቋማት ተግባራዊ ማድረግ የማይፈልጉት የጥቅም ትስስርን ስለሚያስቀር ነው። የፌዴራል ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ተግባራዊ ቢያደርጉ የመንግስት በጀት መቆጠብ ያስችላል።

ተወደደም ተጠላም ከኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓት የሚያመልጥ ምንም ተቋም የለም ያሉት አቶ ሀጂ፤ አምስት የሚሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እስካሁን በግዥ ስርዓቱ ውስጥ አልገቡም። እስካሁን ወደ ኤሌክትሮኒክስ የግዥ ስርዓት ለማስገባት የተገባው ጥረት ስኬታማ ሲሆን እስካሁን ባለው አሰራር የነበረውን የግዥ ስርዓት ሌብነትን 20 ከመቶ ጽዱ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።

የኤሌክትሮኒክስ የመንግስት የግዥ ስርዓቱ ቢያንስ ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ የመንግስት በጀት መቆጠብ እንደሚያስችል የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ገንዘቡ ለኢትዮጵያ ልማት ተጨማሪ አቅም ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪም ጊዜን በመቆጠብ ተወዳዳሪን ያሰፋል፣ ታማኝነቱን ከፍ በማድረግ ንክኪና ብልሹ አሰራርን እንደሚያስቀር አብራርተዋል።

በግዥ ስርዓቱ ላይ የሚስተዋለውን ብልሹ አሰራር ለማስቀረት በጸረ ሙስና ኮሚሽን በኩል የኤሌክትሮኒክስ ግዥ የሚሰጠውን ጥቅም አስመልክቶ 148 በላይ የፌዴራል ተቋማት የተውጣጡ የግዥና የፋይናንስ ባለሙያዎች ስልጠና መሰጠቱንም ጠቅሰዋል።

በቀጣይም በዚህ የግዥ ስርዓት ውስጥ በማይገባ ተቋም ገንዘብ ሚኒስቴር በጀት የሚለቅበት ምክንያት እንደማይኖርም ገልጸዋል።

# በክልሉ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃንን በዘመናዊ መስኖ ልማት ለማሰማራት እየተሰራ ነው

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

ሀዋሳ፡- በሲዳማ ክልላዊ መንግስት አንድ ሺ ሁለት መቶ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን በዘመናዊ የመስኖ ልማት የሚሰማሩበት ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ። ለፕሮጀክቱ ከ935 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት እንደተያዘለትም ተጠቁሟል። የዘመናዊ እርሻ መሳሪያዎችን በመጠቀም የእርሻ ስራውን በማሳለጥ ለሌሎች ፕሮጀክቶች ሞዴል ተደርጎ የሚሰራበት መሆኑም ተመልክቷል።

ፕሮጀክቱ በሀዋሳ ከተማ ይፋ በተደረገበት ወቅት እንደተጠቆመው፣ ፕሮጀክቱ ወጣቶች ከስራ ጠባቂነት ወጥተው በራሳቸው ስራ ፈጠራ መሆን የሚችሉበት ሲሆን የጊዳቦ ግድብን በመጠቀም በአምስት ሺ ሄክታር መሬት ላይ የሚካሄድ ነው።

በፕሮጀክቱ ማስጀመሪያ መድረክ ላይ የተገኙት የክልሉ ምክትል ርእሰ መስተዳድርና የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በየነ ባራሳ፤ ፕሮጀክቱ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃንን ተጠቃሚ የሚያደርግ፣ ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድግ፣ ከአግሮ ፕሮሰሲንግ ፓርኮች ጋርም እንዲተሳሰር ተደርጎ የሚተገበር መሆኑን አስታውቀዋል።

የለውጡ መንግስት ታላላቅ እቅዶችን በመተግበር ላይ ርብርብ እያደረገ መሆኑን ምክትል ርእሰ መስተዳድሩ ጠቅሰው፣ ክልሉ ከተመሰረተ ወዲህ ባሉት ሁለት አመታት የተለያዩ የልማት ግቦችን አንግበን ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረግን እንገኛለን ብለዋል። ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው መካከል ወጣቱን ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችሉት ፕሮጀክት እንደሚገኝበት አመልክተው፣ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው የሚመለሱ ወጣቶች መቀጠር ብቻ ሳይሆን ራሳቸው ሰርተው ሌላውን መጥቀም፣ ሀብት ማፍራትና መቅጠር የሚችሉበት እድል እንዲኖራቸው የማድረጉ ስራ ታቅዶ ሲከናወን መቆየቱን ተናግረዋል። ባለፉት ሁለት ዓመታት ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ወጣቶችም በራሳቸው ሰርተው ሀብት ማፍራት የቻሉበት ሁኔታ መታየቱን ጠቅሰዋል።

ከዚህ አኳያ ሁሉንም ወጣቶች በመድረስ በኩል ገና ይቀረናል፤ ይህንን የሚያግዙ እድሎችን በሙሉ መጠቀም አስፈላጊ ነው ያሉት ምክትል ርእሰ መስተዳድሩ፣ የፌዴራል መንግስት ከመስኖ ልማት ጋር በማቀናጀት ወጣቱን ተጠቃሚ ለማድረግ ያመጣውን ይህን ፕሮጀክት ወደ ስራ ለማስገባት ዝግጅት ሲደረግ መቆየቱን ተናግረዋል።

"ወጣቱ አቅም እና እውቀት አለው፤ የሚያግዘው ካገኘ በራሱ ላብና እውቀት ሀብት ማፍራትና ራሱን መቻል ብቻ ሳይሆን ሀገሩንም ማልማት የሚችልበት እድል አለው" ያሉት ኃላፊው፤ ይህንንም የሚደግፍ ፕሮግራም በዚህ መልኩ ተቀርጾ ሲመጣና ወደ ተግባር ሲገባ በጣም ትልቅ ፋይዳ እንዳለውም አስታውቀዋል። ይህ ፕሮጀክት ግቡን እንዲመታ ሁሉም አካላት የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸውም አስገንዝበዋል።



የጊዳቦ ግድብ

ፕሮጀክቱ በቦታው ተደራሽ እንዲሆን የክልሉ መንግስት በትኩረት እንደሚሰራ አቶ በየነ አረጋግጠው፤ ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት የጊዳቦ ግድብ የመስኖ አውታር ግንባታ እና ያልተጠናቀቀ የመንገድ መሰረተ ልማት በፍጥነት እንዲጠናቀቅ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ጠይቀናል ብለዋል።

ምክትል ርእሰ መስተዳድሩ እንዳሉት፤ ፕሮጀክቱ ወጣቶችን በማደራጀት የሚተገበር እንደመሆኑ መጠን ከዚህ አንጻር የተደራጀው የክልሉ ቢሮ ይህን ለማድረግ ከራሱ የሚጠበቅበትን ፈጣን እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ ነው። በዚህ በኩል የሚያስቸግር ነገር ይገጥማል ተብሎ አይገመትም። ለፕሮጀክቱ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ የሚመለከተው አካል ከወዲሁ ችግሮችን ፈትቶ ስራው በተሳካ መልኩ እንዲጀመር ማድረግ ይጠበቅበታል።

የክልሉ ውሃ፣ ማእድንና ኢነርጂ ቢሮ ኃላፊ አቶ ውብሸት ጲጋዬ ፕሮጀክቱ በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ ባንክ የሚደገፍ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከ935 ሚሊዮን ብር በሚበልጥ በጀት እንደሚካሄድ አስታውቀዋል። ፕሮጀክቱ የታለመትን ግብ እንዲመታ በክልሉ ምክትል ርእሰ መስተዳድር ሰብሳቢነት ከተለያዩ ተቋማት በተውጣጣ ስትሪንግ ኮሚቴ እንደሚመራም አመልክተዋል።

ክልሉ ካለው ቆዳ ስፋት አንጻር ሲታይ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ በሚያደርጉ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለበት መግባባት ላይ ተደርሶ እየተሰራ መሆኑን የቢሮ ኃላፊው ጠቅሰው፤ የዚህ ፕሮግራም ዋናው አላማ ክልሉ ባለው አካባቢ ላይ ምን አይነት ስራ ቢሰራ የበለጠ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል የሚለውንም የያዘ መሆኑን ጠቁመዋል። ፕሮጀክቱ ዘመናዊ የመስኖ ስራ የሚሰራበት እንደመሆኑ ከዚህ አኳያ ፋይዳው ከፍተኛ ነው ብለዋል።

በቆላማ አካባቢና መስኖ ልማት ሚኒስቴር የብሄራዊ ፒኤስአይፒ ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ ጌታሰው መኮንን ፕሮጀክቱ በሀገሪቱ ሶስት ክልሎች ላይ እንደሚሰራ ገልጸው፤ እነሱም በአማራ ክልል ጣና በለስ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች፣ በኦሮሚያ ክልልና ሲዳማ ክልል ደግሞ 12 ሺ ሄክታር መሬት በመስኖ ማልማት የሚያስችል መሆኑን አስታውቋል፤፤ በአጠቃላይ ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁ ሶስት ሺ ወጣት ተማሪዎችን የሚያሳትፍ መሆኑ ተጠቁሟል። ለሀገሪቱ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ግብአት የሚያቀርብም እንዲሆን ተደርጎ የሚካሄድ መሆኑን አመልክቷል።

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በርካታ ግዙፍ ፕሮጀክቶች እንዳሉት ጠቅሶ፤ እነዚህን ፕሮጀክቶች ለየት የሚያደርገው ሞዴል ፕሮጀክት ይሆናል ተብሎ ይታሰባል ብለዋል። ወጣቶች ከግብርና ጋር በተገናኘ ማሽኖችን መሰረት ባደረገ መልኩ የዘመናዊ እርሻ መሳሪያዎችን በመጠቀም የእርሻ ስራውን በማሳለጥ ለሌሎች ፕሮጀክቶች ሞዴል ተደርጎ የሚሰራበት መሆኑም ጠቁሟል።

በግድቡ አካባቢ ሊተገበር ይፋ የተደረገው ፕሮጀክት ከዩኒቨርሲቲ ምሩቃን በተጨማሪ በቀጥታና በተዘዋዋሪ በርካታ በግድቡ አካባቢ የሚኖሩ ወጣቶችንና ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ እንደሚያደርግም ታምኖበታል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የጊዳቦ ግድብ በኦሮሚያ ክልል በኩል ስምንት ሺ ሄክታር በሲዳማ ክልል በኩል ደግሞ አምስት ሺ ሄክታር መሬት በመስኖ ማልማት የሚያስችል ነው።

# ጣውላን በሀገር ውስጥ በማምረት ከ2 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማዳን ተችሏል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት ከውጭ ይገባ የነበረን የጣውላ ምርት በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት ከ2ነጥብ6 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማዳን መቻሉን የደብረብርሃን ውድ ፕሮሰሲንግ ድርጅት አስታወቀ።

በአማራ ደን ኢንተርፕራይዝ 51 በመቶ እንዲሁም በቻይና የግል ባለሀብቶች 49 በመቶ ድርሻ ያለው የደብረብርሃን ውድ ፕሮሰሲንግ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ አቶ ባዩ ደጀኔ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ወራት አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስድስት ሜትር ኪዩብ ዜኒርና ከሰማንያ ስድስት ሺህ በላይ ጣውላ በማምረት ከአንድ መቶ አርባ ሚሊዮን ብር በላይ ሽያጭ አከናውኗል።

አቶ ባዩ እንዳስገነዘቡት፤ የደብረብርሃን ውድ ፕሮሰሲንግ በ2007 ዓ.ም የዜኒርና ፕላይት ምርት ለማምረት የተቋቋመ ነው። ዜኒር ማለት ያላለቀለት ምርት ሲሆን የፕላይት ምርት ለማምረት የሚያገለግል ግብዓት ነው። የፕላይት ምርት በዋናነት ለጣውላ ስራ፣ ለግንባታ ስራዎች፣ ለመኪና ስፖንዳ፣ ለኮንቴነርና ለልዩ ልዩ የግንባታ ስራዎች የሚያገለግል ንብብር ጣውላ ነው።

እንደ ሥራ አስኪያጁ ማብራሪያ፤ በ2015 በጀት አመት የስድስት ወር አፈጻጸም አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስድስት ሜትር ኪዩብ ዜኒር ተመርቷል። 86 ሺህ 189 ጣውላ በማምረት 140 ሚሊዮን 624 ሺህ 275 ብር ሽያጭ ተከናውኗል።

ባለፉት ስድስት ወራት የተገኘው ውጤት ብዙ ፈታኝ ሂደቶች የነበሩበት መሆኑን የጠቀሱት አቶ ባዩ፤ በዋናነት የውጭ ምንዛሬ እጥረት አንዱ ነበር ብለዋል። በጥሬ እቃነት የምንጠቀመው የባህርዛፍ ግንዲላና ዩሪያ ፎርማል ኬሚካል ሲሆን፤ ኬሚካሉ በሀገር ውስጥ ስለማይመረት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከውጭ የሚገባ ነው። በአመት ውስጥ ስድስት መቶ ቶን ኬሚካል ስለሚያስፈልግ ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ ግዥ እንፈጽማለን ብለዋል።

የሚገዛው በውጭ ምንዛሬ በመሆኑ በስራችን ላይ ችግር እየፈጠረ ነው ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ እንዲሁም ለማሽኖች የሚሆን መለዋወጫ እቃዎችንና ያረጁ ማሽኖችን በአዲስ ለመተካት ከውጭ የሚገቡ በመሆኑና የዶላር እጥረት በመኖሩ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረብን ነው ብለዋል።

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ የተመረቱ ምርቶችን ለመሸጥ የገበያ ችግር የለም። በዋናነት ምርቶቻችንን የሚቀበሉን የግንባታ ድርጅቶች፣ ልዩ ልዩ የጣውላ ስራ የሚያካሄዱ አካላት፣ ሪል ስቴቶች፣የመኖሪያ ቤትና የተለያዩ ድርጅት የሚገነቡ ግለሰቦች ናቸው። በተለይ ጥራት ያለው ምርት በማምረት በገበያ ውስጥ ገብተናል ብለዋል።

እንደ አቶ ባዩ ገለጻ፤ ከ90 በመቶ በላይ የግንባታ እቃዎችን የምናመርት በመሆኑ በስፋት በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ አካላት ደንበኞቻችን ናቸው። በቀጣይ ምርትን በስፋትና በጥራት በማምረት ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ በመገኘት የውጭ ምንዛሬን ማስቀረት ትልቁ አላማቸው አድርገው እየተንቀሳቀሱ ነው።

ምርቱን በሀገር ውስጥ ማምረት ባንችል በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከውጭ እናስገባ ነበር ያሉት አቶ ባዩ፤ ምርቱን በማምረታችን በአመት ከ3 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬን እያስቀረን ነው ብለዋል።

ከዚህም ባሻገር ድርጅቱ በቋሚነት፣ በኮንትራትና በኢንተርፕራዝ ተደራጅተው ለሚሰሩ ከ360 በላይ ሰራተኞች የስራ እድል መፍጠሩንም ስራ አስኪያጁ ጠቁመዋል።

# የአውሮፓ ኅብረት ፓርላማ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ትብብር እንደሚያጠናክር አስታወቀ

ጌትነት ተስፋማርያም


ካትለን ቫን ብሬምት


ዶክተር አብዱሰመድ ሁሴን

አዲስ አበባ፡- በጤና ጉዳዮች ዙሪያ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን የትብብርና ድጋፍ ስራዎች የማጠናከር ፍላጎት እንዳለው የአውሮፓ ኅብረት ፓርላማ አስታወቀ።

የኅብረቱ ፓርላማ አባላት ከኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጤና፣ የማህበራዊ ልማት፣ የባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ጋር ተወያይተዋል።

በውይይቱ ወቅት የአውሮፓ ኅብረት ፓርላማ የኮቪድ-19 ልዩ ኮሚቴ ሰብሳቢ ካትለን ቫን ብሬምት እንደገለጹት፤ በጤናው ዘርፍ ከኢትዮጵያ ፓርላማና ከተለያዩ ተቋማት ጋር በተጠናከረ ሁኔታ በጋራ ለመስራት ፍላጎት አለ።

በተለይ ወረርሽኞችን በመከላከልና በተለያዩ የጤና ጉዳዮች ላይ በትብብር መንፈስ መስራት የምንችልበት ዕድል አለ ያሉት የኮሚቴው ሰብሳቢ ካትለን ቫን፤ ከሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ጋር በተያያዘ የተከሰቱ ስነልቦናዊና ማህበራዊ የጤና ጉዳዮች ላይ በጋራ እንሰራለን ሲሉ ተናግረዋል።

ግጭት፣ ድርቅና፣ የአየር ንብረት ለውጥ የጤና ስርዓቶችን እየጎዱ ይገኛል። በመሆኑም ችግሮችን በቅንጅት መፍታት በሚቻልባቸው መንገዶች ላይ የልምድ ልውውጥ በማድረግ በጋራ ትብብር መንፈስ ከኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር ጠንካራ ግንኙነት መመስረት እንፈልጋለን ብለዋል።

ኢትዮጵያ የኮቪድ ወረርሽን በመከላከል ረገድ ያሳየችው ውጤታማነት የሚደነቅ ነው፤ በተጨማሪም ከአየር ንብረት ለውጥ መከላከል ጋር በተያያዘ ለሰው ልጅ ጤና የሚጠቅሙ ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑ የሚበረታታ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተወካይ ዶክተር አብዱሰመድ ሁሴን በበኩላቸው፤ የጤና ዘርፉን ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት በትብብር መስራት የሚያስችል ውይይት ከአውሮፓ ኅብረት አባላት ጋር መደረጉን ገልጸዋል።

የአውሮፓ ኅብረት ፓርላማ ልዑክ በግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን የጤና ተቋማት መልሰው ወደስራ እንዲገቡ በሚያስችሉ ስራዎች ፣ ለሴቶች ህጻናት የስነልቦና ድጋፍ በማቅረብ እንዲሁም በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ የሚያደርጉትን ድጋፍ እንዲያጠናክሩ ጥያቄ መቅረቡን ተናግረዋል።

ከኢፌዴሪ የፓርላማ አባላት የኅብረቱ ፓርላማ አባላት ጋር ያደረጉት ውይይትና የልምድ ልውውጥ ጠቃሚ ግብዓት የተገኘበት መሆኑን ዶክተር አብዱሰመድ አስረድተዋል።

ስለኢትዮጵያ አጠቃላይ የባህል፣ የታሪክና የፖለቲካ ሁኔታ ለአውሮፓ ኅብረት ፓርላማ የኮቪድ-19 ልዩ ኮሚቴ አመራርና አባላት ገለጻ ተደርጎላቸዋል።

# ምርታማነትን ለማሳደግ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከኢንዱስትሪዎች ጋር በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል

ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምርታማነትን ለማሳደግ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከኢንዱስትሪ ዘርፉ ጋር በቅንጅት መስራት እንዳለባቸው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል ትናንት ከዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጋር ውይይት ባደረጉት ወቅት እንደገለጹት፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከኢንዱስትሪ ዘርፉ ጋር በጋራ በመስራት የሀገር ውስጥ ምርታማነትን በዘላቂነት ለማሳደግ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

የኢትዮጵያ ታምርት ሀገራዊ ንቅናቄ የተቋማትን ቅንጅት በማሳደግ ረገድ መልካም ተሞክሮ የታየበት ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ ኢንዱስትሪዎች ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመናበብ ለአገር የሚበጁ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ በስፋት መሳተፍ አለባቸው ብለዋል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመራቂ ተማሪዎች በቆይታቸው ያገኙትን እውቀት፣ ክህሎትና ብቃትን በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ገብተው እንዲጠቀሙበትና በሀገር ልማት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲያሳድጉ ቅንጅታዊ ስራው አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል።

የሀገርን የኢኮኖሚ እድገት ከሚወስኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ የተማረ የሰው ኃይል ማፍራት ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ ለሀገር ልማት መልካም አመለካከት ያላቸው በእውቀትና ክህሎት የበቁ ዜጎችን መፍጠር ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የተጀመረውን የኢንዱስትሪ ልማት በውጤታማነት ለመምራት በትግበራዊ ልምድ የዳበረ የሰው ኃይል ማፍራት ላይ ትኩረት መደረግ አለበት። ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና አምራች ኢንዱስትሪዎችም በትብብር መንፈስ የሚያከናውኗቸውን ስራዎች ማሳደግ አለባቸው ብለዋል።

ሚኒስትሩ እንዳስታወቁት፤ ከዚህ ቀደም የኢንዱስትሪ ዘርፍ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቅንጅት ባለመስራታቸው በሚፈለገው ልክ ውጤት አልመጣም። እንደሀገር የተያዘውን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የኢንዱስትሪ ዘርፍ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተናበበ ስራ ሊያከናውኑ ይገባል።

የኢትዮጵያ ታምርት ሀገራዊ ንቅናቄ ዋና አስተባባሪና የሚኒስትሩ አማካሪ አቶ አስፋው አበበ በበኩላቸው፤ በአምራች ዘርፉ ያሉ ተግዳሮቶችን አመላክተው እንደአገር ያሉትን የኢንዱስትሪ ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ትውልዱ ብቁ ስራ እንዲያከናውን ማገዝ ይገባል ብለዋል።

መላው ዜጋ የሀገሩን ምርት በመጠቀም ኢኮኖሚያችንን ለማጠናከር መስራት አለበት ያሉት አማካሪው፤ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ማህበረሰቡ የአምራች ዘርፉ ላይ የተጋረጡ የአመለካከትና የእውቀት ችግሮችን ለመቅረፍ የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል።

እንደሀገር ብቃትና ክህሎት ያለውን የሰው ሃይል በብዛት ወደ ኢንዱስትሪ ዘርፉ ለማምጣት እየተሰራ ነው ያሉት አማካሪው፤ ትግበራው ሙሉ በሙሉ ውጤታማ ሲሆን በዘርፉ ያሉ ችግሮችን መቅረፍ ያስችላል ሲሉ ጠቁመዋል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ ዘርፉ ጋር ያላቸው ትስስር ሚዛኑን መሳት የለበትም ያሉት አማካሪው፤ የኢትዮጵያ ታምርት ሀገራዊ ንቅናቄ እንደሀገር ቅንጅታዊ ስራ ለማከናወን የሚያስችለውን ሚዛናዊ ግንኙነት ለማስጠበቅ የሚረዳ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አማካሪው ገለጻ፤ የሀገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ስራ ያስፈልጋል፤ በዚህ ረገድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ያለውን አቅም ወደኢንዱስትሪ ዘርፉ በማምጣት በአግባቡ መጠቀም ይገባል።



# በድሬዳዋ ለዓባይ ግድብ ባለፉት ስድስት ወራት 3ነጥብ 6 ሚሊዮን ብር ተሰበሰበ

## - በአስተዳደሩ እስካሁን የተሰበሰበው ድጋፍ 92 ሚሊዮን ብር ደርሷል

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ስድስት ወራት ለዓባይ ግድብ ግንባታ 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ብር ገቢ ከቦንድ ሽያጭ ማሰባሰቡን የግድቡ የድሬዳዋ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት አስታወቀ። እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ 25 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማሰባሰብ ጥረት እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል።

የዓባይ ግድብ የድሬዳዋ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሀብታሙ አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤በከተማ አስተዳደሩ በተከናወኑ የገቢ ማሰባሰቢያ ስራዎች በስድስት ወራት ውስጥ ከቦንድ ሽያጭ 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ብር ተሰብስቧል። በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ገቢውን 25 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማድረስ ታቅዷል።

በድሬዳዋ ከተማ ከ2004 ጀምሮ ቦንድ በመግዛት እና በአጭር ጽሁፍ መልዕክት የገቢ ማሰባሰቢያ ስርዓቶች ህብረተሰቡ እየተሳተፈ ይገኛል። የከተማ አስተዳደሩ ህዝብ ለግድቡ ግንባታ በአጠቃላይ ያሰባሰበው ገንዘብ ከ92 ሚሊዮን ብር በላይ ሆኗል ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ፤ የግድቡ ግንባታ እየተከናወነ ባለበት ወቅት ህብረተሰቡ ለግድቡ የሚያደርገውን ድጋፍ እንዲያጠናክር የሚረዱ የቅስቀሳ መርሃ ግብሮች በመከናወን ላይ ናቸው።

በየካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ግቢ የዓባይ ግድብ ገቢ ማሰባሰቢያ የንቅናቄና ቅስቀሳ መርሃግብር ይካሄዳል።በዚህም ግድቡ አሁን ያለበትን ደረጃ ለማህበረሰቡ በማሳወቅ በቦንድ ሽያጭ ማከናወን፣የህዳሴውን አርማ ለሽያጭ የማቅረብና በአጭር የጽሁፍ መልዕክት የገቢ ማሰባሰቢያ መርሃግብር ይከናወናል ብለዋል።

የከተማዋ ነዋሪዎች የህዳሴው ግድብ ተጠናቆ መመልከት ትልቅ ህልማቸው መሆኑን በየጊዜው ይገልጻሉ ያሉት ኃላፊው፤ የካቲት 30 ለሚካሄደው የግድቡ ድጋፍ ማሰባሰቢያ መርሃግብር ላይ በርካቶች እንደሚሳተፉ ከወዲሁ እያሳወቁ ይገኛል ሲሉ ጠቁመዋል።

በከተማ አስተዳደሩ የሚከናወነውን የህዝባዊ ንቅናቄ መድረክ በተከታታይ ለአንድ ወር ለማስቀጠል መታቀዱንም አስታውቀዋል።

በተጨማሪ የዓባይ ግድብ የተጀመረበት የመጋቢት ወር ላይ የከተማውንና የገጠሩን ማህበረሰብ ያሳተፉ የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች በሰፊው ይከናወናሉ ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ በገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶቹ ላይ ህብረተሰቡ በቦንድ ሽያጭ፣ በአጭር ጽሁፍ መልዕክትና በሌሎች የልገሳ መርሃግብሮች ተሳትፎ እንደሚያደርግ ይጠበቃል ብለዋል።

እንደ ዓባይ ግድብ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት መረጃ ከሆነ በሀገር ውስጥና ከሃገር ውጪ ከሚገኙ ኢትዮጵያዊያን እስከ ህዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ከ17 ቢሊዮን 595 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰብ ተችሏል።

ዜና

# በኦሮሚያ ከሚያስፈልጉት 25 ሚሊዮን መጽሐፍት የታተመው ሰባት ሚሊዮን ብቻ ነው

## - የ2ኛ፣4ኛ እና 6ኛ ክፍል መጽሐፍት ህትመት ለቀጣዩ ዓመት ተሸጋግሯል

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በአዲሱ የትምህርት ካሪኩለም ከሚያስፈልገው 25 ሚሊዮን መጽሐፍት ውስጥ እስካሁን የታተመው ሰባት ሚሊዮኑ ብቻ መሆኑን የክልሉ ትምህርት ቢሮ ገለጸ። የ2ኛ፣ 4ኛና 6ኛ ክፍል መጽሐፍት ህትመት ለቀጣዩ አመት መሸጋገሩም ተጠቁሟል።

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በክልሉ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ 25 ሚሊዮን የአዲሱ ካሪኩለም መጽሐፍት አሳትሞ ለማሰራጨት ታቅዶ፤ እስካሁን ሰባት ሚሊዮኑ ብቻ ታትሟል።

የክልሉ ትምህርት ቢሮ የሚያስፈልገውን መጽሐፍት ለማሳተም የ6 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በጀት እንደሚጠይቅ የተናገሩት ዶክተር ቶላ፣ ትምህርት ቢሮው የተጠየቀው በጀትም በወቅቱ ተገኝቶ እንደነበር ተናግረዋል።

ይሁንና መጽሐፍቱን በአገር ውስጥ ለማሳተም በክልሉ የሚገኙ ማተሚያ ቤቶች እንደአማራጭ ተወስደው ነበር ያሉት ኃላፊው፤ ማተሚያ ቤቶቹ የአቅም፣ የጥራትና የፍጥነት ሁኔታቸው ህትመቱን ለማከናወን የሚያስችል ባለመሆኑ በህንድ አገር እንዲታተም መደረጉን ጠቁመዋል።


በውጪ ሀገር መታተሙ ጥራቱና ፍጥነቱን ለመጨመር ያስችላል ያሉት ኃላፊው፤ የህትመት ዋጋ ከሀገር ውስጥ ይልቅ የውጭ አገሩ ይቀንሳል። ይሁንና የማጓጓዣ ወጪው በእራሱ ከፍተኛ በመሆኑ በወቅቱ ማስገባት አልተቻለም ሲሉ ተናግረዋል።


ዶክተር ቶላ እንዳሉት፤ ከመንግስት በተገኘው በጀት ማሳተም የተቻለው ሰባት ሚሊዮኑን መጽሐፍት ብቻ ነው፤ ከዚህ ውስጥ ከአምስት ሚሊዮን በላይ መፅሐፍት ተሰራጭተዋል። አፈጻጸሙም ከታቀደው የ25 ሚሊዮን መጽሐፍት ህትመትና ስርጭት አንጻር ሲታይ ደካማ ነው ብለዋል።

ኃላፊው እንደገለጹት፤ በመጽሐፍት እጥረት የተነሳ የ2ኛ፣ 4ኛ፣6ኛ ክፍልን የመጽሐፍት ህትመትና ስርጭት ለሚቀጥለው ዓመት ተሸጋግሯል። የ1ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ክፍል መፅሐፍትንም በተዘጋጀው እቅድ አማካኝነት ስራ ላይ ለማዋል ታስቦ ማድረስ አልተቻለም።

በክልሉ ከ550ሺህ በላይ የስምንተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ተፈታኝ ተማሪዎች መኖራቸውን ኃላፊው አስረድተው፤ በዚህ የተነሳ የ8ኛ ክፍል የአዲሱ ካሪኩለም መፅሐፍን ቅድሚያ ሰጥቶ ለማሰራጨት ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል።

የመምህራን መመሪያ መጽሐፍትን በተመለከተ ለ1ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛና 8ኛን ክፍሎች መምህራን በሁሉም ትምህርት አይነቶች የማስተማሪያ መመሪያ መጽሐፍቱን ማዳረስ ቢቻልም፣ ለሌሎቹ ግን ህትመቱ ባለመድረሱ ማሰራጨት እንዳልተቻለ አስታውቀዋል።




# ባለፉት ስድስት ወራት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንደገለጹት፤ ሚኒስቴሩ ለ 90 አስመጪዎች ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ማረጋገጫ በመስጠት አራት መቶ ሺህ 962 ለተለያዩ የግብርና መካናይዜሽን የሚውሉ ትራክተሮችን ፣ ኮምባይነር እና ሁለገብ መውቂያ ፣ ቢለር ፣ ኢንኩቤተር ፣ የእንስሳት መኖ ማቀናበሪያ ፣ የቡና መፈልፈያ ፣ የወተት ማለቢያ ፣ የሰብል ጸረ ተባይ መርጫ እና ሌሎች ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ ማሽነሪዎች ወደ ሀገር እንዲገቡ ድጋፍ አድርጓል።

አንደ አቶ በረከት ገለጻ፤ ሰባ ሺህ 718 የተለያዩ መለዋወጫዎች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ስራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን፤ በተጨማሪም ለ10 የተለያዩ የጸረ ሰብል ኬሚካል መርጫ እና መለዋወጫ አስመጪዎች የቴክኒክ ምርመራ ድጋፍ በመስጠት በአጠቃላይ 348 ሺህ 503 የኬሚካል መለዋወጫዎች እና የተለያዩ የሰብል ጸረ ተባይ ኬሚካል መርጫ መሳሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ ተገልጿል።

መለዋወጫዎቹ ከገቡም በኋላ የግብርና መካናይዜሽን ማሽነሪዎችን የአጠቃቀም ስልጠና የሚሰጡ ባለሙያዎችን አዘጋጅተን ጥሩ ስራ ሰርተናል ያሉት ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ በተጨማሪም በፌዴራል ኤ.ቲ.ቬ.ት የተዘጋጀውን የሙያ ደረጃና ስርአተ ትምህርት ለማሻሻል ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የግብርና ሜካይዜሽን ቴክኖሎጂ ኦፕሬሽን እና ጥገና ባለሙያዎችን ለማሰልጠን ከደረጃ አንድ እስከ አራት የሙያ ደረጃ እንዲሻሻል እና ካሪኩለም በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ ተደርጓል ብለዋል።

አሁን በዋናነት እየሰራን ያለነው የግብርና መካናይዜሽን ግብአቶች እንደ ሌላው የግብርና ግብአት በአንዴ የሚያልቁ ስላልሆኑ ተገዝተው ከገቡ በኋላ በትንሹ እስከ አስር አመት ማገልገል እንዲችሉ ለአርሶ አደሩ ስልጠና መስጠት ላይ እንገኛለን ብለዋል።

# በቢሾፍቱ ከተማ በ108 ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንደ ምክትል ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ኢንቨስትመንትን የበለጠ ለማጠናከር ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች እና የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በልዩ ሁኔታ የሚደግፉ ፖሊሲዎች እና ማሻሻያዎች ጸድቀው ወደ ስራ በመግባት አመርቂ ውጤቶች እየተመዘገበ ነው። ለአብነትም ባለፉት ስድስት ወራት ከሁለት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መሳብ ተችሏል ብለዋል ።

የኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ ማህበር ሊቀመንበር ዶክተር ብዙአየሁ ታደለ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የፓርኩ ግንባታ ሲጠናቀቅ ስፋቱ ወደ 100 ሄክታር የሚያድግ ሲሆን ለ15 ሺህ የሰው ኃይል የሥራ ዕድል ከመፍጠሩም ባሻገር ለቴክኖሎጂ ሽግግር ዕድል የሚፈጥር ነው።

የማስፋፊያ ፕሮጀክቱ በ108 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚለማ ሲሆን ንድፉ የኢንዱስትሪያል ፓርክ አጠቃቀም ሥርዓትን የተከተለ፣ መሰረተ ልማት የተሟላለት፣ 40 ሜጋ ዋት የኃይል አቅርቦት የሚኖረው እና ታዳሽ ኃይል ላይ በትኩረት የሚሰራ እንዲሁም ኤክስፖርትን የሚያሳድግ ነው ሲሉ አብራርተዋል። በተጨማሪም የአካባቢውን አርሶ አደሮች በምርት አቅርቦት የሚያስተሳስር እና ለሀገር ውስጥ ግብዓት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ነው ሲሉ አክለዋል።

እንደ ዶክተር ብዙአየሁ ገለጻ፤ ፓርኩ ሙሉ ለሙሉ ወደስራ ሲገባ ምርቶችን ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ከማቅረብ ባሻገር ኤክስፖርት በማድረግ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኝ ይሆናል።

ፓርኩ ከአዲስ አበባ በ40 ኪሎ ሜትር ላይ መገኘቱ እና ከኢትዮ ጇቡቲ ምድር ባቡር ጣቢያ በቅርብ ርቀት እንደሚገኝ ገልጸው፤ ከአዲስ አበባ አዳማ ፈጣን መንገድ በሦስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገነባ መሆኑ እና ከሞጆ ደረቅ ወደብ በ15 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ መሆኑ ፓርኩን ልዩ እንደሚያደርገው ገልጸዋል።

ኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ ማህበር በውስጡ የተለያዩ ኢንቨስትመንቶችን የያዘ የሀገር በቀል ኩባንያ ሲሆን፤ ከዚህም መካከል የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት፣ ሲሚንቶ ምርት፣ አላቂ እቃዎች፣ የሪልስቴት ልማት፣ ማዕድን ልማት እና ሎጀስቲክ የንግድ ዘርፍ የያዘ እና ከስድስት ሺህ በላይ ቋሚ እና ጊዜያዊ ሰራተኞች የስራ ዕድል መፍጠር የቻለ ድርጅት ነው።

# በቦረና ዞን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ ዘውዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት በቦረና ዞን በድርቅ አደጋ ጉዳት ከደረሰባቸው ዜጎች ውስጥ በ13 ወረዳዎች ውስጥ ለሚገኙ ወደ 604 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የእለት ድጋፍ ቀርቦላቸዋል። ካለፉት ሁለት ወራት በ15 ቀናት ውስጥም ለእነዚሁ ወገኖች 204 ሺህ 765 ኩንታል ምግብ ወደ አካባቢው ተልኮ ተሰራጭቷል። ከጉዳቱ አንጻርና የተጎጂዎች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ በመንግስትና በአጋር አካላት ቀጣይ ድጋፍ ማድረግ የሚያስችል የቅንጅት ሥራ እየተሰራ ነው።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ኮሚሽኑ በተለይ ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ህጻናት፣ ነፍሰ ጡሮች፣ አጥቢ እናቶችና አቅመ ደካሞች የሚሆን 10 ኩንታል አልሚ ምግብ ወደ አካባቢው ተልኳል። ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢው ህብረተሰብ፣ ባለሀብቱ፣ ድጋፍ ሰጪዎችና መንግስትም በዚሁ መልኩ ለወገኖች ሊደርስ የሚችለውን ድጋፍ እያቀረቡ ይገኛሉ።

ክልሉ 800ሺህ ለሚጠጉ ዜጎች የዕለት ድጋፍ መጠየቁን ገልጸው፤ በዚሁ ቁጥር ልክ ድጋፉ እንዲሰጥ ከአጋር አካላት ጋር አብሮ የሚሰራ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

ድርቅን በሚመለከት በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ክስተቱ እንዳለ የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ክስተቱ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ጉዳት እያስከተለ ይገኛል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የተፈጥሮ አደጋዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜም በሦስት አካላት ድጋፍ እንደሚደረግ ጠቁመው፤ እነዚህም መንግስት፣ የዓለም ምግብ ፕሮግራም፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል። እነዚህም በየአካባቢው ጉዳት ባጋጠመባቸው ስፍራዎች የየድርሻቸውን በመያዝ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን ከክልል ጋር በመሆን ለሥርጭት እንዲበቃ ያደርጋሉ ነው ያሉት።

እንዲህ አይነት ችግሮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ እንደ ኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የማስተባበር ሥራን በመስራት ከሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ከክልሎች ጋር አብሮ የሚሰራባቸው ስልቶች እንዳሉ ዳይሬክተሩ አክለው ገልጸዋል።

ከእነዚህ ሥራዎች ውስጥም በክልል ደረጃ የአስቸኳይ ጊዜ ማስተባበሪያ ማዕከል ማቋቋም አንዱ እንደሆነና በዞን ደረጃ ብዙ ቁጥር ያላቸው ወገኖች ጉዳት ሲደርስባቸው የአስቸኳይ ጊዜ ኮማንድ ፖስት እንደሚቋቋም ጠቅሰዋል።

ይህም በክልል የሚመራና ኮሚሽኑ የሚደግፈው የጤና፣ የግብርና፣ የውሃ፣ የትምህርትና ሌሎች ጉዳዮች እንደመኖራቸው ሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶችን አስተባብሮ ማስኬድ የሚያስችል ድጋፍ በቅንጅት እየተሰራ እንዳለ አመላክተዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ባሉ ሁኔታዎች ምክንያት በአጋር አካላት የሚደርሰው ድጋፍ ላይ ተጽእኖ ሊያሳርፉ ይችላሉ ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የተበታተነውን ሁኔታ መሰብሰብ የሚያስችል ከአገር ቤት እስከ ውጭ ያሉ አካላት የሚሳተፉበት ተግባራትም እንዳሉ ጠቁመዋል።

አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው ተክለማርያምን ጨምሮ በየቢሯቸው በመገኘት አጋር አካላትን፣ ኤምባሲዎችን፣ የመንግስታቱ ኀብረት ተወካዮችን እያነጋገሩ እንዳለ ገልጸዋል። በዚህ መልክ ድጋፉ እንዲጠናከር ይደረጋል ሲሉም አስታውቀዋል።

ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ በአገሪቷ ድርቅና ሌሎች ተዛማች ችግሮች አሉ። በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለመቋቋም ከአገር ውስጥ አቅም ባሻገር የአጋር አካላት አስተዋጽኦ ወሳኝ ነው። ለዚህም አጋር አካላት የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጥረት እየተደረገ ነው። በአሁኑ ወቅትም ድጋፉ እየመጣ ነው። ለዚህም በሚፈለገው ደረጃ ማሰራጨት የሚያስችል የቅንጅት ሥራ እየተሰራ ነው።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሄት




“የአንድ በዓይን የማይታይ ትንሽ የሕይወት አካል መበላሸት ብዙ ችግሮችን ያስከትላል”

- ዶክተር መለሰ ማሪዮ
የብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

ገጽ 6

ሱሰኝነትና የአዕምሮ በሽታ

ገጽ 8



አህጉሪቱን የማስተሳሰር ተስፋ የተጣለበት የአፍሪካ መሰረተ ልማት ፕሮግራም

ገጽ 14



የአልጋ ኪራይ-ከኬሻ በጠረባ እስከ G+8

ገጽ 16

## በውስጥ ገጾች


የአፍሪካ
“ከራስ ጋር እርቅ”
ገጽ 9

የቄስ ትምህርት እና የአሸር ቤት
ገጽ 12

# የዘመን እንግዳ

# “የአንድ በዓይን የማይታይ ትንሽ የሕይወት አካል መበላሸት ብዙ ችግሮችን ያስከትላል”

*ዶክተር መለሰ ማሪዮ*
*የብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር*

አስመረት ብስራት

ከተወለዱባት ሀዲያ አካባቢ ከሚገኝ የገበሬዎች መንደር የተገኙት ዶክተር መለሰ ማሪዮ በልጅነታቸው የእውቀት ቀንድ የተባሉ ጎበዝ ተማሪ ነበሩ። በወቅቱ 12ኛ ክፍልን ጨርሶ ዩኒቨርሲቲ መግባት እንደ ብርቅ የሚታይበት ጊዜ ስለነበር አብረዋቸው ከተፈተኑት ሶስት መቶ ሀምሳ ተማሪዎች ሁለቱ ብቻ ሲያልፉ እርሳቸው አንዱ ነበሩ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ክፍል በባዮሎጂ የትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ተቀብለዋል። ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በእፅዋት ሳይንስ ጨረሱ። 3ኛ ዲግሪያቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አግሮ ባዮ ዳይቨርሲቲ በሚባል የትምህርት ዘርፍ ጨረሱ።

ሥራ የጀመሩት በሁለተኛ ደረጃ መምህርነት በሀላባ በሚገኝ ህፃናት አምባ ትምህርት ቤት ነበር። ለስምንት ዓመታት አገልግለዋል። በመቀጠል ዲላ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በመምህርነትና ተመራማሪ በመሆን፤ በተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ኃላፊነት ቦታ ላይ ከ15 ዓመታት በላይ አገልግለዋል። ከዛም የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ በነበሩበት ወቅት ተቋማት በኤክስፐርቶች ይመሩ በሚል ሀሳብ የብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር በመሆን ለስድስት ዓመታት አገልግለዋል፤ አሁንም እያገለገሉ ይገኛሉ።

በዩኒቨርሲቲና በብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት ውስጥ በርካታ ከብዝሃ ህይወት ጋር የተገናኙ ምርምሮችን ከማድረጋቸው በሻገር፤ አሁንም በበጎ ፈቃደኝነት ኮተቤ ሜትሮ ፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የተለያዩ ሙያዊ ድጋፎችን ያደርጋሉ። ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ የ3ተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ያማክራሉ።

በተጨማሪም የዲላ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ፤ የጉለሌ ቦታኒካል ጋርደን ቦርድ፤ የግብርና ሴክሬተርያት ፅህፈት ቤት የቦርድ አባል፤ የዓለም አቀፉ የብዝሃ ህይወት ስምምነት የኢትዮጵያ ፎካል ፐርሰን ሆነው አገልግለዋል፤ ስምምነቱን ከፈረሙት 196 አገራት አፍሪካን በመወከል በዓለም ካሉ 10 የቢሮ አባላት ውስጥ አንዱ በመሆን የአፍሪካ የብዝሃ ህይወት ችግሮችን በማንሳት የሚሰሩ ሰው ሆነው ከአራት ዓመት በፊት ጀምሮ እያገለገሉ ይገኛሉ። እነኚህን ተመራማሪ በብዝሃ ህይወት ዘርፍ እና አጠቃላይ ስላሳቸው ተሞክሮና የተለያዩ የህይወት ልምዳቸው በዚህ መልኩ አካፍለውናል። መልካም ቆይታ።

**አዲስ ዘመን፤- በርካታ ምርምሮችን አድርገዋልና ምን ምን አይነት አካባቢዎች የነካኩ ምርምሮችን ሰርተዋል?**

**ዶክተር መለሰ፡-** ምርመር ካደረኩባቸው ዘርፎች አንዱ መድኃኒታዊ እጽዋትን ፈዋሽነት በጥናት ማረጋገጥ አንዱ ነው። በአብዛኛው ጥብቅ ደኖች ውስጥ ያሉ መድሀኒቶችን የማጥናት ስራ ይሰራል። በጥናቱ መሠረት ከ100 ሺህ በላይ መድኃኒትነት ያላቸው እጽዋት በአካባቢው እንደሚገኙም ተረጋግጧል።

እንደነ ቻይና ያሉ በኢኮኖሚ የበለጸጉ አገራትም ባሕላዊ ሕክምናን ከዘመናዊው ጋር አጣምረው በሚገባ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። የአሜሪካ ብሔራዊ የጤና ተቋምም የቻይናን ባሕላዊ መድኃኒት ውጤታማነቱን እና ሁነኛ አማራጭ መድኃኒት መሆኑን አረጋግጧል፤ ጥቅም ላይ እንዲውሉም ፈቅዷል። በዚህ ወቅትም የቻይና ባሕላዊ መድኃኒት ፈዋሽነቱ ውጤታማ በመሆኑ በርካታ ተጠቃሚዎች አሉት። ለአገሪቱ ዜጎችም እንደ አንድ ሙያ ተደርጎ ተወስዷል።



ፎቶ፡ ፀሐይ ገጉሜ

**እኛ ሀገር ጥናቶች ዝም ብለው እንዲታተሙ ይደረጋል፤ ይህ ደግሞ የማህበረሰብ ሀብትን አሳልፎ እንደመስጠት ነው፡፡ ስለዚህ ያለንን የምርምር አቅም ወደ ፋብሪካ ምርትነት በመቀየር ውጤታማ መሆን አለብን**

በእኛም አገር ባሕላዊ መድኃኒት የጥንት አያቶቻችን ያወረሱን የአገር በቀል ዕውቀት ነው። ይህ ውርስ በአግባቡ ተጠብቆ ባለመቆየቱ እጽዋቱ የሚሰጡትን አገልግሎት በአግባቡ መጠቀም እንዳንችል አድርጎናል። የአገር በቀል እውቀቶችን ትሩፋት ለመካፈልና ለቀጣይ ለትውልድ ለማስተላለፍ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ መድኃኒታዊ እጽዋትን ማልማት፣ አጠቃቀማቸውንና ያላቸውን ፋይዳም ከአባቶች በመጠየቅ ወቅቱ እና የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ በሚፈቅደው መልኩ በዘመናዊ መንገድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ሌሎች በመጥፋት ላይ ስላሉ ደኖች፤ ስለ አዝእርትና ሆርቲ ካልቸር፤ ዝርያቸው እየጠፉ ስላሉ እንስሳትና ሌሎች ጥናቶችን በየጊዜው ስናደርግ ቆይተናል።

በአገራችን እንደ ባህል ሆኖ ጓሮ አካባቢ ዳማከሴና ጤና አዳምን መትከል የተለመደ ነው። ብርድ ብርድ የሚል ስሜት ሲሰማ ዳማከሴን አሽቶ ከቡና ጋር መጠጣት ማሽተትም ለምች ፍቱን መድኃኒት ነው ይባላል። ለራስ ህመም ጠንከር አድርጎ ማሰር፣ ለጉንፋን ዝንጅብል በማር፣ ለሆድ ድርቀት ተልባን በጥብጦ መጠጣት ብዙ ኢትዮጵያውያን ለራሳቸው ሆነ ለወዳጆቻቸው ፈውስ ብለው የሚመክሯቸው መሆናቸው የባህል ህክምናን እንደፈውስ አድርጎ የመቀበል ዝንባሌያችን ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል። በገጠሪቷ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በከተማም በሽታ ባስ ካላለ ወደ ህክምና ተቋማት መሄድ የተለመደ አይደለም፤ ቤት ውስጥ የተገኘውን በሙሉ ተጠቅሞ ፈውስን ፍለጋ ተቀዳሚ ምርጫችን እናደርገዋለን።

ባህላዊ ህክምና በሥሩ በርካታ የባህል መድኃኒት ዘርፎችን ያቅፋል። በተለይ ከባህላዊ መድኃኒት ዘርፍ ውስጥ ባህላዊ የዕፅዋት መድኃኒት ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል። ባህላዊ መድኃኒት ከጥንት ጀምሮ ዛሬ ድረስ በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድ በህክምናው መስክ ከፍተኛ የሆነ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሀገረ ሰባዊ የዕውቀት ዘርፍ ነው። ይህን ሀገረሰባዊ የእውቀት ዘርፍ እንዲያድግ ደግሞ ተፈጥሮ የለገሰችውን መድኃኒታማ ቅጠላ ቅጠልና ሥራ ሥር መንከባከብ የግድ ነው።

ኢትዮጵያ ከ6500 እስከ 7500 የአበባ ዕፅዋት አላት ተብሎ ይገመታል። ከዚህ ውስጥ 20 በመቶ የሚሆኑት በተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በመድኃኒትነት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ጥናቶች ያመለክታሉ። በአብዛኛው ከእነዚህ መድኃኒታማ ተክሎች መካከል 70 በመቶ የሚሆኑት ዱር በቀል ናቸው። እኛ አገር ጥናቶች ዝም ብለው እንዲታተሙ ይደረጋል፤ ይህ ደግሞ የማህበረሰብ ሀብትን አሳልፎ እንደመስጠት ነው። ስለዚህ ያለንን የምርምር አቅም ወደ ፋብሪካ ምርትነት በመቀየር ውጤታማ መሆን አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ብዝሃ ህይወት ምንድን ነው?**

**ዶክተር መለሰ፡-** ብዝሃ ህይወት ማለት በመሬት ላይ ያሉ ሁሉም ስነ-ህይወታዊ ሀብቶች፣ እፅዋት፣ እንስሳትና ደቂቅ አካላት እንዲሁም በውስጣቸው የያዟቸው ዘረ-መሎችና እነዚሁ የሚፈጥሯቸውን ውህዶች የሚያካትት ነው። በመሆኑም ብዝሃ ህይወት በዓለም ላይ የ ህያዋን ዝርያዎችን ያካተቱ ዛፎች፣ የሣር ዝርያዎች፣ ቁጥቋጦዎች፣ በራሪ አዕዋፋት፣ ባክቴሪያዎች፣ ትላትሎች፣ ተሣቢና ተራማጅ እንስሳት፣ በውሃ ውስጥ የሚገኙ ፍጥረታትን ጨምሮ የሁሉም ህይወት ያላቸው አካላት ስብስብን ያካተተ የወል መጠሪያ ነው።

ብዝሃ ህይወት ለዘላቂ የህይወት ቀጣይነት ብቸኛው መሰረት ነው። የእዚህ ህይወታዊ ሀብት ስርጭት በዓለም ዙሪያ ተመሣሣይ እንዳልሆነ የሚታወቅ ሲሆን በብዝሀ ህይወት ሀብታቸው ከታወቁት ውስን አገራት መካከል አንዷ አገራችን ኢትዮጵያ ናት። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው የብዝሃ ህይወት ሀብት የመመናመን አደጋ የተጋረጠበት በመሆኑ አብዛኛዎቹ የአገሪቱ ክፍል የብዝሀ ህይወት ሀብት ጥበቃ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገባ የተለዩ የዓለማችን አካባቢዎች አንዷ እንደሆነች የተለያዩ መረጃዎች ያመላክታል።

አገራችን በሰብል ጄኔቲክ ሀብት ከ12 አገሮች አንዷ ስትሆን፤ በደን ብዝሀ ህይወት ሃብቷ ደግሞ ከ25 አገሮች አንዷ በመሆን ትመደባለች። ኢትዮጵያ ውስጥ በመጀመርያ ተገኝተው የመጀመሪያው የጀኔቲክ ማእከል ካደርግዋት የሰብል ምግብ እፅዋት ዝሪያዎች ውስጥ ጤፍ፣ ኑግ ሰናፍጭ፣ እንሰሳትና ቡና ሲሆኑ፤ ከሌላ አገር ገብተው 2ኛ የጀኔቲክ ማእከል ያደረግዋት የምግብ ሰብሎች ደግሞ ዳጉሳ፣ ምስር ፣ ተልባ፣ ገብስ እና ስንዴ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ደቂቀ አካላት የምንላቸው ምንድን ናቸው?**

**ዶክተር መለሰ፡-** ደቂቀ አካላት (ማይክሮ ኦርጋኒዝምስ/ማይክሮብስ) አጉልቶ በሚያሳይ መነጽር ካልሆነ በዓይን የማይታዩ የፍጥረት አካላት ናቸው። እነዚህ አካላት ቫይረስ፣ ባክቴሪያ፣ ፈንገስ፣ ማይክሮ አልጌና ፕሮቶዝዋ ይባላሉ። ከሃይማኖታዊ ውጭ በሳይንሳዊ መንገድ ካየን ዓለም ገና ስትፈጠር የነበሩ የመጀመርያው ፍጥረታት ደቂቀ አካላት ናቸው። ይህም በመሆኑ ኦክስጅንና ፎቶሲንተሲስን ለዓለም አበርክተዋል። እንዲሁም ካርቦንዳይ ኦክሳይድን የሚያመጡ ናቸው። እንዳው በአጠቃላይ ለቀጣዩም የፍጥረት ዓይነት መነሻ የሆኑ ነገሮችን ያመቻቹ፣ ለእንስሳትም ሆነ ለሰው የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ ያለስስት በመስጠት ሕይወት እንድትቀጥል የሚያደርጉ

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

ናቸው። እኛ የምንመገበውን ምግብ ጥርሳችን በግርድፉ ከፈጨው በኋላ ወደ አንጀታችን ይገባል። አንጀታችን ውስጥ በግርድፉ የገባውን እህል አድቅቀውና አዋህደው እንዲሠራጭ የሚያደርጉት ደግሞ ሆዳችን ውስጥ ያሉት ደቂቀ አካላት (ማይክሮ ኦርጋኒዝምስ) ናቸው።

በምግባችን እርሾን ይሠራሉ። እንጀራ ቢጋገር፣ ዳቦ ቢደፋ፣ ጠላ ቢጠመቅ ወተት ቢረጋ ዝርያቸው ይለያይ እንጂ ይህን የሚያደርጉት ደቂቀ አካላት ናቸው። ስለዚህ ከእኛ ጋር ይኖራሉ፣ እኛን ያግዛሉ። ከዚህም ሌላ ከአፈር ውስጥ ያለውን ንጥረ ነገር እየሰባበሩና እየመጠኑ በመስጠት እፀዋት እንዲያድጉ እንዲሁም እንስሳት ሆድ አንጀት ውስጥ ያለውን የሚበላ ነገር እንዲብላላ በማድረግ ረገድም ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። እነዚህ ደቂቀ አካላት ከተፈጠሩ ከሁለት ቢሊዮን ዓመታት በኋላ ሌሎች ሕይወት ያላቸው እንደመጡ ሳይንስ ያስረዳል።

ደቂቅ አካላት ቁጥራቸውን መግለፅ ይከብዳል። በአንድ ትንሽ የሻይ ማንኪያ አፈር ውስጥ እስከ ሁለት ቢሊዮን የሚሆኑ ደቂቅ አካላት እንደሚኖሩ ይገመታል። ከእነዚህም ውስጥ 0 ነጥብ 01 በመቶ ያህሉ የሚታወቁ ሲሆን፣ ከሚታወቁም መካከል በሽታ አምጪ በመባል የተሰየሙት በጣም ጥቂቶቹ ናቸው። ገና ከጅምሩ ግን አፈጣጠራቸው ሲታይ በሽታ አምጪ አልነበሩም። በሽታ አምጪ ሊሆኑ የቻሉት የሚኖሩበት አካባቢ በሰው ሲዛባ ወይም ሲጠቃ ነው። በዚህ ጊዜ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለመፈለግ ሲሉ ወደ ሰው ይሄዳሉ። ከዚህም ያረፉበትን ሰው ሊጎዱ ይችላሉ። አሁን የመጣው ኮሮናም የዚህ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። እነርሱ ግን አይሞቱም፤ ሕይወት ይቀጥላል።

ደቂቀ አካላት የሚኖሩት በሁለት መንገድ ነው። ይህም ከአካባቢው ጋር ይላመዳሉ ወይም የአካባቢውን ሥነ ምኅዳር ለእነርሱ በሚስማማ መልኩ ይለውጣሉ። በአጠቃላይ ባዮሎጂካል ኢሞርታል (ለዘላለም የሚኖሩት) ከሚባሉት የፍጥረት ዝርያዎች መካከል አንዱ ደቂቅ አካላት ናቸው።

ለምሳሌ ያህል አንበሳ የሚኖረው ሰንበሌጥ፣ ጫካና ሌሎች እንስሳት ባሉባቸው አካባቢ ነው። ይህ ዓይነቱ አካባቢ በሰው ሲነካበት ወይም ሲራቆትበት ሥነ ምኅዳሩ ይናጋበታል፣ ይበላሽበታል። በዚህም የተነሳ ወደ ሰው መጠጋቱና መተናኮሉ አይቀሬ ነው። ከዚህም አኳያ ደቂቅ አካላት አካባቢያቸው ሲናጋ ወይም ኢኮ-ሲስተማቸው ሲዛባ ወደ ሰው በቀላሉ ይተላለፍና ይላመዳሉ። ሰውነታችን ደግሞ ከእነሱ ጋር ትውውቅ ስላልነበረውና ያንን የመከላከል አቅም ስላላዘጋጀ የመጀመርያው ጥቃት ሞት ነው። በሂደት ውስጥ ግን ሰውነታችን ያንን የመከላከል ብቃት ይጨምራል። ይኼም በኮሮና ቫይረስ የታየ ነው።

መታሰብ ያለበት አንዱ ትልቅ ነገር ቢኖር የትኛውም የፍጥረት አካል የሚኖረው በመስተጋብር፣ በመረዳዳትና በመተሳሰር ነው። የተፈጥሮ ሕግም የሚለው ይህንኑ ነው። ሰው ግን በተፈጥሮ ሲኖር ራሱን የበላይ አድርጎ ይቆጥራል። በዚህም የተነሳ ተፈጥሮን እንደፈለገው ለማድረግ ይንቀሳቀሳል። በዚህ እንቅስቃሴ ተፈጥሮን እያሳሳ ይሄዳል። የአንድ በዓይን የማይታይ ትንሽ የሕይወት አካል መበላሸት ብዙ ችግሮችን ያስከትላል።

የደቂቀ አካላት መኖሪያ የትም ነው። አይኖሩበትም የተባለ ቦታ የለም። ሰው በማይኖርበት ቦታ ሁሉ ይኖራሉ። አካባቢን ያሳመሩም እነሱ ናቸው። እንዲያውም የምድር ኢንጅነሮች ይባላሉ። ደኑ ለልማት ሲውል በተጠናና በተጠበቀ መንገድ መሆን አለበት። መነካትና ዝም ተብሎ መጨፍጨፍ የለበትም። እርሻ ላይ ያሉ የአዝዕርት ዝርያዎች እኛ ዘንድ አሉ። ለምን ቢባል በአንድ ወቅት እንዳይጠፉ ነው። የእንስሳት ዝርያዎች አርሶ አደሩ በአግባቡ እንዲጠብቅ እናስተምራለን። የእንስሳት ዘረ መልን እናቀርባለን።

የተፈጥሮ አካባቢ ከሰው ንክኪ ነፃ እንዲሆን እንሠራለን። የአካባቢ መጠበቅ ደግሞ በዓይን የማይታዩ ደቂቅ አካላት የተጠበቁ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ከዚህም ሌላ በኢንስቲትዩቱ ለዚህ ሲባል በተዘጋጀ ቀዝቃዛ ክፍል ውስጥ ደቂቀ አካላትን እናስቀምጣለን። በሽታ አምጭ ናቸው የተባሉ ደቂቀ አካላትም ጥቅም ስላላቸው እንይዛቸዋለን። ጥቅማቸውም ለፈውስ የሚሆን መድኃኒት ከነሱ ማምረት መቻሉ ነው።

እነዚህን ለማንበርና ለመለየት ባክቴሪያ ላይ የሠራ፣ ስለቫይረስ የተማረ፣ በሁለተኛ እና በሶስተኛ ዲግሪ ደረጃ ፈንገስና ማይክሮ አግሪ ላይ የተማረ ባለሙያና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያስፈልጋል። እነዚህን የተዘረዘሩት ባለሙያዎችና ቴክኖሎጂዎችን ኢንስቲትዩቱ በተፈለገው መልኩ አላሟላም። ይህም የሆነበት ምክንያት ለኢንስቲትዩቱ እንደ አገር የተሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ ነው።

**አዲስ ዘመን፡-የእንስሳት ዝርያዎች እንዳይጠፉ ምን ምን ስራዎች ይሰራሉ?**

**ዶክተር መለሰ፡-** እንስሳቶች እንዳይጠፉ የማንበር ሥራዎች ይሰራሉ። የእንስሳቱ ጥበቃ የሚከናወነው በሁለት መልክ ነው። ይህም አንደኛ በኢ ዘቦታ በሚባለው መንገድ ነው። ይህ ኢዘቦታ የሚባለው የማንበር መንገድ ዝርያቸው የተመናመኑትን የወንድ አባላዘር በመሰብሰብ በጂን ባንክ በማስቀመጥ እንደ አስፈላጊነቱ የማሰራጨት እና ዝርያ እንዳይጠፋ የማድረግ ተግባር ነው። በዘቦታ የሚባለው የማንበር መንገድ ደግሞ ዝርያው በማህበረሰቡ እጅ ሆኖ ከተፈጥሮ አካባቢያቸው ሳይወጡ እዛው ጥበቃ እንዲደረግላቸው ለማድረግ ነው።

ይህም ማለት አገር በቀል ዝርያዎች ሆነው ከእነሱ መካከል ከፍተኛ መጠን ያለው ምርት የሚሰጡትን በመምረጥ የማዳቀል ሥራ ነው። ለምሳሌ ከወተት ምርት አንፃር፤ ከስጋ ምርት አንፃር፤ የተሻለ ዝርያ ያላቸውን በማዳቀል እና አገሪቱ ባላት የጀነቲክ ሀብት በዘላቂነት የምትጠቀምበትና ህብረተሰቡም በተወሰነ አቅም ብዙ ምርት የሚያገኝበትን አካሄድ ለማስቀጠል የተለያዩ ምርምሮች ብሎም በተግባር የሚከናወኑ ሥራዎች ይሰራሉ።

የተሻሉ ምርቶችን ለማግኘት ከመስክ ጀምሮ በላብራቶሪ የተደገፉ የምርምር ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው። በሁሉም የእንስሳት ዘርፍ ምርምር የሚያደርጉ ከመጀመሪያ ዲግሪ እስከ ፒ ኤች ዲ ዲግሪ ደረጃ ድረስ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ተመራማሪዎች በያዘ የተለያዩ የምርምር ሥራዎች ይሰራሉ።

የዝርያ መጥፋት ስጋት ያለባቸው እንስሳት ማለትም የመጥፋት አደጋ ያንዣበበባቸው ናቸው ሲባል፤ ቁጥራቸው በዓለም አቀፉ እስታንዳርድ ከ250 በታች ሲሆን ነው። የእንስሳቱ ቁጥር እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ዝርያውን መመለስ አዳጋች እንዲሆን ያደርገዋል።

በአገራችንም ይህ ስጋት ያንዣበበባቸው ሁለት ዝርያዎቸ አሉ። የሸኮ ዳልጋ ከበትና የቁንዱዶ ፈረስ ዝርያዎች ቁጥራቸው እጅግ ዝቅ ብሎ ነበር። የቁንድዶ ፈረስ በ2006 ዓ.ም ቁጥራቸው ስድስት ነበር። ከማህበረሰቡ ጋር በመሆን በተሰራው ስራ ቁጥራቸው ወደ 31 ከፍ ብሏል። እነዚህ የቁንዱዶ ፈረስ ዝርያዎች የፈረስ አይነት ሆነው በዱር የሚኖሩ የፈረስ ዝርያዎች ሲሆኑ፤ በተለያዩ ምክንያቶች ተመናምነው ነበር። ምንም እንኳን አሁን ቁጥራቸው የማንሰራራት ሁኔታ ላይ ቢሆንም ከመጥፋት አደጋ ስጋት እንዲወጡ እየተሠራ ነው።

ለእዚህም በአካባቢው የሚገኘው የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ፤ የኦሮሚያ የአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን፤ የአካባቢው ማህበረሰብ እና ኢንስቲትዩቱ በጋራ በመሆን ዝርያው ከአደጋ ስጋት ነፃ እንዲሆን እየተሰራ ነው።

ሌላው የመጥፋት ስጋት ያንዣበበባቸው የሸኮ ዳልጋ ከብት የሚባሉት ዝርያዎች ናቸው። መገኛቸው በደቡብ ክልል ሆኖ ልዩ የሚያደርጋቸው አገሪቱ ካላት 28 የቀንድ ከብት ዝርያዎች በፀፀ ዝንብ ምክንያት የሚመጣውን ፀፀ በሽታ መቋቋም የሚችሉና በቀላሉ በበሽታው በመጠቃት የማይሞቱ ናቸው። እነዚህ ዝርያዎችም ቁጥራቸው ወርዶ የነበረ ሲሆን፤ የአካባቢውን ማህበረሰብ በማደራጀት የእዚህን ዝርያ ኮርማ እንዲጠቀሙ በማድረግ ዝርያው ከስጋት እንዲወጣ ብሎም እንዲያገግም ተሰርቷል።

ከዚህም በተጨማሪ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ዝርያቸውን የማብዛት ስራ እየተሰራባቸው ያሉ የቦረና፤ የሸኮ፤ ቤጋይት፤ ፎገራ፤ ቤጋሪያ ዳልጋ ከብቶችን ሲሆን፤ ይህ የቦረና ዳልጋ ከብት ቀደም ሲል የመጥፋት ስጋት ነበረበት። አሁን በተከሰተው የድርቅ አደጋ ምክንያት ዝርያው የመመናመን ሁኔታ ታይቶበታል። ቦረና አካባቢ ያለው ይህ ዝርያ እንዳይጠፋ ተቋሙ ወደ አንድ ሚሊየን



**ብዝሃ ህይወት ማለት በመሬት ላይ ያሉ ሁሉም ስነ-ህይወታዊ ሀብቶች፣ እፅዋት፣ እንስሳትና ደቂቅ አካላት እንዲሁም በውስጣቸው የያዟቸው ዘረ-መሎችና እነዚሁ የሚፈጥሯቸውን ውህዶች የሚያካትት ነው**

ብር የሚጠጋ ገንዘብ ወጪ በማድረግ መኖ የማቅረብ ሥራ ሰርቷል።

በሥራ ክፍሉ ዝርያ የማሻሻል ስራ ይሰራል ሲባል የውጭ ዝርያዎቸን እያመጡ ማዳቀል ሳይሆን በአገር ውስጥ የተሻለ ምርት የሚሰጡትን በመለየት በማዳቀል የእነሱን ዝርያ የማብዛት ስራ እየተሰራ ነው። ከውጭ ከሚመጡት በተሻለ የአካባቢውን ችግር መቋቋም የሚችሉ በመሆናቸው ቅድሚያ ተሰጥቶ ይሰራል።

የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ላይ የሚሰሩ ጥናቶች በጣም ውስን ከመሆናቸው የተነሳ የሚገኙ ውጤቶችም ተመሳሳይ የሆነ ቁጥሮች ናቸው። ለምሳሌ የውሃ ውስጥ አካላት በጣም በርካታ ዝርያዎች ቢኖሩም በአገሪቱ ተጠንቶ ቁጥሩ ሊታወቅ የቻለው ግን የአሳ ዝርያ ብቻ ነው። በአገራችን የሚገኙ የአሳ ዝርያዎችም ወደ 200 ዝርያ የሚጠጉ መሆናቸው በጥናት ተለይቷል።

በዘርፉ በቂ ባለሙያ አለመኖሩ ስራው በስፋት እንዳይሰራ ያደረገው መሆኑን ገልፀው፤ ወደፊት ባለሙያው ሲፈጠር በጥናት ሊለይ ይችላል በማለት ዝርያዎች እንዳይጠፉ ለማድረግ የመሰብሰብ ስራ ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል።

በአጠቃላይ የተፈጥሮ ገፀ በረከት እንዳይጠፉ የመባዛት፤ ዝርያውን የመሰብሰብ፤ የመመራመር ስራን በመስራት ከምድረ ገፅ የሚጠፉ ሀብቶቻችንን የመጠበቅ ስራ የብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት እየሰራ ነው። ማህበረሰቡ ግን ዝርያዎች የመጥፋት አደጋ እንዳይጋረጥባቸው በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት ይኖርበታል።

**አዲስ ዘመን፡ ብዝሃ ህይወትን ማንበር ስንል ምን ማለታችን ነው?**

**ዶክተር መለሰ፡-** ምድር ተፈጥሯዊን ጠብቃ ትኖር ዘንድ የብዝሃ ህይወት ሀብትን ለይቶ መንከባከብ ተገቢ ነው። የብዝሃ ህይወት ሀብቶችን መጠበቅና መንከባከብ ሲባል ግን ዘሩን ሰብስቦ ከማንበር በዘለለ ተፈጥሮ የለገሰቻቸውን ሀብቶች አካባቢያዊ ስነ ምህዳር እንደጠበቀ ለማቆየት የግድ የስርዓት ምህዳር መስተጋብር መጠበቅ ይኖርበታል።

የብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት ሀብት የመጠበቅ የመንከባከበና ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት ይዞ የሚንቀሳቀስ፤ ብዝሀ ህይወት ላይም ጥናትና ምርምር የሚያካሂድ ተቋም ነው። ተቋሙ መጀመሪያ ሲቋቋም የግብርና ሰብሎችን መሰረት አድርጎ የተቋቋመ ነበር። በሂደት ግን እየተደራጀ እየተሻሻለ መዋቅራዊ ለውጥ እያደረገ ከግብርና ሰብሎች ውጪ ያሉ ሰብሎችን በተለይ ደግሞ የዓለም አቀፉ የብዝሀ ህይወት ስምምነት በ1991 በፈረንጆቹ አቆጣጠር ከፀደቀ በኋላ ሁሉንም የብዝሃ ህይወት ሀብቶችን ማለትም የእንስሳትና የዕፅዋት አጠቃላይ የደቂቀ አካላት ምርምርና ጥበቃ ሥራዎች ሲሰራ ኖሯል።

ብዝሃ ህይወትን እንጠብቅ ሲባል የምንጠብቀው ለምንድ ነው? በመጠበቃችን የተነሳ ከመክሰር የምናድነው ዋጋስ ስንት ነው? ቢጠፉስ ምን ይጎዳሉ? የሚሉት ለመለየት ሰዎች ተፈጥሮን ዘላቂነቱን በጠበቀ መልኩ እንዲያከናወኑት በማድረግ የተፈጥሮ ሀብትን በዘቦታ ማለትም ባሉበት የተፈጥሮ ሰነምህዳርና በኢ ዘቦታ ደግሞ በጀነቲክ ማቆያ የማንበር ተግባራትን ያከናውናሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ዶክተር ቀሪ ዘመናቸውን ምን በመስራት ቢያሳልፉ ደስ ይላቸዋል የሚል ጥያቄ ሳነሳ ወደድኩ መልሶ ምን ይሆን?**

**ዶክተር መለሰ፡-** ቀሪ ዘመኔን በጀመርኩት የማስተማር ስራ፤ የተለያዩ ምርምሮችም ፋብሪካ ገብተው ተጨባጭ ወጤት በማምጣት የአገር ኢኮኖሚ የሚያድግበትን ሰራ ለመስራትና የተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራ ላይ ብሰማራ ደሰ ይለኛል።

**አዲሰ ዘመን፡- ውድ ጊዜዎን ሰውተው ጠቃሚ ሀሳብ ስላካፈሉን እናመሰግናለን።**

**ዶክተር መለሰ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## ሱሰኝነትና የአዕምሮ በሽታ

እፀገነት አክሊሉ

**የአእምሮ ጤና ማለት ምንም ዓይነት የአእምሮ ሕመም አለመኖር ብቻ ሳይሆን የአዕምሮ ጤና ችሎታችንን የምንገነዘብበትና የመደበኛ ህይወት ጭንቀቶችን የምንሸከምበት መንገድ ነው። ከዚህ ውጪ ሲሆን ደግሞ በአስተሳሰባችን፣ በስሜታችን፣ በድርጊታችን እንዲሁም በህይወታችን ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። የአእምሮ ጤና ከዓለም አቀፍ የበሽታዎች ሸክም 14 በመቶ የሚሆነውን መያዙም ይነገራል።**

**በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአገራችን በጣም የተለመዱት የአዕምሮ ህመሞች ማለትም ድብርት፣ ጭንቀት፣ የስሜት መለዋወጥ፣ ከአሰቃቂ ጭንቀት በኋላ የሚከሰቱ ችግሮች ፣ እፅ መጠቀምና ሌሎችም ናቸው። እኛም በተለይም ሱሰኝነት በአእምሮ ጤና ላይ ሲያሳድር የሚችለውን ችግር እንዲሁም መፍትሔውን በተመለከተ በቅዱስ አማኑኤል አእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የክሊኒካል ሳይኮሎጂ ባለሙያና የቡድን መሪ ከሆኑት ከአቶ ስዩም ዘውዴ ጋር ቆይታን አድርገናል።**

**አዲስ ዘመን፡- የአእምሮ ጤና ስንል ምን ማለታችን ነው?**

**አቶ ስዩም፡-** የአእምሮ ጤናን ስናስብ ከግምት ልናስገባቸው የሚገቡ ሶስት መሰረታዊ ነገሮች አሉ፤ እነዚህም ባህርይ ስሜትና አስተሳሰብ ናቸው። ከዚህ አንጻር የአእምሮ ጤና ስንል እነዚህን ሶስቱን ነገሮች አቀናጅቶ እለት ተእለት የምናደርጋቸውን ነገሮች ጤናማ በሆነ መልኩ መተግበር ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአእምሮ ህመምስ ስንልስ ምን ማለታችን ነው?**

**አቶ ስዩም፡-** የአእምሮ ጤና ብለን ስንተረጉም ያነሳናቸው ሶስት መሰረታዊ ነገሮችን አስተካክሎ በእለት ተእለት ኑሮው ውስጥ የሚተገብር አካል የአእምሮ ጤንነቱ የተረጋገጠ ሲሆን እነሱን በትክክል መተግበር ሳይቻል ሲቀር ደግሞ በአእምሮ ላይ ችግር አለ ማለት ነው።

በጠቅላላ የአእምሮ ጤና ችግር የሚባለው ጤነኛ አስተሳሰብ ባህርይና ስሜትን አቀናጅቶ በአግባቡ መተግበር አለመቻል ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- የአእምሮ ጤና በምን ምክንያት ሊጎዳ ይችላል ?**

**አቶ ስዩም፡-** አእምሮ የተፈጠረው ከተለያዩ ኒውሮሎችና ኬሚካሎች ነው። የእነዚህ ኬሚካሎች በተለያየ ምክንያት መዛባት፣ ከመጠን በላይ መመረት ወይንም ማነስ ለአእምሮ ህመም ይዳርጋል።

ሌላው ምክንያት ደግሞ ስነ ልቦናዊ ሲሆን ይህም ማለት በእለት እለት እንቅስቃሴያችን በግል ህይወታችን ላይ የሚደርሱ የተለያዩ ጫናዎች ሲያጋጥሙን የሚፈጠር ነው። ለምሳሌ በአኗኗራችን፣ የሚወዱትን በማጣት፣ በጦርነት፣ ብዙ አደጋዎችን በማስተናገድና በተለያየ ምክንያቶች ጭንቀት ውስጥ በሚያስገቡ አጋጣሚዎች ለአእምሮ ህመም መጋለጥ ይከሰታል።

ከእነዚህ በተጨማሪም ማህበራዊ ምክንያቶች አሉ፤ በተለይም በማህበረሰቡ ውስጥ ከአእምሮ ህመም ጋር ወይም በእለት ተዕለት ህይወታችን ላይ የምናዘወትራቸው ትክክል ያልሆኑ ባህርያት ለአእምሮ ህመም ልንጋለጥ እንችላለን። ከነዚህ ውስጥም ሱስ መጠቀም፣ ሌሎች ሰዎች የሚያሳድሩብን ጫና፣ ያደግንበት መንገድ ና ሀይማኖታዊ ሂደቶች ይጠቀሳሉ፤ እዚህ ላይ ግን ልብ ሊባል የሚገባው ሀይማኖት በራሱ ለአእምሮ ህመም አጋላጭ ነው ማለት ሳይሆን፤ ሀይማኖት ውስጥ በሚኮንበት ጊዜ እርስ በእርስ የሚፈጠሩ ግጭቶችና ጥያቄዎች አእምሯችን ላይ የሚፈጥሩት ጠባሳ ለስነ አእምሮ ቀውስ የመዳረግ እድሉ ሰፊ መሆኑን ለመግለጽ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአዕምሮ ጤናን ሊጎዱ ከሚችሉ ነገሮች መካከል ሱስ ተጠቃሽ ነውና ሱስ ሲባል ግን ምን ዓይነት ሱስ?**

**አቶ ስዩም፡-** ሱስ ብለን ስናስብ የአእምሮን አሰራር መቀየር የሚችሉ ንጥረ ነገሮችን ያካተተ ሲሆን እዚህ ላይ አሰራሩ በጣም ፈጣን አልያም በጣም አዝጋሚ እንዲሆን ሊያደርጉ የሚችሉ ሱስ አምጪ የሆኑ ነገሮችን በምንጠቀምበት ጊዜ በሂደት የሚመጣ ችግር ይሆናል።

አንድ ሰው ደስተኛ አልያም ሀዘንተኛ የሚሆነው በምክንያት ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ግን ይህንን ለማድረግ ሊያስቸግር ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ደግሞ አእምሮ ብዙ ስለሚያስብ ከላላስፈላጊ ችግር ይጋለጣል።

በመሆኑም ሱስ አምጪ ነገሮች የአእምሮን አሰራር ስለሚቀይሩና ሁልጊዜ እነሱን ስንጠቀም እለት እለት የምናደርጋቸውን ስራዎች በአግባቡ ማከናወን ስለሚቸግረን ወደአእምሮ ጤና መታወክ እንገባለን ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አልኮል ሳይበዛ መጠጣት ለጤና ጥሩ ነው የሚሉ ሰዎች አሉ ፤ በዚህም ምክንያት በቀን አንድ ወይም ሁለት ይጠጣሉ፤ እነዚህ ሰዎች ወደሱስ ውስጥ የመግባታቸው ደረጃ ምን ያህል ነው?**

**አቶ ስዩም፡-** በስነ አእምሮ ህክምና ውስጥ አንድ ሰው በሱስ ተጠቂ ነው ብለን እንድንል የሚያደርጉ መገለጫዎች አሉ። በእኛ ማህበረሰብ ደግሞ የትኛውንም መጠጥ አንድ ሁለት መጠጣት ባህልም አልፎ ተርፎም መዝናኛ አድርጎ የመቁጠር ሁኔታ አለ። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ከፍ እያለ ከእለት እለት መጠኑን እየጨመረ ከገደብ እያለፈ ሲመጣ ወደሱስነት የመለወጥ አጋጣሚው ሰፊ ነው።

መጠኑ ከፍ እያለ ወደሱስነት ተሸጋገረ ማለት ደግሞ ሰዎች ከመጠጥ ውጪ ሲያከናውኗቸው የነበሩ ነገሮች ማከናወን የማይችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ማለት ነው። በመሆኑም እነዚህ ችግሮች እያደጉ ሲሄዱ ከሱሱ ጋር ተያይዞ የሚመጡ የጤና ወይም የአእምሮ ችግር እየተከሰተባቸው መሆኑን እያወቁ እንኳን እነዚያን ሱስ አስያዥ ነገሮች አቁመው ከሱስ ነጻ የሆነ ህይወት መኖር ሲያቅታቸው ነው።

አምጣ አምጣ የሚል ስሜት ከሚጠጣ ነገር ውጪ ራሳቸውን ማዘዝ እንዲሁም መረጋጋት ሲሳናቸው ባለመጠጣታቸው ጥሩ ያልሆኑ ባህርያት ሲከሰትባቸው እነዚህን ያጧቸውን ደስታዎች ለማግኘት ደግሞ ከፍተኛ የሆነ መጠን ያለው መጠጥን መጠቀም ሲጀምሩ እንዲሁም በማህበራዊ ህይወታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን ማሳደር ሲጀምሩ ድርጊቶቹ ወደሱስነት ደረጃ አድገዋል ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ሱስ የአእምሮ ጤናን እየጎዳ ነው ለማለት ምን ዓይነት ምልክቶች ይታያሉ?**

**አቶ ስዩም፡-** አንድ ሰው ሱስ የአእምሮ ጤናውን ጎድቶታል ስንል ሰዎች ሱሱን በመጠቀማቸው ምክንያት ጭንቀት ውስጥ ሲገቡ ነው። ለምሳሌ በግል ህይወታችን ላይ የሚፈጥረው ያለመረጋጋት ስሜት፤ ደስተኛ ያለመሆን ሁኔታ ሲፈጠር ሱሱ ወደከባድ የአእምሮ ጤና ችግር እየሄደ ነው ማለት ይቻላል፤

በሌላ በኩል አንድ ሰው በቀን ውስጥ 8 ሰዓት መስራት ካለበት ስራውን ከመስራት ይልቅ አብዛኛውን ሰዓቱን ለሱሱ በመስጠትና በመጠቀም ጊዜውን የሚያቃጥል ከሆነ በአእምሮ ጤንነቱ ላይ ቀውስ አስከትሏል ማለት እንችላለን።

ቀደም ብለን የአእምሮ ጤናን ትርጉም እንዳስቀመጥነው ማለትም ጤናማ የሆነ አስተሳሰብ ስሜትና ባህርይ ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር የአስተሳሰብ መዛባት ስሜትን መቆጣጠር አለመቻል እንዲሁም ከሰዎች የተለየ አዳዲስ ባህርያትን ማሳየት በግንኙነቶች ላይ ጤናማነት ማጣት ከተከሰተ ሱሱ የአእምሮ ጤንነታቸው ላይ ጉዳት እያስከተለ ለመሆኑ ምልክቶች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- በሱስ ምክንያት የአእምሮ መቃወስ የገጠመው ሰው ሲደረግለት የሚገባው ክትትልና ህክምና ከምንድን ነው የሚጀምረው?**

**አቶ ስዩም፡-** ሱስ እንደ ችግር ከምንቆጥረውና ከአእምሮ ህመሞች መካከል አንዱ ነው። በመሆኑም መጀመሪያ ሰዎች ሱስ መጠቀምን እንደ ችግር መረዳት ይገባቸዋል። ለዚህ ደግሞ በማህበረሰቡ ላይ ከፍ ያለ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን ደግሞ እነዚህን ሰዎች ማገዝ መርዳት እንዲሁም መረዳት ይቻላል።

ስለዚህ እነዚህን ሰዎች መንከባከብ የሚጀመረው ሱስ ለአእምሮ ጤና መታወክ አንዱ ምክንያት መሆኑን በመረዳት ነው። ከዛ ቀጥሎ ወደ ስነ ልቦና አማካሪዎችና ህክምና ተቋማት በመምጣት አስፈላጊውን የምክር እንዲሁም የመድሃኒት ህክምናዎችን በመከታተል ከሱሱ ማገገም ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ሰዎች ወደ ሱስ እንዳይገቡ ምን ማድረግ አለባቸው?**

**አቶ ስዩም፡-** አንድ ታዳጊ ወይም ወጣት አብዛኛውን ነገሩን አውቆና ተቀርጾ የሚወጣው ከቤተሰቦቹ በመሆኑ የመጀመሪያው ባለድርሻ አካል ቤተሰብ ነው። ቤተሰብ ልጆቹን ሲያሳድጉ ጤናማ በሆነ መልኩ እያስተማረ ከዛም አልፎ ሰዎች ወደሱስ በመግባታቸው ምክንያት ሊመጡባቸው የሚችሉትን ጉዳቶች እንዲረዱና ራሳቸውን ከዛ እንዲጠብቁ የሚያደርጉ ምክሮችን በመለገስ ሊሆን ይገባል።

ሌላው ደግሞ ልጆች በትምህርት ቤት ያሳልፋሉ ይህንን ጊዜያቸውን በምን መልኩ አሳለፉት የሚለውን የመከታተል ኃላፊነት ደግሞ የመምህራንና የትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ነው። በመሆኑም በትምህርት ስርዓታችን (ካሪኩለማችን) ውስጥ በሱስ ምክንያት ስለሚከሰቱ ችግሮች ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማስተማር መምከር መገሰጽ ማሳወቅ አሁንም ወደፊትም በሰፊው ሊሰራበት የሚገባ ነው።

እንደ አገርና መንግስት ደግሞ በተለይም አሁን አሁን በከተማችን ባሉ ትምህርት ቤቶች ዙሪያ የሚስተዋሉ ሱስ አስያዥ ቤቶችን በሌሎች ወጣቱን ሊስቡ ሊያዝናኑና እውቀት ሊያስጨብጡ በሚችሉ ነገሮች መቀየር ያስፈልጋል ። ለዚህ ደግሞ ፖሊሲዎችን መቅረጽና ማዘጋጀት ምናልባትም እንደ አገር ከተጋረጠብን አደጋ ያድነናል።

የመጨረሻው ግን በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ አልፎም ሰዎች በሱስ ውስጥ ይገባሉ። ለዚህ ደግሞ ምን እናድርግ ካልን በቅዱስ አማኑኤል አእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ውስጥ ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል የሱስ ማገገሚያ ማዕከል አንዱ በመሆኑ ሰዎች ችግር ውስጥ ከገቡ በኋላ ከችግሩ ጋር ረጅም ርቀት አብረው እንዳይቀጥሉ በሙያ የታገዘ አገልግሎት ስለሚሰጥ ወደዚህ መምጣቱ ጥሩ አማራጭ ነው።

መገናኛ ብዙኃንም አሁን ላይ ስር ስለሰደደው የሱስ ችግር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት ሰዎች እንዲረዱ ማድረግ ችግር ውስጥ ላሉትም መፍትሔ እንዳለው ማመላከት ይጠበቅባችኋል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ በአገራችን በሱስ ምክንያት አእምሮ ህመምተኛ እየሆኑ ያሉ ሰዎች መጠን ምን ይመስላል?**

**አቶ ስዩም፡-** አሁን ሆስፒታሉ ላይ ከሱስ ጋር በተያያዘ ችግር እንዲሁም በሌሎች የአእምሮ ጤና ቀውሶች ምክንያት ገብተው ተኝተው የሚታከሙ በርካታ ሰዎች አሉ። ስለ ሱስ ስናስብ ሁለት ነገሮችን ማሰብ አለብን። አንደኛው ሱስና ሱስን ብቻ በመጠቀም ለስነ አእምሮ ጉዳት የተጋለጡ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሱስን በመጠቀማቸው ምክንያት ለሌላ ህመም ተጋልጠዋል ወይም ደግሞ ከሌላ ህመም ጋር ተጨምሮባቸው አገልግሎት እያገኙ ያሉትን ነው። በመሆኑም እንደ አጠቃላይ ስናያቸው ብዙ ጊዜ የሱስ ማገገሚያ ተቋማቶች ህመምተኞቹ ስለራሳቸው የሚያውቁ በመሆናቸው ሲገቡም ራሳቸው ፈርመው ነው የሚመጡት፤ ከሱሱ ለመውጣትም ተዘጋጅተው የሚመጡ ናቸው።

በነገራችን ላይ ሌሎች የአእምሮ ህመምተኞችም የሱስ ተጠቃሚዎች ከመሆናቸው አንጻር ለይቶ መጠኑን መናገር ሊያስቸግር ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- ቅዱስ አማኑኤል የአእምሮ ህክምና ሆስፒታል በተለይም ከሱስ ጋር ተያይዞ ችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችን በምን መልኩ ነው የሚረዳው?**

**አቶ ስዩም፡-** ከሱስ ጋር ተያይዞ ለሚመጡ ህሙማን የምንሰጠው አገልግሎት በየስነ ልቦና ማማከርና የመድሃኒት ህክምና ነው። በመሆኑም የመጀመሪያው የህክምና አይነት በመድሃኒት የሚደረግ ሲሆን ይህ ህክምናም ሰዎች ብዙ ጊዜ ሱስ ውስጥ ሲቆዩ ሰውነት ውስጥ የሚቀሩ ኬሚካሎች የምንጸዳበት ነው። ቀጥሎም የስነ ልቦና ህክምና እንዲያገኙ ይደረጋል። በዚህም ሰዎች ተነቃቅተው አቅም አግኝተው ካሉበት ሁኔታ እንዲወጡ የሚያስችላቸው ነው። ይህንን ህክምና የሚያገኙ ሰዎች ደግሞ በተለያዩ መንገዶች ውስጥ ያልፋሉ አንዳንዶች ሱስ በመጠቀማቸው ምክንያት የሚከሰትባቸው ጉዳት እንደሌለ የሚያምኑም በመሆናቸው ሱስ በመጠቀማቸው የሚያመጣባቸውን ችግር ተረድተው ወደቀጣዩ ስራ እንዲሄዱ ማዘጋጀትም ሌላው የህክምና አይነት ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ችግሩን ተረድተው ከሱስ ውስጥ ግን ለመውጣት የሚቸገሩ ከሆነ ሱሱን ተጠቅመው ሲያደርጉ የነበሩ ነገሮችን በሌሎች አማራጮች ቀይረው እንዲጠቀሙ ማገዝና ራሳቸውን ለቀጣይ ህክምና እንዲያዘጋጁ ያሉትን የህይወት አማራጮች አይተው የባለሙያ የቤተሰብ የጓደኛ እገዛ ተጠቅመው ካሉበት ሁኔታ ወጥተው ጤናማ ህይወት መኖር የሚችሉበት ዝግጅት የሚያደርጉበት ሁኔታ ነው።


አቶ ስዩም ዘውዴ

የመጨረሻው ሰዎች ዳግም ወደተውት ነገር እንዳይመለሱ የሚደረግበት ሲሆን እዚህ ላይ ዳግም ወደተውት ነገር መመለስ በምን ምክንያት ይመጣል ሊመጣባቸው የሚችልባቸውን ምክንያቶች ማስረዳት ምናልባት አካባቢያዊ ምክንያቶች የጓደኛ ጫናና ሌሎችም ካሉ እንዲፈቱ የሚደረግበት ነው።

ሆስፒታሉ ከሱስና ሱስ ነክ እንዲሁም በሌሎች ስነ አእምሯዊ ችግሮች ምክንያት አእምሯቸው ላይ ጉዳት ያጋጠማቸውን ሰዎች በማከም ግንባር ቀደሙና ዓመታትን ያስቆጠረ ነው። ራሱን የቻለ የሱስ ማገገሚያ ማዕከልም ያለው ነው። በመሆኑም በማዕከሉ ውስጥ ሳይካትሪስቶች ክሊኒካል ሳይኮሎጂስቶች እንዲሁም የማህበራዊና የነርስ ሙያ ላይ ያሉ በጋራ ሆነው አገልግሎት የሚሰጡበት ተቋም ነው።

የሆስፒታሉን የሱስ ማገገሚያ ልዩ የሚያደርገው ሌላ የስነ አእምሮ ችግር ያላቸው ሰዎች የቆይታ ጊዜ ትንሽ ነው በአማካይም ከአምስት ቀን እስከ አንድ ወር ነው። የሱስ ማገገሚያ ማዕከሉ ላይ ግን በአማካይ 2 ወር ይቆያሉ ይህም ሰዎቹ ሙሉ ለሙሉ ከችግራቸው ወጥተው በራሳቸው የመወሰን አቅማቸው እስኪዳብር ድረስ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ እንደ ባለሙያ ሰዎች በምን መልኩ ነው የአእምሮ ጤናቸውን መጠበቅ ይችላሉ ብለው ይመክራሉ?**

**አቶ ስዩም፡-** ሰዎች በህይወት እስካለን ድረስ በእለት ተዕለት ኑሯቸው በችግር ውስጥ ማለፋችን አይቀርም፤ በመሆኑም ችግሮቹን የምንረዳበት መንገድና ለችግሮቹ አፋጣኝ መፍትሔ መፈለግ የመጀመሪያው ሲሆን ለምሳሌ ሰዎች ጭንቀት ሲፈጠርባቸው ችግሩን እፈታበታለሁ ብለው የሚሄዱበት መንገድ በራሱ ለሌላ የአእምሮ መቃወስ ሊዳርጋቸው ይችላል፤ በመሆኑም እንዲህ አይነት ከበድ ያሉ ጉዳዮች ሲገጥሙን ሊያግዙን ይችላሉ ብለን የምንተማመንባቸውን ሰዎች ማማከር፤ ሌላው ሀይማኖታዊ ቦታዎችን ማዘውተር፤ ጤናማ አስተሳሰብ ካላቸው ሰዎች ጋር መዋል ያስፈልጋል ።

ችግሩ መከሰቱን በራሳችን ላይ ማስተዋል ስንጀምር ደግሞ እርዳታን ለማግኘት መሞከር ከተባባሰ የአእምሮ ጤና ችግር ያድናል በመሆኑም ቶሎ ወደህክምና ተቋም መምጣት ያስፈልጋል።

የስነ አእምሮ ችግር ሰው በመሆናችን ምክንያት የሚከሰት አንዱ የአእምሮ ጤና ቀውስ መሆኑን ሁሉም ሊረዳው ይገባል። ምክንያቱም ስለ ችግሩ ያለን መረዳትና ግንዛቤ ሰዎች ችግሩ እየታየባቸው በጊዜ ህክምናውን እንዳያገኙ ከችግራቸው እንዳይወጡ እንዲባባስባቸውና ጉዳቱም ዘርፈ ብዙ እንዲሆን እያደረገው በመሆኑ ለስነ አእምሮ ህመም የምንሰጠውን ግምትና አስተሳሳብ መቀየር ከሁላችንም የሚጠበቅ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግንሀሁ።**

**አቶ ስዩም፡-** እኔም አመሰግናለሁ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)

gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የአፍሪካ “ከራስ ጋር እርቅ”

### ቀዳሚ የምሥጋና ቃል፤

ከየካቲት 11 እስከ 12 ቀን 2015 ዓ.ም ለሁለት ቀናት ያህል በጋራ አህጉራዊ ጉዳዮች ላይ ሲመክር የሰነበተው የአፍሪካ የመሪዎች ጉባዔ በሰላም ተጠናቆ የደርሶ መልስ አሸኛኘቱም በስኬት መከናወኑ በይፋ ተገልጾልናል። የመሪዎቹ መርሃ ግብር የተከናወነባቸውን ሁለት ቀናት በዋነኛነት ጠቀስን እንጂ “ዝግጅቱና ምጡ” የጀመረው ከዓመት በፊት መሆኑ ጠፍቶን አይደለም።

በተለይም የኅብረቱ ዋና ጽ/ቤት መቀመጫ የሆነችው አዲስ አበባ ከተማችን ለመሪዎቹና ለልዑካን ቡድኖቹ፤ “እንግዳ፡- ፊት ወርቅ፣ ኋላ ብር፣ ኋላ ጨርቅ” ሆኖ እንዳያስገምታት በመጠንቀቅ ለመስተንግዶውና ለደህንነታቸው ጉዳይ እንቅልፍ አጥታ ስትጨነቅ እንደሰነበተች ከማናችንም የሚሰወር አይደለም።

የጉባኤው ዝግጅት እንዲሰምርና በስኬት እንዲጠናቀቅ ለደከሙትና ዋጋ ለከፈሉት ባለድርሻ አካላት፣ ለፀጥታው ክፍል ባልደረቦችና ለሚዲያ ባለሙያዎች በሙሉ በስምሪት ሰጭ ተቋሞቻቸው አማካይነት ብቻ ሳይሆን በእኛ በተራ ዜጎች “ተራ አንደበት” ጭምር እየተጨበጨበ ቢመሰገኑ ለቀጣዩ አገልግሎታቸው ብርታትና ስንቅ እንደሚሆናቸው ስለምናምን እነሆ ምሥጋናችን ይድረሳቸው እንላለን። ኢትዮጵያ ሆይ እንኳን ደስ አለሽ! ለአፍሪካ ኅብረት ጽ/ቤት ዋነኛ ሹሞችና ባልደረቦችም በሙሉ ገለቶማ! ብለን አክብሮታችንን እንገልጽላቸዋለን።

### የጋራ ቤት የጋራ ድምቀት፤

የሚዲያ ሠራዊት ተሰለፍ፣ ፎቶግራፍ አንሺዎች ተደርድረው ከሚከናወነው የመሪዎች ጉባኤ ጎን ለጎን “ለአፍሪካ ትንሣኤ” የሚበጁ እጅግ በርካታ መርሃ ግብሮች ሲከናወኑ ከርመዋል። ለአብነት ያህልም ይህ አምደኛ ከአፍሪካ ሀገራት ከተውጣጡ በርካታ ወንድም እህቶቹ ጋር ለአንድ ሣምንት ያህል በአህጉራዊ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ በቀረቡ ትምህርቶችና ሴሚናሮች አማካይነት እውቀት፣ ጥበብና የየሀገሩን መልካም ተሞክሮዎች ሲቀስም ከርሟል። የእግረ መንገድ አጋጣሚዎች ሲመቻቹለትም ስለ ሀገሩ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ለመመለስና ለማብራራት መሞከሩ አልቀረም።

ይህንን ታላቅ የአፍሪካውያን ጉባዔ በራስ ተነሳሽነት በማዘጋጀት እጅግ ከፍ ያለ ዋጋ የከፈለው ቤዛ ኢንተርናሽናል የተባለ ቤተ እምነት መሆኑን ቀደም ባለው ጽሑፌ ለመግለጽ ሞክሬያለሁ። ይህ አህጉራዊ ፕሮግራም በሀገራችን እንዲካሄድ ራእዩን ጸንሶ ወደ ተግባር እንዲለወጥ ቀዳሚውን ድርሻ የወሰዱት የቤተ እምነቱ መሪዎች ዶ/ር ቤተ መንግሥቱና ልጃቸው መጋቢ ዘሩባቤል መንግስቱ ከፍ ያለ የአክብሮት ምሥጋና ይገባቸዋል።

“አፍሪካ ተነሽ” - “Africa Arise” በሚል መሪ ርዕስ ከአፍሪካ ሀገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችና መሪዎች ጉባዔዎች ጎን ለጎን ፕሮግራሙ መካሄድ ከጀመረ ከአሥር ዓመት በላይ አስቆጥሯል። የፕሮግራሙ አንድ አካል የሆነውና “The African Union Prayer Breakfast” በሚል ዓላማ መሪዎቹ ጉባዔያቸውን በሚጀምሩበት ዕለት የሚከናወነው መርሃ ግብር ሲመራ የቆየው በቀድሞ የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት በክቡር ኦሊሴንጎ ኦባሳንጆ የበላይ ጠባቂነት ነው። የካቲት 11 ቀን 2015 በዚያው በአፍሪካ ኅብረት ጽ/ቤት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ማለዳ ላይ የተከናወነው ይህ መርሃ ግብር የተከፈተውም በእኚሁ ታላቅ አፍሪካዊ አባት መሳጭ ንግግር አማካይነት ነበር።

ፓፓ ኦባሳንጆ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ተከስቶ በመቶ ሺህዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች የሕይወት እልፈት፣ እጅግ ለሚበዙትም መፈናቀልና የንብረት ውድመት ምክንያት የሆነው ጦርነትና ግጭት በሰላማዊ ንግግርና ውይይት እንዲቋጭ አማጺውን የሕወሓት ቡድንና የፌዴራል መንግሥቱን በማቀራረብ የከፈሉት ዋጋም በታሪካችን ውስጥ ሁሌም ሲታወስ የሚኖር ነው።

በማለዳው የጸሎት መርሃ ግብር ላይ ለሰላም ንግግሩ የተሄደበትን እጅግ ፈታኝ መንገድ በማስታወስ ለስኬት ላበቃቸው ለፈጣሪ ተገቢው ምሥጋና እንዲቀርብ ጉባዔተኞችን ጠይቀዋል። እኚሁ ታላቅ የአፍሪካ አባት ለኢትዮጵያ ሰላም መስፈን ስላደረጉት በጎነት እጅግ ከፍ ያለ ምሥጋና የቀረበላቸው ሲሆን ለዕድሜ ልክ ትዝታቸውና ለበጎነታቸው መታሰቢያ እንዲሆንም “በዕድሜዬ ዘመን ሁሉ እንዲህ ዓይነት የከበረ ሽልማት አላገኘሁም” በማለት የመሰከሩለትን ሽልማት ከፕሮግራሙ ባለ ራእዮች እጅ ተቀብለዋል።

ከእርሳቸው በማስከተልም ጉባዔውን በጸሎት የከፈቱት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹእ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ ነበሩ። የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሣህለ ወርቅ ዘውዴ በክብር እንግድነት በተገኙበት በዚህ የማለዳ የጸሎት መርሃ ግብር ላይ የአፍሪካ ኅብረት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችም የተዳሙ ሲሆን የማሳረጊያውን የቡራኬ ጸሎት የመሩት ደግሞ ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ብጹእ ካርዲናል ብርሃነ ኢየሱስ ሱራፌል ነበሩ።

የአፍሪካን ተስፋ የሚያነቃቃ እጅግ መሳጭ ንግግር ያደረጉት ዶ/ር ማሙሻ ፈንታ ሲሆኑ መልእክቱም ጉባዔተኛውን ያነቃቃና በይዘቱም ወቅታዊ ነበር። አፍሪካዊያኑ ወንድም እህቶቻችን ይህን እጅግ የሰመረ “የአፍሪካ ተነሽ!” ጉባኤና የማለዳ መርሃ ግብር ልብ ተቀልብ ሆነው ከተከታተሉ በኋላ በማጠቃለያው መርሃ ግብር ላይ የሰጧቸው ተመሳሳይ አስተያየቶች ሲጨመቁ “ኢትዮጵያ ለአፍሪካ መጻኢ ትንሣኤ በርግጥም ተስፋ መሆኗን አረጋግጠናል” የሚል ነበር። እንደ ምኞታቸው እንዲሁ ይሁንልን።

### ስንፍና የቅርቡን እርቆ የሩቁን ያስመኛል፤

አፍሪካን ለዘመናት የተጫናት አዚም ፈውስና መፍትሔ እንዲያገኝ ብዙ መሠራት እንደሚገባ በየመርሃ ግብሩ ላይ በስፋትና በዝርዝር ተወስቷል። መሪዎቿ በአደባባይ ሲመካከሩ እየዋሉ በየጓዳቸው የጠብ እሳት መጫር የተለመደ ባህርያቸው እስኪመስል ድረስ የአህጉሪቱ እንቆቅልሽ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲወሳሰብ እንጂ ሲቀል አለመስተዋሉም በምሁራኑ አቅርቦት ላይ ተንጸባርቋል።

የእርስ በእርስ ጦርነት በረደ ሲባል ርሃብና ድርቅ መከሰቱ፤ አበረታች የልማት ጅምሮች መስተዋል ሲጀምሩ የአሸባሪዎች እኩይ ጥፋት ገንኖ መውጣቱ፤ አንዱ የችግር ቀዳዳ ሲደፈን በሌላ በኩል ማፈትለኩ፤ በጥናት የተደገፉ ማስረጃዎች እየተጠቀሱ ዋና ዋና የአህጉራችን ችግሮች በሚገባ ተዘርዝረው ቀርበዋል። በበሳል የአህጉሪቱ ምሁራን ሲንቆረቆር የሰነበተው ይህን መሰሉ “የቤት ልጆች የመማማር ጉባዔ” የሚዘነጋ ብቻ ሳይሆን ለተግባር እርምጃም የሚያስጨክን ነበር።

የአፍሪካ ህመሟ ጠንክሮ ፈውሷ ሊርቅ የቻለው ሰበበ ምክንያት እጅግ ብዙና የተወሳሰበ ቢሆንም የአፍሪካ መሪዎችና ምሁራን በአንድነት ተባብረው ለመደጋገፍ ከበረቱና ከጨከኑ ግን አህጉራችን “የዳቦ ቅርጫት፣ የሰላም ርግቦች ጎጆ፣ የእውቀት መፍለቂያ ምንጭ” ሆና ከፍታ እንደምትጨምር ማረጋገጫዎች ተሰጥተዋል።

ከሌሎች ሀገራትና አህጉራት ከመማር ይልቅ በሌሎች ማሳበብ የብዙ አፍሪካዊያን ባህልና ተግባር መሆኑም በድፍረት ተብራርቷል። የአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት ዘመን ያከተመው አፍሪካ ራሷን የራሷ ቅኝ ግዢና ተገዢ እንድትሆን ተደርጎ በተዋቀረ ስትራቴጂ እንደነበርም በብዙ ማሳያዎች ለማመላከት ተሞክሯል።

እርግጥ ነው፡- የምድር በረከት ሳይጎል፣ ከሰማይ ደመና ሳይጠፉ ስለምን አፍሪካ በርሃብ ልትጠቃና ልትታወቅ እንደበቃች ማሰላሰሉ በራሱ ጤና ይነሳል። ጦርነትን ባህሏ አድርጋ፤ መገዳደልን እንደ ጀብድ ቆጥራ፤ በድርቅና በርሃብ እየተፈተነች እስከ መቼ እንደምትዘልቅም አዋቂው አንድዬ ብቻ ነው።

ከሴሚናሮቹና ከንግግሮቹ መካከል የሦስት ያህሉን ተናጋሪዎች መርጠን ለአብነት እናስታውስ። ዲዩዶኔ ናሂመና ‹Dieudonnè Nahimana› በብሩንዲ ሕዝብ ዘንድ እጅግ የተከበሩና አንቱታን ያተረፉ የአፍሪካ ልጅ ናቸው። በጎዳና ወጣቶች ሕይወት ዙሪያ የሚሠራ አንድ ውጤታማ ተቋም በስማቸው በማቋቋም ዓለም አቀፍ እውቅና እስከ ማግኘትም የደረሱ ናቸው።

እኚህ የተከበሩ ሰው “የግል ምስክርነቴ” በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ1993 በቡሩንዲ ውስጥ በተፈጸመው የዘር እልቂት ምክንያት ከአካባቢያቸው ሸሽተው ለጎዳና ሕይወት መዳረጋቸውና አባታቸው፣ በርካታ የቤተሰባቸው አባላትና የማሕበረሰቡ ነዋሪዎች በአሰቃቂ ሁኔታ መጨፍጨፋቸውን ሲተርኩ በእውነቱ የሰብዓዊነት ትርጉም ግራ እስኪያጋባ ድረስ ታዳሚው ያደምጣቸው የነበረው “እኛም እኮ!...” በሚል ቁጭት እምባውን እያፈሰሰ ነበር።

እጅግ የሚያስገርመው ግን የአባታቸውን ደም ጨምሮ የብዙ ዜጎቻቸውን ሕይወት በግፍ ለቀጠፉት አንድ ግለሰብ ቀዬአቸው ደረስ በመሄድ ይቅርታ ማድረጋቸውና ወዳጃቸው እንጂ ጠላታቸው ያለመሆናቸው አቅፈው በመሳም ያሳዩትን ርህራሄ ማድመጥ “በውኑ ዓለም በርግጡ ሊደረግ ይችላል ወይ?” እስከ ማለት አድርሶ ነበር።

ይቅርታ ማድረግ ብቻም ሳይሆን የልጆቻቸውን ሙሉ ኃላፊነት በመውሰድ ጭምር እስከ መጨረሻው አስተምረው ለቁም ነገር ለማብቃት መወሰናቸውንም ያረጋገጡላቸው በፍቅር በተነካ ልብ ነበር። ከተናገሯቸው ኃይለ ቃላት መካከል ጥቂቱን እንጥቀስ፡- “There is no future for Africa without forgiveness and reconciliation... Our Heads of States are sitting together but don’t love each other... We have to take every opportunity to be agents of peace and reconciliation.”

ሁለተኛው ተናጋሪ የግብጽ የልዑካን ቡድን መሪ የሆኑት ዶ/ር ሳሜህ ናቸው። እኚህ ታላቅ ሰው ያስተማሩት ስለ አንድነትና ተቀራርቦ አብሮ ስለመሥራት ነው። እጅግ በሚመሰጥ ንግግር መልእክታቸውን ያስተላለፉት “የዓባይን ውሃ እንደሚጋራ” የሩቅ ሀገር ሰው ሳይሆን እንደ አንድ የቤተሰብ አባል አድርገው ራሳቸውን በመቁጠር ነበር። አብሮ በመደጋገፍ ተራራው ደልደላ ሜዳ፣ ሸለቆው በበረከት ውሃ እንደሚሞላም ተስፋቸውን ገልጸዋል።

ሦስተኛው ተናጋሪ ከደቡብ ሱዳን የመጡት ቢሾፕ ፖል ዴንግ ጀሹዋ ሊክ ነበሩ። በአነቃቂ ንግግሮቻቸው፣ ስለ ሀገራቸው የነፃነት ትግል በዓይን ምስክርነት በሚያጋሩትና በማይሰለቹ የታሪክ ነገራ ችሎታቸው የሚታወቁት እኚህ ሰው “The Spirit of Politics” በሚል ርዕስ የጻፉት መጽሐፍ በአፍሪካ ዙሪያ ተወዶ እየተነበበላቸው ነው።

እኚህ ሰው የተናገሩበት ርዕስ “Breaking the Horns of Limitations” በሚል ርዕስ ሲሆን “አፍሪካን ከላይ ወደ ታች የተጫኗት አራት ቀንዶች ናቸው። እነዚህ አራት ቀንዶች በፍቅር፣ በይቅርታ፣ በሰላምና በምህረት እስካልተሰባበሩና ተሸንፈው እስካልተነቃቀሉ ድረስ አፍሪካ ከህመሟ ልትፈወስ አትችልም”፤ ዋና የንግግራቸው አንኳር ሃሳብ ነበር።

በአራት ተዋጊ ቀንዶች የወከሏቸውና የአፍሪካ ቀዳሚ ችግሮች ያሏቸው፡- “The horns that are raised up in this continent are greed, tribalism, poverty and shame. We need ask ourselves why we struggle with all these failures and poverty in the midst of such fertile ground and good weather; why we are so divided. These horns of limitations have scattered us.” በማለት ነበር።

እናጠቃለው፡- ሥልጡኖቹ የአውሮፓ ሀገራት 27 ሆነው በመሰባሰብ (Supranational Political and Economic Union) በሚል የበላይነት መርህ ከእርስ በእርሳቸው መደጋገፍ አልፈው ዓለምን ለመቆጣጠር እያለሙ ነው። በፓርላማ፣ በካውንስል፣ በኮሚሽን፣ በፍትሕ፣ በመረጃ ደህንነትና ጥበቃ፣ በእምባ አባሽነት ወዘተ. ባዋቀሯቸው በርካታ ተቋማት እየተመሩ ለየሀገራቸውና ለቡድናቸው ከፍታ ሲጨምሩ አፍሪካ ግን ገና ከእንቅልፏ ለመባነን ብርታት ያለማግኘቷ ለመሪዎቿ ብቻ ሳይሆን ለምሁራኗና ለዜጎቿም ጭምር በእኩል ደረጃ አሳሳቢ ተግዳሮቶች ናቸው።

እ.አ.አ በ1945 የተመሠረተው የአረብ ሀገራት ሊግ በ22 አባል ሀገራት ተደራጅቶ ተፈጥሮ በለገሰቻቸው በነዳጅና በከርሰ ምድር ሀብታቸው ሲቀናጡ የእኛይቱ አህጉር ግን “ርሃቧን” እንደ ምክንያት እየጠቀሰች የተጋገረ ዳቦ ትለምናቸዋለች። መጨራረሻዋን የጦር መሣሪያ እንዲያቀርቡላትም ትማጸናቸዋለች፤ ልጆቿንም “በቤት ሠራተኝነት” እየላከች ኑሯቸውን ታዳምቅላቸዋለች።

አሜሪካና ካናዳን ጨምሮ ሌሎች አምስት የአውሮፓ ሀገራትን ያሰባሰበው የG-7 ቡድን ዋነኛ ትኩረት በፖለቲካና በሴኪዩሪቲ ዙሪያ ዓለማችንን ለመቆጣጠር መሆኑ ፖለቲካቸውን ለሚከታተል ለማንም ሰው ግልጽ ነው። G-8 እና G-20 በሚል ስያሜ የሚሰባሰቡት ታላላቅ የአውሮፓና የሰሜን አሜሪካኖቹ ሁለቱ ኃያላን ሀገራት ምን ተልእኮ ለማስፈጸም እንደተቋቋሙ ከማንም የተሰወረ አይደለም። የአፍሪካንና የእስያ አህጉራትን ከርሰ ምድርና ገጸ ምድር በዝብዞና አግዞ የብልጽግናቸውን ከፍታ ለማተለቅ እንደሆነም በግልጽ ይታወቃል።

“ምድራችሁን፣ ጠፈራችሁንና የባሕር ዳርቻዎቻችሁን ‹የጦር ቤዝ› እንድንመሰርት ዝግጁ አድርጉልን” ጥያቄያቸውም ፋታ የሚሰጥ አይደለም። ማስፈራሪያቸው ደግሞ ርዳታና ብድር መሆኑ የታወቀ ነው። “ወንድ ወደሽ፤ ጢም ጠልተሽ” እንዲሉ አፍሪካ በሥልጡኖች ሀገራትና በኅብረታቸው አማካይነት የውጥር ተይዛ ልትቀሰፍ የቻለችው ዓለም አቀፉን የፖለቲካ አዙሪት በኅብረት ለመቋቋም ገና ጉልበቷ ስላልጸና ነው።

የአውሮፓ ሀገራት በቪዛና በንግድ ሥርዓታቸው ተደጋግፈውና ተናበው ሲሰሩ የአህጉራችን መሪዎች ግን ዛሬም ድረስ ስለ “ነፃ የንግድ ቀጣና ምሥረታና ስለ ጋራ የቪዛ አገልግሎት” ተስማምተው መወሰን ተስኗቸው “እባብ ለእባብ ይተያያሉ ካብ ለካብ” እንዲሉ ከእርስ በእርስ መጠራጠር ስሜታቸውን ሊያነጹና ሊያጠሩ አልቻሉም።

“አፍሪካ ተነሺ!” የሚለው ዓመታዊ ጉባዔ ለተዘረዘሩት ዘመን ጠገብ ችግሮች በሙሉ መፍትሔ ያመጣል ባይባልም የምሁራኑ ዓይን ከፋች ትምህርቶች፣ የጋራ ምክክሮቹና፣ ልባዊ የአብሮነት ጸሎቱ ግን ውጤት አምጥቶ የአፍሪካን የራስ ከራስ እርቅና ትንሣኤ ሊያፋጥን እንደሚችል ይታመናል። ሰላም ለሀገራችን፤ ለሕዝባችንም በጎ ፈቃድ።

# ተናጋሪው ዶሴ

## ብሶት ያመጣው መዘዝ

**አስመረት ብስራት**

መቼም የጦርነት ደግ የሰላም ክፉ የለውም ይባላል። ጦርነት ካለ ሰው በሰላም መኖሩ አክትሞ በጭንቀትና በሀዘን እንዲኖር ይፈረድበታል። በጦርነት ከሚመጡት ሰብዓዊ ቀውሶች አንሰቶ ሰው እድሜ ዘመኑን ያፈራውን ሀብት ንብረት እንዲያጣ ይሆናል። ይባስ ብሎ ስደቱ መፈናቀሉ ሲታከልበት ባለ ሙሉ አካሉ ሰው ወደ ተረጂነት ሲቀየር አእምሮው ይዛባል። የሚያደርገው እና የሚያስበው ሁሉ ጥፋት ብቻ ይሆናል። ስለጦርነት ማንሳታችን ለዛሬ ከፍትህ ሚኒስቴር ያገኘነውን በሰሜኑ ጦርነት የተነሳ ከቀየው ተፈናቅሎ ወደ ወንጀል የገባውን ሰው ታሪክ ልንገልፅላችሁ ስለወደድን ነው ። ታሪኩ እንዲህ ነው.....



### ብሶተኛው አዳነ

አቶ አዳነ ሰማው ተወለዶ ያደገው ሰሜን ወሎ አካባቢ ነው። እርሱ የተወለደባት ቆቦ አካባቢ የሚገኝ የገጠር ቀበሌ በምርታማነቷ የታወቀች ምርት በገፍ የሚታፈስባት ነበረች። መሬቱ የሰጡትን ተቀብሎ ያለስስት ጎተራ ሙሉ የሚያሳቅፋቸው የአካባቢው ገበሬዎች በምርት ጊዜ ወለም ዘለምን የማያውቁ ታታሪዎች ነበሩ። ከታታሪዎቹ ገበሬዎች አንዱ የሆነው አቶ አዳነ ጎተራው ማጀቱ ሙሉ ከራሱ አልፎ ለሰው የሚተርፍ የጠገበ ገበሬ ነው።

በሀገሩ ወግ ተድሮ የሙሽራነት ጊዜውን በወጉ ሳያጣጥም የሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ተቀሰቀሰ። ሙሽራይቱን ሚስቱን ሳይጠግብ ለአመት ይሆነኛል ብሎ ጎተራ የሞላውን እህል ሳይሸጥ ሁሉም በጅምር እንዳለ ጦርነቱ ወደ እነሱ ቀበሌ መስፋፋት ጀመረ። ሚስቱን ከእናት ከአባቱ ጋር ቀደም ብለው እንዲወጡ አድርጎ ቤቱ የቀረው ቆፍጣና ገበሬ እጅግ በጣም ያዝን ጀመር።

ከልጅነቱ ጀምሮ ቦርቆ ያደገባት ውቧ ቀዬው ሰው አልባ ሆና፤ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ በአካባቢው ያሉ የቤት እንስሳትን ሲሰበስቡ ብሎም ሀገራቸውን ከጥፋት ሲጠብቁ ሰነበቱ። ይባስ ብሎ የመንግስት ጦርም ሆነ የሌለኛው ወገን ጦር በቅርብ ርቀት መመሸጋቸውን ሰማ። ያኔ ከመሞት መሰንበት ብሎ ቤቱን መለስ አድርጎ በመውጣት ወደ ዋና መዲናይቱ አዲስ አበባ ገባ። የስልክ አገልግሎት ስላልነበረ ቤተሰቦቹም የት እንደደረሱ ማወቅ አልቻለም። እንደ ምንም አዲስ አበባ የገባው ገበሬ በያዛት ሳንቲም ቤት ተከራይቶ የአቅሙን ስራ ለመስራት ቢሞክርም ሊሆንለት አልቻለም።

ከተማዋ ከአቅሟ በላይ ስራ አጥ ሰዎችን በመሸከሟ ለአዲስ መጤዎቹ ጭርሱኑ ቦታ አልነበራትም። ትናንት ተንደላቆ ይኖር የነበረው፤ ከራሱ አልፎ ለሰዎች የሚተርፈው፤ ከእጁ አጥቶ ነጥቶ የማያውቀው ገበሬ እጅጉን ተከፋ፤ ንዴቱ አቅሉን አስቶት ከሳሩም ከቅጠሉም ጋር መጣላት ጀመረ።

### የሰላም ሰፈሩ ሰላም አደፍራሽ

ይሳቅ ያዕቆብ እና መልካሙ በንቲ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ልዩ ቦታው ሰላም ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪዎች ናቸው። ጥብቅ ጓደኛሞች ነበሩ። ከስራ መልስ ተጠራረተው ሻይ ቡና ማለትን ለምደዋል። ሰዎቹ ጨዋታ የማያልቅባቸው ሁሌ ፊታቸው በፈገግታ ተሞልቱ የሚታዩ ደስተኞች ነበሩ።

ይሳቅን ያለ መልካሙ መልካሙን ያለ ይሳቅ ሰፈር ውስጥ መመልከት ያልተለመደ ነበር። አይለያዩም ሁልጊዜ አብረው ናቸው። ወዳጅነታቸው የሚያስቀናው እነዚህ ጓደኛሞች አንዳንድ ጊዜ የእግር ጉዞ በማድረግ መንገድ ላይ ቆም እያሉ ያወሩ ነበር። አንዳንዴ ደግሞ መጠጥ ቤት ውስጥ እየተጎነጩም ያመሻሹ ነበር። ብቻ ምንም ይሁን ምን ሳይገናኙ ማደር እስከማየችሉ ድረስ በየእለቱ አብረው ይውላሉ፤ ያመሻሉ።

አንድ ቀን እንደልማዳቸው ከሰፈራቸው ወጣ ያለ አካባቢ ድረስ በእግራቸው ሄደው እየተመለሱ ነበር። ወሬያቸው ሞቅ ሲለ መንገድ ላይ ቆም እያሉ አውርተው ጉዟቸውን ይቀጥላሉ። አሁንም ቆም ደግሞ ሄድ እያሉ የሚያወሩት ጓደኛሞች ትኩረታቸው በሙሉ ጨዋታቸው ላይ ስለነበር ሌላውን ነገር እያስተዋሉ አልነበረም።

ጨዋታቸው ሞቅ ስላለ የሰዓቱንም መሄድ ልብ አላሉም ነበር። በዝግታ እየተጓዙ ሞቅ ባለ አንደበት ያወራሉ። ያኔ ከየት መጣ ያላሉቱን የቁጣ ድምፅ ይሰማሉ። ቀና ብለው ሲያዩ የሁለቱም ቤት አቅራቢያ ደርሰዋል። ያለምንም ስጋት " አቤት...." አሉ። "ተንቀሳቀስ መንገድ ዘግተህ መቆም አትችልም...." የሚል የቁጣ ድምፅ ከወደ ጨለማው አቅጣጫ መጣ።

### የሞቀውን ጨዋታ ወደ ስቅሶ የቀየረው ገጠመኝ

ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም ነበር። ቀዝቀዝ ያለው የጥቅምት ንፋስ ፊትን በለሆሳስ እየገረፈ ያልፋል። ንፋሱ ቀዝቀዝ ቢልም ብርዱ ግን አጥንት ሰንጣቂ አይነት ነበር። ቀደም ብለው ጃኬቶቻቸውን ደራርበው፤ እጃቸውን ጃኬታቸው ኪስ ከተው ለሀገር ጉዞ የወጡት ጓደኛሞች ሞቅ ባለ ጨዋታቸው ብርዱን ረስተው የእግር ጉዞ ያደርጋሉ። ከምሽቱ 2፡30 አካባቢ ሲሆን ከሄዱበት እየተመለሱ በለሚኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ክልል ልዩ ቦታው ሰላም ሰፈር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ደርሰዋል። ወሬያቸውን ስላልጨረሱ ቆም ብለው ጨዋታቸውን ቀጥለዋል።

ድንገት ‹‹ተበተኑ እናንተ መንገድ ዘግታቹህ ትቆማላቹሁ፤ እዚያ ሰው እያለቀ ነው። እኛም የመጣነው ጠላት ከመኖሪያ ቄያችን አባሮን ነው።›› የሚል ድምፅ ይሰማሉ። ድምፁ ወደመጣበት አቅጣጫ ፊታቸውን ሲያዞሩ አንድ በንዴት የተሞላ ሰው ሽጉጥ ደግኖ ወደ እነሱ አቅጣጫ ሲመጣ ተመለከቱ።

ሰውየው አለባበሱ የባላገር ሰው ይመስላል። "ከሌላ ሰው ጋር ተመሳስለንበት ይሆን?" ከሚል ጥርጣሬ ባለፈ አደጋ ያደረስብናል የሚል ግምት አልነበራቸውም። ሁለቱም ሰውየው እንዲረጋጋ ለማድረግ ቢሞክሩም ሰውየው ንግግራቸው እያናደደው ጭራሽ መጮህና መሳደብ ጀመረ። ነገሩ ያላማራቸው ጓደኛሞች ከቦታው ለመሄድ ፊታቸውን ሲያዞሩ ይዞት በነበረው ሽጉጥ ሁለቱንም አንድ አንድ ጊዜ ተኩሶ አንደኛውን ጀርባው ላይ ሌላኛውን ደግሞ የግራ ትክሻው ላይ በመምታት ይጥላቸዋል። በደረሰባቸው ምት የተነሳ ከሁለቱም ከፍተኛ ደም መፍሰስ ይጀምራል።

በሰላም ስራ ውለው ልማዳቸውን አደርሰው፤ በሰላም ወደ ቤታቸው ሊገቡ የነበሩት ጓደኛሞች ባልታሰበው ዱብዳ ቆሰሉ። የተኩስ ድምፅ የሰሙት የአካባቢው ነዋሪዎችና የፀጥታ ኃይሎች በአካባቢው ሲደርሱ ሁለቱ ታጣቂዎች መሬት ወድቀው አጥቂው ደግሞ ዙሪያቸውን እየዞረ ዘራፍ ሲል ይደርሳሉ። ማህበረሰቡ ተባብሮ ወንጀለኛውን በቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ ተጎጂዎቹን ወደ ሆስፒታል አደረሷቸው።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ካዋለ በኋላ፤ ምርመራውን ጀመረ። የግል ተበዳዮች በጊዜ ሆስፒታል በመድረሳቸው ብዙ ደም ቢፈሳቸውም ሕይወታቸው አልጠፋም። ከህመማቸው እንዳገገሙም ፖሊስ ቃላቸውን ሊቀበላቸው ወደ ሆስፒታል ጎራ አለ።

የግል ተበዳዮችም ያልታሰበውን ገጠመኝ ለፖሊስ አብራርተው ካስረዱ በኋላ ፖሊስ የወንጀል ፈፃሚው ለዚህ ጥፋት መገፋፋት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል? በማለት የተለያዩ ምርመራዎችን ሲያደረግ ቆየ። ከዛም ወንጀለኛው ቤት ንብረቱን በማጣቱ የተነሳ ከደረሰበት ብሶት የተነሳ በሰዎች ሁሉ ላይ ያሳደረው ጥላቻ መሆኑን ለመረዳት ተቻለ።

ምንም እንኳን በመከፋት ውስጥ ቢቆይም ሰውን ማጥፋት ወንጀል በመሆኑና፤ ፍቃድ የሌለው መሳሪያ ይዞ በመገኘቱ ፖሊስ ለዐቃቤ ህግ ክስ እንዲመሰረትበት ማስረጃዎቹን አጠናቅሮ አቀረበ።

### የፍርድ ቤት ክርክር

በፍትህ ሚኒስቴር በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ዘርፍ ቦሌ ምድብ ጽ/ቤት የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 27/1/ እና 540 ስር የተመለከተውን በመተላለፉ ተከሳሽ ላይ ክስ ተመሰረተ።

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ 4ኛ ወንጀል ችሎት ክርክሩን መርቶ የቅጣት ውሳኔውን አስተላለፈ። ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ 2፡30 ሰዓት ሲሆን፤ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ክልል ልዩ ቦታው ሰላም ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የግል ተበዳይ ይሳቅ ያዕቆብ እና መልካሙ በንቲ የተባሉትን ግለሰቦች ‹‹ተበተኑ እናንተ መንገድ ዘግታቹህ ትቆማላቹሁ፤ እዚያ ሰው እያለቀ ነው። እኛም የመጣነው ጠላት ከመኖሪያ ቄያችን አባሮን ነው።›› በማለት ይዞት በነበረው ሽጉጥ ሁለቱንም የግል ተበዳዮች አንድ አንድ ጊዜ ተኩሶ አንደኛውን ጀርባው ላይ ሌላኛውን ደግሞ የግራ ትከሻው ላይ በመምታት በሁለቱም ተበዳዮች ላይ ከፍተኛ ደም መፍሰስ እንዲያገጥማቸው ያደረገ በመሆኑ በፈፀመው ተራ የሰው ግድያ ሙከራ ወንጀል ተከሰሰ።

ተከሳሽ በችሎት ቀርቦ ክሱ ደርሶትና ተነቦለት የእምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ "እኔ ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛም አይደለሁም " ሲል ቃሉን ሰጥቷል።

ዐቃቤ ህግ በበኩሉ የተከሳሽን ጥፋተኝነት ለፍርድ ቤቱ ያስረዱልኛል ያላቸውን ዝርዝር ሶስት የምስክሮች ቃል፣ የሰነድ፣ ኤግዚቢት እና ገላጭ ማስረጃዎችን በማቅረብ በበቂ ሁኔታ ለችሎቱ በማስረዳቱ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን እንዲከላከል ብይን ቢሰጥም፤ የዐቃቤ ህግን ክስ እና ማስረጃ ማስተባበል ባለመቻሉ የግራ ቀኙን ክርክር ያዳመጠው ፍርድ ቤት ዐቃቤ በበቂ ሁኔታ ተከሳሽ ወንጀሉን መፈጸሙን ያረጋገጠ በመሆኑ የጥፋተኝነት ፍርድ አስተላልፏል።

### ውሳኔ

በክርክሩ መሰረት ተከሳሽ ከዚህ በፊት የጥፋተኝነት ሪከርድ የሌለበት፤ ወንጀሉ በሙከራ ደረጃ የቀረ በመሆኑ የቅጣት ማቅለያዎች ተይዘውለት በ10 ዓመት ፅኑ እስራት ተቀጣ። ነገር ግን ውሳኔው ወንጀለኛው ዋስትና ተፈቀዶለት በሌለበት የተሰጠ ውሳኔ ነበር፡፡

የግድያ ወንጀልን በተመለከተ በጊዜ ቀጠሮም ሆነ በመደበኛ ክስ መዝገብ ማንኛውም ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ክስ እንደሚቀርብበት ወይም በተከሰሰበት ክስ ጥፋተኛ እንደሚባል አውቆ መሰወሩ መደበኛ ክርክር ማድረግን የማይከለክል ሲሆን፤ መብቱን ጠብቆ አለመከራከር መብት ከማሳጣቱም በላይ ዘወትር የፍርሃት እና የስጋት ኑሮን እንዲመሩ ያደርጋል፡፡ ከፍትህ በድብብቆሽ እንደማይኖር አውቆ ወንጀለኛው እጁን እንዲሰጥ ጥሪ ቀርቦለታል።

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የትምህርት ተቋማት የመረጃ ቋት ጉዳይ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

በአገራችን የነፃ ገበያ ሲመጣ፤ ከአጸደ ህፃናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ድረስ የግል ትምህርት ተቋማት በየቦታው መስፋፋታቸው ማንም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። በአዲስ አበባ ለግለሰብ መኖሪያ ቤትነት የተዘጋጁ በብዛት አፀደ ህፃናት ሲሆኑ አይተናል።

ፈረንጆቹ ‹kindergarten› የሚሉት አፀደ ህፃናት ትምህርት ቤቶች በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች በመከፈታቸው ለብዙ ሰዎች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል። ወላጆችም ለልጆቻቸው የተሻለ ትምህርት ቤት በመሻት እነዚህን ትምህርት ቤቶች ምርጫቸው ሲያደርጉ ይስተዋላል። ሆኖም የግል ትምህርት ቤቶች ሁሉ ግን የተሻለ፣ ተመራጭ እና ተወዳጅ ናቸው ማለት አይቻልም።

አንዳንዶቹ የግል ትምህርት ቤቶች ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች እጅግ በጣም የተጋነነ ክፍያ ያስከፍላሉ፤ ወላጆች ለልጆቻቸው የላቀ ስለከፈሉ የሞቀ የደመቀ ትምህርት ቤት ሁሉ ያስገቡ ይመስላቸዋል። አንዳንዶቹ ህፃናት የተወሰነ እንግሊዝኛ ሰባብረው ሲናገሩ በግንዛቤ ማነስ ወላጆች ልጄን ጥሩ ትምህርት ቤት አስገባሁት ብለው ይረካሉ፣ ይኮራሉ።

ከመዋዕለ ህፃናት መካከል በትምህርት ቢሮ የሚታተሙ መፃሕፍትን ወደ ጎን ትተው የራሳቸውን መፃህፍት አሳትመው ለህፃናቱ የሚማሩበት በሚል ለወላጆች በግዴታ የሚሸጡ አሉ። ይህም የትምህርት ቢሮዎች ክትትል ማነስ ውጤት ነው። ሌላው በሰበብ አስባብ የትምህርት ክፍያ የሚጨምሩ ይገኙበታል፤ በአንድ ወቅት የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የግል ትምህርት ቤቶች በመጪው አዲስ ዓመት ምንም ዓይነት የትምህርት ክፍያ መጨመር እንደማይችሉ ማሳሰባቸውም በኑሮ ውድነት ለሚንገላቱት ወላጆች አንድ ፋታ እና እፎይታ ነው።

መምህራኑ ምን ያህል ብቃት አላቸው የሚለውም ያጠያይቃል። አንዳንዶቹ ተማሪዎቹን ለማስተማር ሳይሆን ለማጫወትም ብቃት ያላቸው አይመስሉም፤ ለህፃናቱ የሚጠይቁት ጥያቄ አንዳንዴ አዋቂዎችንም ግራ ያጋባል። ስለልጅዎ ትምህርት በትምህርት መጽሐፉ ላይ ጽፈው አስተያየት ሲሰጡ እንግሊዝኛውን ሰዋሰዋዊ ሥርዓት የማያውቁ አይቻለሁ። ለወንድ ህፃን (she was a good student) ጥሩ ተማሪ ነበረች፤ ብለው ለወላጅ አስተያየት ሲጽፉ አያስገርምም? አስተማሪው ራሱ ስለሚያስተምርበት ቋንቋ ሳያውቅ ሲያስተምር ተማሪውን ከማደናገር እና ከማደናቆር በቀር ፋይዳ የለውም።

በተለይም በአዲስ አበባ የሚያስተምሩበት ግቢ በብዛት ለሰው መኖሪያ ቤት የተዘጋጀ እና ለአፀደ ህፃናት ታስቦ የተሠራ ስላልሆነ ህፃናቱ እንደልብ የሚጫወቱበት ሠፋ ያለ ቦታ የላቸውም። ከመቶ በላይ ተማሪ በጠባብ ግቢ ሰብስቦ ማስተማር ህፃናቱን ማጨናነቅ ነው። ህፃናት ማስተማር የሚቻለው በጨዋታ፣ በውዝዋዜ፣ በዘፈን፣ በተረት፣ በስዕል በመሳሰሉት ነው። ዕድሜያቸው ለትምህርት ያልደረሱ ሕፃናት በአጸደ ህፃናት የሚማሩት ለዋናው ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው። ለዚህ ደግሞ እንደ ልብ የሚቦርቁበት ሠፋ ያለ ግቢና መጫወቻዎች ለህፃናቱ ማስፈለጉ ግድ ነው። ጨዋታና ብላቴና አይነጣጠሉምና።

ወደ ግል ኮሌጆች ስንመጣም አንዳንድ እንከኖች ሊኖሩባቸው እንደሚችሉ ማሰቡ ጥሩ ነው። ትምህርታቸውን በለብለብ መልኩ የሚሰጡ ብዙ ኮሌጆች አሉ። አንዳንዶቹ በዲግሪ ተመርቀው ስማቸውን እንኳ በቅጡ መፃፍ አይችሉም። ይህ ለነገሩ የመንግሥት ኮሌጆችንና ዩኒቨርሲቲዎችንም ይመለከታል። ከተወሰኑ ዓመታት በፊት የታጠፈው የከፍተኛ ትምህርት ጉዳዮች ሚኒስቴር ዓላማው በዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች ላይ ክትትል ቁጥጥር ማድረግ ነበር። በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያደረገው ቁጥጥርና ክትትል ብዙም ሳይሰማ ነው የታጠፈው። በትምህርት ሚኒስቴር ሥር የተቋቋመው የኢፌዴሪ ትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ጉዳዮች ነቃ ያለ ክትትል ቁጥጥር እያደረገ ይገኛል።

ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የተጀመረውም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ነው። በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣኑ በአራት ዙር ባደረገው ድንገተኛ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፍተሻ 332 ካምፓሶችና ቅርንጫፎች ላይ እርምጃ ወስዷል።

ባለሥልጣኑ ባጠቃላይ በ2014 ዓ.ም በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ባደረገው ድንገተኛ ፍተሻ በአንደኛው ዙር በአዲስ አበባ እና በክልል ከተሞች 106፣ በ2ኛው ዙር 95፣ በ3ኛው ዙር 104 እና በ4ኛው ዙር 27 ካምፓሶችና ቅርንጫፎች ላይ እርምጃ ወስዷል። እርምጃ ከተወሰደባቸው መካከል፤ ግብአቶች ያጓደሉ፣ የዕውቅና ፈቃድ ሳያሳድሱ ተማሪ የመዘገቡ፣ የዕውቅና ፈቃድ ባልተሰጠበት የርቀት ቅርንጫፍ ማዕከል ከፍተው ተማሪዎች መዝግበው ያስተማሩ፣ ያለባለሥልጣኑ ዕውቅና የህንፃ ለውጥ ያደረጉ ያልተሰጣቸውን የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ደረጃ ስያሜ የተጠቀሙ ይገኙበታል።

ሌላው የግል ኮሌጅ ተማሪ የዲግሪ ዲፕሎማ ትምህርት ማስረጃው ቢጠፋ እና በአጋጣሚ የተማረበት ኮሌጅ ቢዘጋ ችግሮች መፈጠራቸው የማይቀር መሆኑ ነው። የትምህርት ማስረጃውን ቢጠፋ ከየት ያገኘዋል? በእኔ ግምት ተምሮ እንዳልተማረ የሚሆንበት ዕድሉ ሠፊ ነው።

ያም ሆነ ይህ ትምህርት ሚኒስቴር በዜጎች ትምህርት ውጤትና ምረቃ ማስረጃ ላይ ተመርኩዞ የመረጃ ቋት ማዘጋጀት አለበት። የግልና የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስለተማሪዎቻቸው ትምህርትና ውጤት ምረቃን ሁሉ በየጊዜው ማስረጃ ነክ ዝርዝር ጉዳዮችን ለትምህርት ሚኒስቴር እንዲልኩ መደረግ ያለበት ይመስለኛል። ትምህርት ሚኒስቴርም፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ተማሪዎች፣ ትምህርት፣ ውጤትና ምረቃን ሁሉ በየዓመቱ መሰነድን ሊመለከተው ይገባል። የተማሪዎችንም ሆነ የትምህርት ቤቶችን ማስረጃዎችን ሁሉ ለመያዝ ደግሞ ዘመኑ የፈጠረው በይነ መረብ ለዚህ የተመቸ ነው። የኮሌጆችና የዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም የተማሪዎቻቸውን ሁኔታ የትምህርት ውጤቶቻቸውንና ነጥቦቻቸውን በመረጃ ቋት ሥርዓት ሰብስቦ የሚይዝ ቡድን መፍጠር አለበት።

በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተከሰቱ የፀጥታ ችግሮች በዩኒቨርሲቲዎች ይማሩ የነበሩ ትምህርታቸውን ትተው ሸሽተው መጥተዋል። በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን ቀጥለዋል። ሆኖም ትምህርታቸውን ካቋረጡበት ቀጠሉ፤ ሊመረቁ ሲሉ ግን ዩኒቨርሲቲዎቹ የተማራችሁበትን የትምህርት ማስረጃ እንስጣለን እንጂ አናስመርቅም አሉ። ተማሪዎቹም ቅሬታቸውን አሰምተዋል። ችግሩ ሊከሰት የቻለው በአገሪቱ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎችና ተማሪዎች ዙሪያ በየጊዜው በድረግብር (network) የሚጠናከር የመረጃ ቋት ሥርዓት ባለመኖሩ ነው።

የግልና የመንግሥት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ከመጀመሪያው ዓመት ጀምሮ እስኪያጠናቅቁ ድረስ የትምህርት መረጃዎቻቸው የትምህርቱ ዓይነቱና ውጤቱ ሁሉ በአንድ የመረጃ ቋት ቢሰበሰብ፤ ተማሪዎች የትምህርት ማስረጃዎቻቸው ቢጠፉ በቀላሉ መረጃውን ሊያገኙ ይችላሉ። የግድ የተማሩበት ዩኒቨርሲቲ ድረስ የማይሄዱበትሥርዓት ይኖራል። ሳይማሩ ተምረናል የሚሉ አይኖሩም። ቢተገበር እና ቢጀመር ተማሪዎችና ተመራቂዎች መረጃ ፍለጋ እንዳይንከራተቱ ይረዳል።

# ዓለም አቀፍ



## ዩክሬን ለጦርነቱ መታሰቢያ አዲስ የገንዘብ ኖት ይፋ አደረገች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዩክሬን ማዕከላዊ ባንክ አንድ ዓመት የሆነውንና ዩክሬን "የሩሲያ ወረራ" እያለች የምትጠራውን ጦርነት መታሰቢያ የሚሆን የብር ኖት ይፋ አድርጓል፡፡

ይፋ በተደረገው የገንዘብ ኖት በአንዱ ገጽ ላይ በጦርነቱ የተፈጸሙ ወንጀሎች የሚገልጹ ሁለት የታሰሩ እጆች እንዲሁም በሌላኛው ሶስት ወታደሮች የአገሪቱ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ሲያወለበልቡ የሚያሳይ ምስል ያለበት ነው፡፡

የዩክሬን ብሔራዊ ባንክ ገዥ አንድሪይ ፒሽኒ "የጦርነቱን አንደኛ ዓመት ለማክበር በትንሽ ወረቀት ላይ የአንድ አመት ስሜትን፣ ስርዓትን፣ ይዘትን እና ምስላዊ ነገሮችን የሚያሳይ የመታሰቢያ የገንዘብ ኖት ይፋ ለማድረግ ወሰንን" ሲሉ ተናግረዋል።

"በዚህ ዓመት ውስጥ ዩክሬናውያን ያላቸውን ኃይል፣ አስፈላጊነታቸው፣ የተቃጣባቸውን አደጋ መቋቋም ብቻ ሳይሆን ለተፈጸመው ወንጀል ይቅር ሳይሉ ምላሽ በመስጠት ማሸነፍ እንደሚችሉ ተገንዝበዋል" ያሉት የዩክሬን ብሔራዊ ባንክ ገዥ አንድሪይ ፒሽኒ፤ ድሉ ለዩክሬናውያን ትልቅ ዋጋ ያለው መሆኑም ገልጸዋል፡፡

ኖቱን ለማዘጋጀት ስምንት ወራት ያህል እንደፈጀም ነው ሮይተርስ የዘገበው ሲሆን የባንኩ ኃላፊዎች ጦርነቱን የሚያሳዩ ምስሎች ያሉባቸው ተከታታይ የዩክሬን የብር ኖቶች (ሂሪቪንያ) የማዘጋጀት እቅድ እንዳላቸውም አስታውቀዋል፡፡

በጦርነቱ የተገኙ ድሎችን የሚያስታወሱና እና የዩክሬንን መልሶ ግንባታ የሚያመላክቱ አዳዲስ የብር ኖቶች ከወዲሁ ማዘጋጀት መጀመራቸውንም ነው የገለጹት ኃላፊዎቹ፡፡

የዩክሬን ማዕከላዊ ባንክ ባለፈው ዓመት የካቲት 24 ቀን ሩሲያ በአገሪቱ መጠነ ሰፊ ወታደራዊ ዘመቻ መጀመሯን ተከትሎ ኢኮኖሚውን ለማቆየት እና መረጋጋትን ለመፍጠር ሲታትር የቆየ ተቋም መሆኑ ይነገራል፡

የባንኩ ጥረት በምዕራባውያን አጋሮች ከሚደረገው የቢሊዮን ዶላር ድጋፍ ጋር ተዳምሮ አሁን ላይ የዩክሬን የምንዛሪ ክምችት ወደ 30 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ሲሆን ይህም ጦርነቱ ከተጀመረበት ጊዜ ትንሽ ከፍ ያለ ነው ተብሏል፡፡

## ትውልደ ሕንዳዊ-አሜሪካዊው ዓለም ባንክን ለመምራት በእጩነት ቀረቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ሕንዳዊ አሜሪካዊው የንግድ ሥራ አስፈጻሚ አጃይ ባንጋስ የዓለም ባንክን እንዲመሩ እጩ አድርገው አቀረቡ።

ይህ ዜና የተሰማው ዓለም ባንክ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል የሚሰጠውን ትኩረት እንዲጨምር አሜሪካ የምታሳድረውን ጫና በጨመረችበት ወቅት ሲሆን ባንጋስ 'ማስተርካርድ' የተባለውን ግዙፉን የፋይናንስ ተቋም ከ10 ዓመት በላይ የመሩና አሁን ላይ በግል ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ናቸው፡፡

የአሜሪካ ባለስልጣናት ባንጋስ በግሉ ዘርፍ ያካበቱት ልምድ የዓለም ባንክን ግቦች ለማሳካት ይረዳል ሲሉ የተናገሩ ሲሆን የዓለም ባንክን ቀጣይ መሪ የመሾም ኃላፊነት የባንኩ ቦርድ ነው ተብሏል።

የዓለም ባንክ ለሶስት እጩዎች ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ማቀዱን ገልጾ፤ በቀጣዩ ሰኔ አዲስ ኃላፊ እንደሚሾም ይፋ አድርጎ ነበር፡፡ የዓለም ባንክ ሴት አመልካቾች ይበረታታሉም ብሎም ነበር።

እንደ አሜሪካ ሁሉ ሌሎች አገራት ጥቆማ ስለማቅረባቸው የተባለ ነገር ግን አለመኖሩንና ለአገራት በቢሊዮን ዶላሮች የሚቆጠር ገንዘብ የሚያበድረውና አሜሪካ ትልቁን ድርሻ የምታበረክትበት የዓለም ባንክ በተለምዶ መሪው የሚመረጠው በአሜሪካ መሆኑ ተናግሯል።

የአሜሪካ ግምጃ ቤት ኃላፊ ጄንት ያለን የዓለም ባንክ ትክክለኛውን አጀንዳ ትኩረት እንዲያደርግ ፍላጎታቸው መሆኑን ተናግረው፤ አሁን በአሜሪካ በኩል በእጩነተ የቀረቡት አጃይ ባንጋስ፤ በተለየ ሁኔታ ለውጥ ላይ የተካኑ ናቸው ያሉ ሲሆን በመንግሥት፤ በኩባንያዎችና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችን በማስተሳሰር የተዋጣላቸው ናቸው ብለዋል።

የአሜሪካ ዜግነት ያላቸው ባንጋስ ስራቸውን የጀመሩት በተወለዱበትና አባታቸው ወታደራዊ መኮንን በነበሩበት ሕንድ ሲሆን በግሉ ዘርፍ ያለውን ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ያለመና ከኋይት ሃውስ ጋር የሚሰራ መርሃግብር ላይ ተባባሪ ሊቀመንበር ናቸው።

ባንጋስ የሚመረጡ ከሆነ አሁን በስራ ላይ ያሉትን በቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የታጩትን እና በሚቀጥለው ሰኔ ከኃላፊነት እለቃለሁ ያሉት ዴቪድ ማልፓስ ይተካሉ ተብሏል።

# የቄስ ትምህርት እና የአሸር ቤት

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

በአገሪቱ ዘመናዊ ትምህርት በ19ኛው መቶ ዘመን በነገሡት በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን በአሁን ዘመን ዳግማዊ ምኒልክ ተብሎ የሚጠራውና ዘመናት የተሻገረው ተቋም መቋቋሙ ይወሳል። እንደ ፕሮፌሰር ጆን ማርካኪስ አገላለጽ «... ምኒልክ ዘመናዊ ትምህርት ቤትን በመክፈት በኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊ የትምህርት ዘር የዘሩ ናቸው። ... ትምህርት ቤቱም የተሠራው ንጉሡ ነገሥቱ በሰጡት የግል ገንዘብ ነው። ...»። በፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ የዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ድርሳን አገላለጽም፣ የመደበኛ ትምህርት በኢትዮጵያ ለመስፋፋት እንደ አንድ ዐቢይ ክስተት የሚቆጠረው ድርጊት በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን የተከናወነው በንጉሡ ነገሥቱ ስም የሚታወቀው ትምህርት ቤት በ1900 ዓ.ም. መከፈቱ ነው። «የዘመናዊ ትምህርት» ፍላጎት እያደገ መምጣት የጀመረው በ19ኛው መቶ ዓመት መሆኑን ከዓድዋ ድል በኋላ ኢትዮጵያ ከአውሮፓና ከአውሮፓውያን ጋር ያላት ግንኙነት እየተጠናከረ ሲሄድ ዘመናዊ ትምህርት ለማስፋፋት አመቺ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን የታሪኩ ድርሳን ያመለክታል።

ይሁን እንጂ ነባሩ የኢትዮጵያ ትምህርት ሥርዓት የሚጀምረው ግን በዘመነ አክሱም ከአራተኛው መቶ ዘመን ጀምሮ መሆኑም ይገለጻል። የተለያዩ ጸሐፍትና የሥነ ትምህርት ምሁራን ነባሩን የትምህርት ሥርዓት ባህላዊ የትምህርት ሥርዓት፣ የቤተክህነት ትምህርት ቢሉትም ደስታ በርሀ ስብሐቱ በአንድ ጥናታቸው እንዳመለከቱት፣ ነባሩ የትምህርት ሥርዓት «የኢትዮጵያ ትምህርት ሥርዓት» መባል አለበት ይላሉ።» ለዚህም ማገናዘቢያቸው እስከ 20ኛው መቶ ዓመት መባቻ ድረስ የኢትዮጵያ ትምህርት በተማከለ ወይም ባልተማከለ መልኩ በተለያዩ አካላትና ተቋማት አስተዳደርና ሥር መከናወኑ ነው፡

ዘመናዊ ትምህርት በሀገራችን ከመጀመሩ በፊት ታዳጊዎችን የሚያስተምሩት የሃይማኖት ትምህርት ቤቶች ነበሩ። በእስልምና አሸር ቤት፣ በክርስትና ቄስ ትምህርት ቤት በሚባል ይጠራሉ። ተማሪዎቹም በቅደም ተከተል ደረሳዎችና የቆሎ ተማሪዎች ይባላሉ። የጠቀስናቸው የሃይማኖት ትምህርት ቤቶች ታዳጊዎችን እያስተማሩ ለወግ ለማዕረግ ያበቁ ነበር።

ትምህርቱ ሃይማኖት ተኮር ቢሆንም በግብረ ገብ የታነፀ በስነ ምግባር የበለፀገ ትውልድ የሚፈራባቸው ነበሩ። አሁን አሁን ደብዛቸው እየጠፋ ቢመጣና በአጸደ ሕፃናት ቢዋጥም፤ በከተሞች የቄስ ትምህርት ቤቶችም በብዛት ነበሩ። በዚህም ከፊደል ቆጠራ ጀምረው እስከ ንባብ ድረስ ይማሩ ነበር። ትምህርት ቤቶቹም በአዲስ አበባ እንኳ እንደነገሩ የነበሩ ናቸው። የተወሰነ ፀሀይ መከላከያ ያለው መኖሪያ ቤት ተዘጋጅቶ ልጆች ተሰብስበው ይማሩበታል። እኔ ስማር የተወሰኑ መቀመጫዎች የአጠና እንጨት ተረብርቦ የተሰራባቸው ጎናቸው ረጃጅም ቁመታቸው አጫጭር አግዳሚዎች ከፊሉ ደግሞ ጠፍጣፋ የሚመስሉ ድንጋይ ወደ ጎን ተደርድረው እንቀመጥባቸው እንደነበር አስታውሳለሁ።

የኔታ (ቄሱ) ድርሻቸው ትልቆቹን ማስተማር ነበር። ጀማሪዎችን ደግሞ እንደደረጃቸው የተወሰነ ፊደል የሚያውቁ ተማሪዎች ያስጠናሉ። የሚያስጠኑትን ደግሞ ሌሎች ከፍ ያለ ደረጃ የደረሱ በተራቸው ያስጠናሉ። ፊደሎቹን መገንዘብ ሲጀምሩ በየኔታ ጥያቄ ይቀርብላቸዋል። ካወቁ ወደ ቀጣይ ከሀሁ ወደ አቡጊዳ፤ መልዕክተ፤ ወንጌል ወዘተ እያሉ ይሄዳሉ። ካላወቁ በአለንጋ ተገርፈው በደንብ እንዲያጠኑ ይደረጋል። እንዲህ እያለ እስከ ዳዊት ማንበብ የሚዘልቅ አለ። በከተሞች ቄስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እረፍት ሲወጡ መጫወቻው የትምህርት ቤቱ ሠፈር ነበር እንጂ የራሱ ግቢ የለውም። ውሃ ከጠማችሁ በረፍታችሁ በአካባቢው ካሉ ቤቶች ሄዳችሁ ውሃ ትላላችሁ ይሰጣችኋል። የጠማውም ያልጠማውም ለመጠጣት ይረባረባል።

ትምህርታችን በመደዳ ተቀምጠን ተቃቅፈን እንደኘዞዋኘዝዌ እየተወዛወዝን ፊደላችንን ይዘን በዜማ እንለው ነበር። ፊደሉን ስንጨርስ « በየኔታ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር፣ በጠላት ጉሮሮ አጥንት ይሰንቀር» ስንል ይታወሰኛል። ወር በገባ በ21 ማርያም ይባልና 10 ሳንቲም ከቤት አምጥተን አምባሻ ተገዝቶ ተቆርሶ በልተን ወደ ቤታችን እንሄዳለን። እረፍት ስለምንሆን ጊዜውን በደስታ እንራገጥበታለን። በቄስ ትምህርት ቤት፤ የትምህርት ጅማሪ ጉዞ እንዲህ አሃዱ ብሎ ህግና ሥርዓት ማክበር ነው። የኔታ! እንደ ጨረቃ ያድምቆ፣ እንደ ሰርዶ ያለምልሞዎ፣ ብሎ መመረቅና ጉልበት መሳም የተለመደ ነበር። እየተማርን የኔታ የሚገቡ ከሆነ ሁላችንም ብድግ ብለን እንነሳ ነበር። ሌሎች እንግዶችም ቢመጡ ታላላቆችን አክብሮ መነሳት ሥርዓት ነበር። ቁጭ በሉ ስንባል እንቀመጣለን።



የቄስ ትምህርት ቤት



የአሸር ቤት ወይም መድረሳ

በከተሞች የቄስ ትምህርት ቤት የሚባለውን በገጠር የቆሎ ትምህርት ቤት ይሉታል። መምህራኑ ግን የአብነት ትምህርት ሲሉ ይጠሩታል። ከአባት የተገኘ ከአበው የተወረሰ ማለት ነው። በዚህም እንደከተሞች ፊደል ቆጥሮ መሰናበት ብቻ ሳይሆን ሀሁ፤ አቡጊዳ ፤ መልዕክተ ዮሐንስ የዮሐንስ ወንጌል ዳዊት ይማሩበታል።

የአብነት ትምህርት ቤቶች «ሃይማኖታዊና ባሕላዊ እሳቤዎችን፤ ዕሴቶች እና ትውፊቶችን ለታዳጊዎች እንዲሁም ለአዋቂዎች » ለማስተማር የተወጠኑ የቤተ ክርስቲያን የትምህርት ተቋማት ናቸው ሲል በዚሁ ርዕስ ላይ ጥናት ያከናወኑት አሰለፈች ገብረኪዳንን ጠቅሶ ቢቢሲ በአንድ ወቅት ዘግቦ ነበር።

አሰለፈች ከአብነት ትምህርት ልዩ መገለጫዎች መካከል ታዳጊ ተማሪዎቹ በራሳቸው ለወላጅ ፈቃድ ብዙም ሳይጨነቁ ወደ አዳዲስ ስፍራዎች የሚንቀሳቀሱ መሆናቸው፤ ተማሪዎቹ ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜም ለትምህርት ያቀኑበት ማኅበረሰብ ምግብ በመቸር የሚደግፋቸው መሆኑ፤ ትምህርቱ በጥቅሉ እስከ አርባ ዓመታት ያህል ሊወስድ መቻሉ እና በአብዛኛውም በአፋዊ አስተምህሮ ላይ የተንጠላጠለ መሆኑ ተጠቃሽ ናቸው ይላሉ።

የአብነት ትምህርት ጉባዔ ቤቶች በሚባሉ የትምህርት ዘርፎች የተከፋፈለ ነው። ፕሮፌሰር ስርግው ሀብተሥላሴና ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት የአብነት ትምህርት ቤት ንባብ ቤት፣ ዜማ ቤት፣ አቋቋም ቤት፣ ቅኔ ቤት፣ ቅዳሴ ቤት እና መፃሕፍት ቤት እንደሚከፈል በጽሁፎቻቸው ጠቅሰዋል። እነዚህ ዘርፎች ከስነ-ኃይማኖታዊ ትምህርት በተጨማሪ የንባብ፣ የሙዚቃ፣ የስነ ግጥም፣ የፈጠራ እንዲሁም የስነ ጽሑፍ ዕውቀትን ለአጥኚዎቻቸው ያበረክታሉ። ደራሲ ሀዲስ አለማየሁ ዮፍታሔ ንጉሤ፣ ፕሮፌሰር መስፍን የዚህ አሻራ ያላቸው ነበሩ።

ጋዜጣ ሲጀምር ጸሐፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ፣ ዐጥሜ፣ አለቃ ታዬ፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ፣ሌሎችም አሻራቸው ነበረ። ይህም በወቅቱ በተማሩት ሀገርኛ ትምህርት ነው። ፊደልን፣ የቁጥር ቀመርን፣ ስነ ጽሕፈትና ስነ ጽሑፍን የተወረሰው ከአብነት ትምህርት ነው። በዘመናቸው የቁም ጽሑፍ የሚጽፉ መጽሐፍ የሚደጉሱ ይገኙ ነበር። ቀደም ባሉት መንግሥታት የአስኳላ ትምህርትን ለመመስረትም ሆነ በመንግሥት ተቋማት ለማገልገል ሲፈለግ ግለሰቦች የተወሰዱት ከአብነት ትምህርት ልሂቃን ነበር። ለዚህም እንደ ምሳሌ እነ ሀዲስ አለማየሁና ዮፍታሄ ንጉሴ ይጠቀሳሉ። ትምህርቱን ሲማሩ ከከፉ ምኞት ይርቃሉ፤ (ከሴሰኝነትና ሱሰኝነት፣ ከጭፈራና ዳንኪራ) የዕውቀት ሰይፍ ይታጠቃሉ፣ ሃይማኖታቸውን ያውቃሉ፣ የበቁ የነቁ ሆነው ይገኛሉ።

ወደ ደረሳዎች ደግሞ እንምጣ ደረሳ በእስልምና ልክ እንደ ቆሎ ተማሪዎች ከቦታ ቦታ እየሄዱ ቁራንን የሚቀሩ ተማሪዎች ናቸው። አሸር ቤት ደግሞ የቁርአንን ትምህርት የሚቀስሙበት ነው። በቅርቡ ደራሲ እና ጋዜጠኛ ሐውለት አሕመድ አሸር ቤት በሚል መጽሐፍ አስመርቃ ነበር።

እኔም አማተር ጋዜጠኛ ሆኜ የሚያውቀኝ የክበቤ አባል የነበረው የአሰላው ወዳጄ ሳዲቅ ሐጐስ መጽሐፉን ገዝቶ አበረክቶልኝ ስለነበር የመጽሐፉን ኮድ በኪስ ስልኬ ልኮ በሀገር ፍቅር አዳራሽ በተካሔደው ምርቃት ተገኝቼ መጽሐፉን ወስጃለሁ። ከታች ያለውም ለዚሁ ጽሑፌ ከመጽሐፉ ያገኘሁትን መረጃ ነው፤ ለግብዓት የወሰድኩት እንደሆነ ይታወቅልኝ።

በአሸር ቤት ረጃጅም አግዳሚ የእንጨት ርብራብ ወንዶቹ የሚቀመጡበት ሲሆን የሴቶቹ ደግሞ ከፊት ለፊት የሚገኝ ሆኖ አጫጭር አግዳሚ እንደሆነ የጠቀስኩት መጽሐፍ ያስረዳል። እንደዚያም ሆኖ ስለማይበቃ ጠፍጣፋ ድንጋዮች በማስገባት ለመቀመጫ ይገለገሉበት እንደነበርና እሱም ካነሰ መሬት ላይ መቀመጥ የተለመደ እንደነበር ሐውለት አሕመድ በአሸር ቤት መጽሐፍ የልጅነት ትዝታዋን ታወጋለች።

የአሸር ቤቱ መምህር አሸር ጌታ ነው የሚባሉት። የቄስ ትምህርት ቤቱ መምህር የኔታ እንደሚባሉት ስሙ መሳ ለመሳ የሚመሳሰል ይመስላል። የደስታ ተክለወልድ አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት የኔታ የሚለውን ቃል የኔ (የእኔ) ጌታ፣ ጌታዬ፣ አስተማሪዬ፣ መምህሬ ማለት ነው በሚል ይፈታዋል።

በአሸር ቤት አዳዲስ ገቢዎችን ከፍ ያሉ ልጆች የሚያቀሯቸው ሲሆን የእነሱን አቅሪዎች ደግሞ ሌላ ከእነርሱ በቁርአን ደረጃ ከፍ ያለው ያቀራቸውዋል። እንዲህ እንዲህ እያለ የመጨረሻውን ደግሞ አሸር ጌታ ያቀራሉ። ይሁንና በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ደረሳ ወደሚቀጥለው ለማለፍ የአሸር ጌታን ማረጋገጫ /ይሁንታ ማግኘት አለበት ስትል ሐውለት አሕመድ በጻፈችው መጽሐፍ ታስረዳለች።

በጠዋቱ ክፍለ ጊዜ ትንንሽ ልጆች ሰልፍ ይዘው ቁርአታቸውን ለአሸር ጌታ ያሰማሉ። በሚጠበቀው ደረጃ ካልቀሩ ተኮርኩመው በደንብ እንዲከርሩ (ደጋግሞ መቅራት) ይደረጋል። ከሰዓት በኋላ ወይም በማግስቱ ሊሃክሙ (የአሸር ጌታን ይሁንታ ማግኘት) ይችላሉ። የአሸር ጌታችን እያንዳንዱ ደረሳ ከሕፃን እስከ ታዳጊ ወጣቶች ያለንበትን የቁርአን ደረጃ ያውቃሉ አንድ መስመር እዘላለሁ ብንል በራሳችን ላይ ነው የምንፈርደው፤ ሲል መጽሀፉ ይገልፃል።

ከላይ የጠቀስናቸው ሀገርኛ ትምህርት ቤቶች ዕውቀት እምነትን ስነ ምግባርን ለዜጋው የሚያስተምሩ ነበሩ። ትምህርቱ ደግሞ አፋዊ (በቃል የሚጠና በቃል የሚያዝ ነው።) በጥንቱ ዘመን መጽሐፍ እንደልብ ስለማይገኝ ያነበቡትን በቃል መያዝ ግድ ነበር። አሁንም ይህ ባህል በጠቀስናቸው ትምህርት ቤቶች ይታወቃል። በደርግ ዘመን የእስልምና ጉዳዮች አመራር የነበሩት እና በክርስቲያኑ በሙስሊሙ የሚወደዱት ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሀቢብ የወጡት በጠቀስነው አሸር ቤት ውስጥ መሆኑን መናገር ለቀባሪ ማርዳት ይሆንብናል።

ዘመናዊ ትምህርት ሲመጣ ሀገርኛውን ዕውቀት ገለል ስላደረገው ሰው ጥላቻ ሰባቂ ጦር ነቅናቂ ዘር/ፓርቲ እየቆጠረ መነቋቆር ሥራው አደረገ። ይህ ሀገርኛ ባህላችን በዘመናችን ዘመናዊ ትምህርት እንዳይኮላሽ፤ ሰው ፈጣሪውን የሚፈራ፤ በሀገሩ በእምነቱ የሚኮራ እንዲሆን፤ ዘመናዊ ትምህርቱንም እየተማረ ጎን ለጎን በትርፍ ሰዓቱ እንዲማር ማድረግ ተገቢ ነው።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የየኔወርቅ መንገድ- ከልጅነት አብሮ ያደገ የንግድ ፍላጎት

**ፍሬሕይወት አወቀ**



መነሻዋ ጠንካራ ከሆኑ ነጋዴ ቤተሰቦች ነው። ወላጅ አባቷ የረጅም ጊዜ ቡና አቅራቢ እንዲሁም ቆዳ ነጋዴ ናቸው። ‹‹ባልና ሚስት ከአንድ ወንዝ ይቀዳል›› እንዲሉ ታዲያ ወላጅ እናቷም የባለቤታቸውን ፈለግ ተከትለው በንግዱ ዘርፍ ከላይ ታች ብለዋል። በቡና፣ በቆዳና በሌሎች የንግድ ዘርፎች በመሰማራት ረጅም ጊዜን ካስቆጠሩት ከነጋዴ ወላጆች የተገኙት ልጆችም አብዛኞቹ ነጋዴዎች አይደሉም። የቤቱ አምስተኛ ልጅ ግን የወላጆቿን ፈለግ ተከትላ ብርቱ ነጋዴ ሆናለች። ከዚህች ብርቱ ነጋዴ ጋር ቆይታ ያደረገው የዝግጅት ክፍላችንም ከሕይወት ልምዷ የተካፈለውን እንካችሁ ብሏል።

የንግድ ሥራ በቤት ውስጥ ሲሰራ እያየችና ወላጆቿን እያገዘች ያደገችው የዛሬ የስኬት እንግዳችን የኔወርቅ ቢወጣ ለዓለም ትባላለች። ተወልዳ ያደገችው በአዊ ዞን አዲስ ቅዳም ከተማ ነው። ቤተሰቦቿ በዋናነት በተሰማሩበት የቡና ሥራ ውስጥ ጉልህ አበርክቶ የነበራት በመሆኑ ዛሬ ብርቱ ነጋዴ መሆን ችላለች። እርግጥ ነው ማንኛውም ልጅ ወላጆቹን በቤት ውስጥ በሥራ እንደሚያግዝ ሁሉ እርሷን ጨምሮ እህት ወንድሞቿ ቤተሰቡን በሥራ አግዘዋል። ከእህት ወንድሞቿ በተለየ ግን የኔወርቅ ቢወጣ ለዓለም እገዛዋ ከውስጥ በመነጨ ፍላጎት ጭምር ነበር።

የልጅነት ግዴታዋን ከፍላጎት ጋር በማዋደድ የንግድ ሥራን በቤት ውስጥ ሆና ከወላጆቿ ተምራለች። ከትምህርቷ የሚተርፋትን ጊዜ ሁሉ ቤተሰቦቿን በንግድ ሥራ እያገዘች አድጋለች። ትምህርቷን ሳትዘነጋ ከልጅነት ዕድሜዋ ጀምሮ በሥራ ያደገችው የኔወርቅ፣ ታላላቆቿ በትምህርት ባይገፉም እርሷ ግን በንግድ ሥራው ወላጆቿን ከማገዝ ጎን ለጎን ለትምህርቷ ትኩረት ትሰጥ ነበር። እርግጥ ነው ተወልዳ ባደገችበት በአዊ ዞን አካባቢ ሴት ልጆችን ገና በጠዋቱ ለትዳር መስጠት የተለመደ ቢሆንም፣ የኔወርቅ ግን ወደ ትዳር ሳይሆን ወደ ትምህርት ቤት የመሄድ ዕድል አግኝታለች።

ከታላላቅ እህት ወንድሞቿና ከአካባቢው ማህበረሰብ በተለየ መንገድ ከትዳር ይልቅ በትምህርቷ መግፋት የቻለችው የኔወርቅ፣ የመጀመሪያ ደረጃን ተወልዳ ባደገችበት አዊ ዞን አዲስ ቅዳም ከተማ ተከታትላለች። በወቅቱ ታዲያ በአዲስ ቅዳም ከተማ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አልነበረም። ያም ቢሆን የኔወርቅን ከህልሟ ሊያሰናክላት አልቻለም። በአካባቢው ወደሚገኙ ቡሬና ፍኖተ ሰላም ከተማ በማቅናት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ተከታትላለች።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን አጠናቅቃ ወደ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ያቀናችው የኔወርቅ፣ በአካውንቲንግና ፋይናንስ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ይዛለች። የአካውንቲንግና ፋይናንስ ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ሥራ ፍለጋ ማስታወቂያ አላገላበጠችም። መረጃዎቿን ይዛም ወዲህ ወዲያ አላለችም። በቀጥታ የቤተሰቦቿን የንግድ ሥራ ተቀላቀለች እንጂ። ቀድሞውኑ ያደገችበትንና የምታውቀውን የንግድ ሥራ ተምራ በተማረችው የትምህርት መስክ ለማገልገል ከፍተኛ ፍላጎት አደረባት።

የቤተሰብ በሆነው የንግድ ሥራ ውስጥ የሒሳብ ባለሙያ በመሆን ወደ ሥራ የተቀላቀለችው የኔወርቅ፣ በአዲስ ቅዳም ከተማ በቤተሰቦቿ የንግድ ሥራ ውስጥ ለወራት ከሰራች በኋላ ሙያዋን የሚፈልጉ በርካታ የሥራ ዘርፎች አዲስ አበባ ላይ በመሆናቸው ወደ አዲስ አበባ አቅንታለች። ቤተሰቡ የተሰማራበት የንግድ ሥራ በዋናነት ቡናና ቆዳ ቢሆንም የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች ወደ አዊ ዞን አዲስ ቅዳም ከተማ የሚላከው ከዚሁ ከአዲስ አበባ በመሆኑ አገልግሎቷን ለማስፋት አዲስ አበባ ከተመች።

ከቡናና ከቆዳ ንግድ በተጨማሪም በህንጻ መሳሪያ፣ በህዝብ ትራንስፖርት፣ በጅምላ ንግድና በሌሎችም ሥራዎች የተሰማራው ቤተሰቡ የኔወርቅ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች እንድትሰማራ ዕድል ከፈተላት። በመሆኑም በዋናነት ከምትሰራው የሂሳብ ሥራ በተጨማሪ ጉዳይ በማስፈጸም፣ ዕቃ በመግዛትና በሌሎች የሥራ ዘርፎች ጭምር ተሳትፋለች።

ከልጅነት ዕድሜዋ ጀምሮ በሥራ ያደገችው የኔወርቅ፣ በተለያየና ሰፊ በሆነ የንግድ ሥራ መሳተፍ አልከበዳትም። ይልቁንም በሌሎች የሥራ ዘርፎች ለመሰማራት ያላት ጉጉት በከፍተኛ መጠን እያደገ ሄዶ ለንግድ ሥራ ተሰጠች። እናም ቤተሰቦቿ ከጀማመሯቸው የንግድ ሥራዎች በተጨማሪ በሂደት የሆቴል ኢንዱስትሪን ተቀላቀለች። በትውልድ አካባቢዋ በህዊ ዞን አዲስ ቅዳም ከተማ የመጀመሪያውን አህዱ ሆቴል በማቋቋም የሆቴል ኢንደስትሪውን አንድ ብላ ጀመረች።

አንድ ተብሎ የተጀመረው ሆቴልም በከፍተኛ ትጋት ሁለት ሊባል ሆነ፣ ሁለተኛውን ሆቴል በዳንግላ ከተማ መገንባት ቻለች። ‹‹ዳንግላ ከተማ ለአዲስ ቅዳም ከተማ ቅርብ ከመሆኗ የተነሳ እንደ ሁለተኛ ከተማችን ናት›› የምትለው የኔወርቅ፣ ሁለተኛውንና ባለ ሶስት ኮከብ ጋሹና ሆቴልን ዳንግላ ከተማ ላይ ስትከፍት ትልቅ ትጋት ጠይቋታል። ከምስረታ ጀምሮ ሆቴሉን በማደራጀትና በመክፈት ጉልህ ድርሻ ቢኖራትም እያንዳንዱ የቤተሰቡ አባላት አሻራው ያረፈበት መሆኑንም ትናገራለች።

ጋሹና ሆቴል በዳንግላ ከተማ ውስጥ ቀዳሚ ሆቴል ሲሆን በወቅቱ 27 አልጋዎች የነበሩት ሲሆን በአሁን ወቅት 54 አልጋዎች አሉት። ሆቴሉ የተሟላ አገልግሎት የሚሰጥ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተለያዩ ስብሰባዎች ይካሄዱበታል።

የተማረችው ትምህርት አግዟት ከእህት ከወንድሞቿ በተለየ መንገድ በቢዝነስ ሥራ ውስጥ ገፍታ የገባችውና በትምህርትም ቀዳሚ የሆነችው የኔወርቅ፣ ከዕለት ዕለት የንግድ ሥራ እየገባት በመሄዱ ውጤታማ መሆን ችላለች። ቤተሰቡ ከለመደው አሰራርና የሥራ ባህሪ ወጣ በማለትም በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ለመሰማራት ሌት ተቀን ተግታለች። ለሥራ ባላት ከፍተኛ ፍላጎት ውጤታማ ያደረጋትን ትጋት በማከል ሁለት ሆቴሎችን ማቋቋም ችላለች።

በአዲስ ቅዳም ከተማ እንደስሙ ቀዳሚ የሆነውን አህዱ ሆቴል እንዲሁም በዳንግላ ከተማ ባለሶስት ኮከብ ጋሹና ሆቴልን ያቋቋመችው የኔወርቅ፣ ሆቴሎቹ በሁለት እግራቸው መቆም መቻላቸውን ስታረጋግጥ ፊቷን ወደ ሌላ የንግድ ሥራ አዞራለች። ወላጅ አባቷ በስፋት ይሰሩት የነበረው የቡና ንግድን ጠንቅቃ ታውቀዋለችና ቡናን እሴት ጨምሮ በአገር ውስጥና በውጭ ገበያ ለማቅረብ ተሰናድታ ወደ ሥራው ገብታለች።

ወላጅ አባቷ በቡና ንግድ ሰፊ ልምድ ያላቸው ቢሆንም እስካሁን ቡናን ማልማት እንዳልጀመሩ ያነሳችው የኔወርቅ፣ ወደፊት ቡናን በማልማት የመሰማራት ፍላጎት እንዳላትና ‹‹ከልማት እስከ ኩባያ›› የሚል እቅድ ያላት መሆኗን ተናግራለች። ይህም ማለት ቡናን ከማልማት ጀምሮ ተፈልቶ እስኪጠጣ ድረስ ባለው ሂደት ተሳታፊ በመሆን በእያንዳንዱ ሰው ቤት ተደራሽ መሆን ነው።

በአሁን ወቅት በየካ አባዶ አካባቢ ጋሹና የቡና ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በማቋቋም ቡናን እሴት በመጨመር ቆልታና ፈጭታ ለገበያ ታቀርባለች። ጥሬ ቡናውን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምታገኝ መሆኑን ያነሳችው የኔወርቅ፣ ወላጅ አባቷ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባላቸው ወንበር እንደሆነም አስረድታለች። ይሁንና ወደፊት የቡና ልማት እንደሚኖራት ትልቁ ምኞቷ ነው። ከምርት ገበያ የምታገኘውን የተለያየ ጣዕም ያላቸውን የቡና አይነቶች በጋሹና ቡና ማቀነባበሪያ ፋብሪካ እሴት በመጨመር በጥንቃቄ ተቆልቶና ተፈጭቶ በአገር ውስጥ እንዲሁም በውጭ ገበያ ተደራሽ ታደርጋለች።

‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ ለቁጥር የበዙ የተለያየ አይነት ጣዕም ያላቸው የቡና ዝርያዎች አሉ›› የምትለው የኔወርቅ፣ ጋሹና ቡናም እነዚህን ኢትዮጵያዊ ጣዕም ያላቸውን የቡና አይነቶች በመጠቀም ለገበያ ተደራሽ ያደርጋል። የይርጋ ጨፌ እንዲሁም የሲዳማ ቡናን ለአገር ውስጥ ገበያ በስፋት የምትጠቀም ሲሆን፣ አልፎ አልፎም የጅማ ቡናን ትጠቀማለች። የውጭ ገበያውን በተመለከተ ሁሉንም የቡና አይነቶች በመጠቀም በጥሬውና እሴት በመጨመር ተቆልቶና ተፈጭቶ እንደገበያው ፍላጎት ታቀርባለች።

ጋሹና ቡና በአሁን ወቅት በአገር ውስጥ ገበያ በስፋት እየገባ መሆኑን ያነሳችው የኔወርቅ፣ ፍላጎቷም ከውጭ ገበያ በበለጠ በአገር ውስጥ ገበያ በስፋት መግባት ነው። ምክንያቱም ጥሩ ጣዕም ያለው ቡና ማህበረሰቡ መጠቀም አለበት የሚል ጠንካራ ዕምነት ያላት በመሆኑ ነው። ‹‹ሰዎች ጥሩና ተመራጭ የሆነውን የአገራቸውን ቡና በመጠጣት የተፈጥሮን ጣዕም ማጣጣም እንዳለባቸውና ቆንጆ ጣዕም ያለውን የኢትዮጵያ ቡና ባህላዊ እሴቱን ሳይለቅ ሁሉም ሰው ደርሶት ይጠጣ›› የምትለውም ለዚሁ ነው።

ጋሹና ቡና ኢትዮጵያዊ ጣዕም ያላቸውን የተለያዩ የቡና አይነቶች ከአገር ውስጥ ባለፈ ወደ ውጭ ገበያ በመላክ የተሰማራ ቢሆንም ቅድሚያ ለአገር ውስጥ ገበያ ይሰጣል። የአገር ውስጥ ገበያውን ተደራሽ በማድረግ ገበያው በፈለገው መጠን ቡናን በጥሬውና እሴት ጨምሮ የተቆላው ቡናን ወደ ውጭ ገበያ እየላከ ይገኛል።

በመላው አገሪቱ ተደራሽ የመሆን ፍላጎት አለኝ የምትለው የኔወርቅ፣ ሁሉም ሰው የኢትዮጵያን ቡና ቢያጣጥመው ትወዳለች። እንደ አገር ደግሞ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመሸፈን በኤክስፖርት ላይ በስፋት ቢሠራ መልካም ነው በማለት የአገርን ገቢ በማሳደግ ረገድ ጉልህ ድርሻ ያለው የቡና ዘርፍ ገና ብዙ ያልተሰራበትና ሊሰራበት የሚገባው ዘርፍ እንደሆነም አጽንኦት ሰጥታ ትናገራለች።

ጋሹና ቡና በስፋት ገበያ ውስጥ ከገባበት አዲስ አበባ ከተማ በተጨማሪ አዳማና ደብረዘይት በመጠኑ ተደራሽ መሆን ችሏል። ይሁንና ድርጅቱ ብራንዲንግ ላይ ወይም ደግሞ መለያ ስም ላይ የሚሰራ በመሆኑ አጠቃላይ ማህበረሰቡ ጋሹና ቡናን በካፌ ደረጃ ማጣጣም የሚችልበትን ዕድል የመፍጠር ዕቅድም አላት። ጎን ለጎንም ሰዎች እንደየፍላጎታቸው ቡናውን በጥሬው፣ እንዲሁም ተቆልቶና ተፈጭቶ መጠቀም እንዲችሉ ይቀርባል።

ከአገር ውስጥ ባለፈ ለውጭ ገበያ የሚቀርበው ጋሹና ቡና በአሜሪካ ቨርጂኒያ፣ ሚኒሶታና ሜሪላንድ ተደራሽ ሲሆን በአፍሪካ ደግሞ ማሊና ባማኮ እንዲሁም በአረብ ኢምሬትስ ሳውዳረቢያ የገበያ መዳረሻዎቹ ናቸው። የውጭ ገበያውን በስፋት ለመቀላቀል በተለይም ጥራት ላይ ትኩረቱን በማድረግ እየሠራ ያለው ጋሹና ቡና በቀጣይም በዓለም አቀፍ ገበያው ተወዳዳሪ ለመሆን የማቀነባበር ሥራውን በተሻለ ጥራት ይሰራል በዚህም ጥሩ ተከፋይ ይሆናል።

ጋሹና ቡና በቀጣይ ያስቀመጣቸው ሰፋፊ እቅዶች እንዳሉ ሆነው በአሁን ወቅት 32 ዜጎች ለሚደርሱ የአካባቢው ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል። እነዚህ ሰራተኞችም ቡናውን ከመልቀም ጀምሮ እስከ ማሸግ ያሉትን ሥራዎች ያከናውናሉ። አብዛኞቹ ሠራተኞች ሴቶች መሆናቸውን ያነሳችው የኔወርቅ፣ ሴቶች ለሥራ ትጉና ጠንቃቃ በመሆናቸው ምክንያት ቅድሚያ መስጠቷን ትናገራለች።

በጋሹና ቡና ማቀነባባሪያ ከተፈጠረው 32 የሥራ ዕድል በተጨማሪ በህዊ ዞን ዳንግላ ከተማ በሚገኘው ጋሹና ባለ ሶስት ኮከብ ሆቴል ከ55 በላይ የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለችው የኔወርቅ፣ ሆቴሉም ለአካባቢው ማህበረሰብ የተሟላ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ከመደበኛው አገልግሎት በተጨማሪም አካባቢዎች እየመጡ ለሰርግ፣ ለልደትና ለተለያዩ ፕሮግራሞች የሚጠቀሙ ደንበኞችም አሉት።

ጋሹና ቡና ማቀነባባሪያ ፋብሪካ የሚገኘው የካ አባዶ ኮንዶሚኒየም አካባቢ በከተማ ኢንዱስትሪ ስር እንደመሆኑ ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ የአካባቢውን መንገድ ማሰራት ችላለች። የሚፈጠረው የሥራ ዕድልም ከአካባቢው ማህበረሰብ ውጭ አይሆንም። ከዚህ በተጨማሪም በበዓላት ወቅት በአካባቢው የሚገኙ አቅመ ደካሞችን በመጎብኘት እንዲሁም መንግሥት በሚያቀርበው ማንኛውም አገራዊ ጥሪ ምላሽ በመስጠት ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ ያለ ተቋም ነው።

በቀጣይም ጋሹና ቡና የተነሳበትን ዓላማ ለማሳካት በቡና ልማት በመሰማራት ኢትዮጵያዊ የሆኑና የተለያየ ጣዕም ያላቸውን የቡና አይነቶች በማልማት ከምርት እስከ መጠጥ እንዲደርስ በትጋት መሥራት የየዕለት ተግባሯ እንደሆነ ትናገራለች። ‹‹የኢትዮጵያ ቡና ልንኮራበት የሚገባ ትልቁ ሀብታችን ነው›› የምትለው የኔወርቅ፣ ከላይ ካለው አካል ጀምሮ እስከታች ያለው አርሶ አደር የኢትዮጵያ ቡና በኩራት ቢያስተዋውቅና ቢሰራበት ሕዝቡም አገሪቷም ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ ይችላሉ። ቡና ለአገሪቷ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ሆኖ ከማገልገሉም ባለፈ በቀጣይም ትልቅ ተስፋ የሚጣልበት ዘርፍ በመሆኑ ትኩረት ያሻዋል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት



## አህጉሪቱን የማስተሳሰር ተስፋ የተጣለበት የአፍሪካ መሰረተ ልማት ፕሮግራም

**መላኩ ኤሮሴ**

መሰረተ ልማት ለኢኮኖሚ እድገት እና ለድህነት ቅነሳ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በአንፃሩ የመሰረተ ልማት እጦት በምርታማነት ላይ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር፤ የምርት እና የግብይት ወጪን ስለሚጨምር የንግድ ድርጅቶችን ተወዳዳሪነት በመቀነስ እና መንግሥታት የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችን የመፈጸም አቅምን በመቀነስ እድገትን ያደናቅፋል።

በአፍሪካ ውስጥ የመሰረተ ልማት እጥረት መኖሩ የማያከራክር ሃቅ ነው:: የመሰረተ ልማት እጥረት በአህጉሪቱ ተወዳዳሪነት ላይ ግልጽ የሆነ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል:: የአፍሪካ ሀገራት በተለይም ከሰሃራ በስተደቡብ ያሉት ሀገራት በዓለም ደረጃ ዝቅተኛ ተወዳዳሪ ከሆኑት ሀገራት ተርታ ይሰለፋሉ:: የመሰረተ ልማቶች እጥረት ሀገራቱን ወደኋላ ከሚጎትቷቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል ተጠቃሽ ነው። ይህ አህጉራዊ መፍትሄ የሚፈልግ አህጉራዊ ችግር ነው።

ከ54ቱ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ አብዛኞቹ ሀገራት ከሕዝብ ቁጥርም ሆነ ከኢኮኖሚ አንጻር ሲታይ ትንንሽ ከመሆናቸው በተጨማሪ የመሰረተ ልማት ስርዓታቸው ልክ እንደ ድንበራቸው ሁሉ የቅኝ ግዛት ዘመን ነፀብራቅ ናቸው:: መንገዶች፣ ወደቦች እና የባቡር ሀዲዶች የአህጉሪቱን ሀገራት በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ከማስተሳሰር ይልቅ ለሀብት ብዝበዛና ፖለቲካዊ ቁጥጥር እንዲያመች ታስቦ በቅኝ ገዥዎች የተገነቡ ናቸው::

እነዚህን ችግሮችን ለመቅረፍ ቀጣናዊ ውህደት ወሳኝ ነው:: አፍሪካ የዕድገት አቅሟን በውል ለመረዳት፣ በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ በብቃት ለመሳተፍ እንዲሁም የሉዓላዊነት (የግሎባላይዜሽን) ጥቅሞችን ለመቋደስ ከሁሉ የተሻለው ምናልባትም ብቸኛው የውህደት መንገድ ነው። ውህደትን እውን ለማድረግ ቀጣናዊ መሰረተ ልማቶች መገንባት ወሳኝ ናቸው::

የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን የመሰረተ ልማት እና ኢነርጂ ኮሚሽነር ዶክተር አቡ-ዘይድ አማኒ እንደሚሉት፤ መሰረተ ልማት የ2063 አጀንዳን ተግባራዊ ለማድረግ እና የአህጉሪቱን ሕዝቦች የልማት ምኞት ለማሳካት የጀርባ አጥንት ነው:: አህጉሪቱን ከማስተሳሰር ባሻገር የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ወሳኝ ነው:: መሰረተ ልማት ሕዝብን ከሕዝብ፣ ገበያን ከገበያ፣ ምርትን ከገበያ፣ ሀገራትን ከሀገራት እና ቀጣናን ከቀጣና ያስተሳስራል:: እንዲሁም ሕዝብ የኤሌክትሪክ ኃይልን በቀላሉ እንዲያገኝ፣ ተማሪን ከትምህርት ቤት ለማገናኘት ከሰዎች ጋር ለመነጋገር እንዲሁም፣ ታማሚን ከጤና ተቋማት ለማድረስ፣ ለሌሎች ጉዳዮች መሰረተ ልማት ወሳኝ ነው:: በአጠቃላይ ለልማት እና ለሕዝቦች ኑሮ መሻሻል መሰረተ ልማት የጀርባ አጥንት ነው::

**መሰረተ ልማት ሕዝብን ከሕዝብ፣ ገበያን ከገበያ፣ ምርትን ከገበያ፣ ሀገራትን ከሀገራት እና ቀጣናን ከቀጣና ያስተሳስራል። እንዲሁም ሕዝብ የኤሌክትሪክ ሀይልን በቀላሉ እንዲያገኝ፣ ተማሪን ከትምህርት ቤት ለማገናኘት ከሰዎች ጋር ለመነጋገር እንዲሁም፣ ታማሚን ከጤና ተቋማት ለማድረስ፣ ለሌሎች ጉዳዮች መሰረተ ልማት ወሳኝ ነው። በአጠቃላይ ለልማት እና ለሕዝቦች ኑሮ መሻሻል መሰረተ ልማት የጀርባ አጥንት ነው**

መሰረተ ልማት ያለውን ጠቃሜታ ከግምት በማስገባት፤ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች በተለያዩ ስብሰባዎች ቀጣናን ከቀጣና እንዲሁም አህጉሪቱን የሚያስተሳስሩ መሰረተ ልማቶች ግንባታ ሊካሄድ እንደሚገባ ለዓመታት ሲማከሩ ቆይተዋል:: በመጨረሻም እ.አ.አ በ2012 በተካሄደው 18ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች መደበኛ ጉባኤ ላይ የአፍሪካ መሰረተ ልማት ፕሮግራም አጽድቀው ወደ ትግበራ ገብቷል:: ፕሮግራሙ ለአህጉሪቱ የረጅም ጊዜ ፋይዳ በሚያስገኙ 10 ዘርፎች ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው::

ፕሮግራሙ የትራንስፖርት፣ የኢነርጂ፣ የድንበር ተሻጋሪ ውሃ እና ቴሌኮሙኒኬሽን አይ ሲ ቲን ጨምሮ በርካታ ዘርፎችን የሚያካትት ባለብዙ ዘርፍ ፕሮግራም ሲሆን፤ የአህጉሪቱን ኃይል የማመንጨት አቅምን መጨመር፤ እያደገ ያለውን የንግድ እና የኢንዱስትሪ ፍላጎትን ለማሟላት የባቡር መሰረተ ልማት ማዘመን፤ አዳዲስ ግድቦችን፣ ሰው ሰራሽ ሀይቆችን፣ የውሃ ቧንቧዎችን በመገንባት ለግብርና፣ እና ለኢንዱስትሪ የውሃ አቅርቦት ማረጋገጥ ይገኙበታል::

በተጨማሪም የሰው እና የሸቀጥ እንቅስቃሴን የሚያሳልጥ የመንገድ፣ የባቡር፣ ወደብ፣ የአየር ትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ግንባታን ማፋጠን፤ አይ ሲቲ በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ላይ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ የኮሙዩኒኬሽን እና የመረጃ ልውውጥ አቅምን ከማሳደግ ባሻገር አህጉሪቱ በዓለም አቀፍ የቢዝነስ ልውውጥ ውስጥ ተሳታፊ እንድትሆን ማስቻልን ትኩረቱ ያደረገ ነው:: ፕሮግራሙ የአፍሪካ ህብረት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚረዳውን የአቡጃ ስምምነትን ተግባራዊ ለማድረግ የተነደፈ ነው።

ኮሚሽነር ዶክተር አቡ- ዘይድ አማኒ እንደሚሉት፤ ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ የረጅም ጊዜ፣ የመካከለኛ ጊዜ እና የአጭር ጊዜ ግቦች የተቀመጡ ሲሆን፤ ፕሮግራሙ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ ነው:: ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ በየዓመቱ 90 ቢሊየን ዶላርን ይጠይቃል:: ቅድሚያ የሚሰጣቸው አንዳንድ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ተደርገዋል:: ተግባራዊ ከተደረጉት ፕሮጀክቶች መካከል በጊኒ ውስጥ የተገነባው የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ተጠቃሽ ነው:: ሌሎች በጣም ጠቃሚ የሆኑ ፕሮጀክቶችም ጥሩ አቋም ላይ ይገኛሉ:: ከግብጽ ካይሮ ተነስቶ እስከ ደቡብ አፍሪካ ኬፕ ታወን ከተማ የሚሄደው የመንገድ ፕሮጀክት ግንባታም ጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል::

ከፕሮግራሙ ሙሉ በሙሉ እውን ሲሆን የሚጠበቁ በርካታ ውጤቶች ያሉ ሲሆን፤ ከፕሮግራሙ ከሚጠበቁ ውጤቶች መካከል የኃይል ወጪዎችን መቀነስ እና የኃይል ተደራሽነትን መጨመር አንዱ ነው:: ፕሮግራሙ እ.አ.አ በ2009 39 በመቶ ላይ የነበረውን የአህጉሪቱን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ቁጥር በ2040 ወደ 70 በመቶ ያሳድጋል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ማለት ለተጨማሪ 800 ሚሊዮን ሕዝብ ተደራሽ ይሆናል እንደማለት ነው።

የትራንስፖርት ወጪን መቀነስ እና የአፍሪካ ውስጥ ንግድን ማሳደግ የፕሮግራሙ ሌላኛው የሚጠበቅ ውጤት ነው። ፕሮግራሙ በአህጉሪቱ ውስጥ የንግድ ኮሪደሮች ክፍት እንዲሆኑ ስለሚያደርግ የትራንስፖርት ውጤታማነትን ይጨምራል:: የትራንስፖርት ውጤታማነት ላይ በሚፈጠረው መሻሻል አህጉሪቱ ቢያንስ እስከ 172 ቢሊየን ዶላር እንድታገኝ ያስችላል:: በቀጣናዊ ውህደት እና አገልግሎቶች ላይ ያለው ቀጣይነት እመርታ በሂደት የአህጉሪቱ ሀገራት ከባህር ማዶ ሀገራት ጋር የሚያደርጉትን የንግድ ልውውጥ በማስቀረት በአፍሪካ ሀገራት እና በቀጣናዎች መካከል የንግድ ልውውጥ እንዲደረግ እድልን ይፈጥራል:: ይህም የ2028 የአፍሪካ የጋራ ገበያ ተስፋን ለማሳካት ይረዳል።

የውሃ እና ምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረገድም ከፍ ያለ ውጤት ያስገኛል ተብሎ ይጠበቃል:: መረጃዎች እንደሚያሳዩት አፍሪካ በዓለም ዝቅተኛ የውሃ ማጠራቀሚያ አቅም እና አነስተኛ የመስኖ ግብርና ያላት ሲሆን፤ ከአህጉሪቱ ግማሽ ያህሉ የውሃ እጥረት ያጋጥመዋል:: በተቃራኒው ፍላጎቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው:: በመጪው ዘመን አህጉሪቱ የሚያጋጥማትን የውሃ ችግር ለመቋቋም ፕሮግራሙ ለምግብ ምርት እና ለንግድ አስፈላጊ የሆነውን የውሃ ማጠራቀሚያ መሠረተ ልማትን እውን ለማድረግ ያስችላል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ነው።

የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ፕሮግራሙ ይፋ በተደረገበት ወቅት ያወጣው መረጃ እንዳመላከተው ፕሮግራሙ አህጉሪቱ ከሌላው ዓለም ጋር ያለውን ግንኙነትም ይጨምራል:: የብሮድባንድ ግንኙነትን በ20 በመቶ ያሳድጋል። እ.ኤ.አ በ2018 የሚጠበቀው የብሮድባንድ ግንኙነትን በ10 በመቶ ማሳደግ በሸቀጦች እና በገበያዎች፣ በሰዎች እና በሥራዎች መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር የአህጉር ውስጥ ምርትን አንድ በመቶ ይጨምራል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበት ነበር::

ፕሮግራሙ እጅግ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን የሚያቅፍና እጅግ ከባድ ሥራ የሚጠይቅ ነው የሚሉት ኮሚሽነር አቡ-ዘይድ አማኒ፤ ከባድ የሚሆነው ከፋይናንስ ረገድ ብቻ አይደለም:: ለአብነት ያህል የተለያዩ ሀገራትን አቋርጠው የሚያልፉ መንገዶችን ለመገንባት የተለያዩ ሀገራት ፖሊሲዎችን ማጣጣም የግድ ነው:: ብዙ ቀጣናዎችን እና ሀገራትን የሚያስተሳስሩ ፕሮጀክቶችን መገንባት የራሱን ስትራቴጂ የሚፈልግ ነው::

ፕሮጀክቶቹ እውን እንዲሆኑ አፍሪካ ህብረት ኮሚሽን የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ከመስራት ጀምሮ፤ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ፕሮጀክቶቹ ተፈጻሚ እንዲሆኑ የገንዘብ ምንጮችን የማዘጋጀት እና ሌሎች አስፈላጊ ሥራዎችን እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል። ፕሮግራሙን ተግባራዊ የሚያደርገው አፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ብቻውን ሳይሆን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በጋር በመተባበር ነው::

በአፍሪካ መሰረተ ልማት ፕሮግራም የተካተቱ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ከተለያዩ አካላት ጋር በከፍተኛ ምክክር ላይ ተመርኩዘው የሚሰሩ ናቸው። የሚሉት ዶክተር አቡ-ዘይድ አማኒ፤ የአፍሪካ ልማት እቅድ እና ማስተባበሪያ ኤጀንሲ (NPCA) እና የአፍሪካ ልማት ባንክ (AFDB) የጋራ አነሳሽነት የተጀመረ ፕሮግራም ነው። ፕሮግራሙ በቀጣናዊ እና አህጉራዊ ማስተር ፕላኖች እና የድርጊት መርሃ ግብሮች እንዲሁም በአፍሪካ ህብረት (AU)፣ ቀጣናዊ የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች (RECs)፣ በቀጣናዊ እና አህጉራዊ ቴክኒካል ኤጀንሲዎች (የሀይቅ እና የተፋሰስ ድርጅቶችን ጨምሮ) በሚመለከታቸው ሀገራት ላይ የተመሰረተ ነው። አዲስ አጋርነት ለአፍሪካ ልማት (ኔፓድ) ደግሞ ለፕሮግራሙ የራሱን ሚና ይጫወታል::

የመሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት ከፍተኛ በመሆኑ ለሥራው የውጭ ድጋፍ አስፈላጊ ቢሆንም፤ በውጭ በጀት ላይ መደገፍ ግን አስፈላጊ አለመሆኑ ስለታመነበት የአፍሪካ መሰረተ ልማት ፕሮግራም ፋይናንስን በተለያዩ መንገዶች ያሰባስባል:: በአህጉሪቱ ውስጥ ካለው የግሉ ዘርፍ ጋር በቅርበት እየተሰራ ነው:: ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተጨማሪ የግሉ ዘርፍ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን መደገፍ አለባቸው:: አብዛኛው የአህጉሪቱ የግል ዘርፍ መዋዕለ ንዋዩን በአይ ሲቲ ዘርፍ ላይ ሲያፈስ ይታያል፤ በዚህ ዘርፍ መዋዕለ ንዋያቸውን የሚያፈሱት በአጭር ጊዜ ውስጥ ትርፍ የሚገኝበት በመሆኑ ነው:: ነገር ግን በረጅም ጊዜ የግሉንም ዘርፍ ሆነ አህጉሪቱን በሚጠቅሙ ፕሮጀክቶች ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን ሊያፈሱ እንደሚገባ ጠቁመዋል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## ወገን ድጋፋችንን የሚጠብቅበት ወሳኝ ወቅት!

ሀገራችን በተለያዩ ወቅቶች ባጋጠሟት የድርቅ አደጋዎች ከፍ ላሉ ሰብዓዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራዎች ተዳርጋለች። በአደጋዎቹ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ለሞትና ለስደት ተዳርገዋል፤ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር የሀገር ሀብትና ንብረት ለውድመት ተዳርጓል፤ በዜጎች ላይ የተፈጠሩ የስነ ልቦና ጠባሳዎችም ዛሬም ቢሆን ገና አላገገሙም።

በ1966 እና በ1977 ዓ.ም በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍሎች በተከሰቱ የድርቅ አደጋዎች ካደረሱት ከፍተኛ ሰብዓዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውድመት ባለፈ ሀገሪቱን በዓለም አቀፍ መድረክ የሀገራችንን ገጽታ በእጅጉ ጎድተዋል፤ የረሀብ ተምሳሌት ተደርጋ እንድትሳልም ነበር። በወቅቱም እንደ ሀገር የከፈልነው ዋጋ የጥቁር ታሪካችን አንድ አካል ተደርጎም ይወሰዳል።

ይህ የታሪካችን ጥቁር ነጥብ አንገት አስደፍቶናል፤ ዛሬ ላይ ሆነን ሳይቀር ወቅቱን ከፍ ባለ የልብ ስብራት እንድናስብ አድርጎናል፤ በተለይም ፈጥነን በመንቀሳቀስ ልንታደጋቸው እንችል የነበርናቸውን ወገኖቻችንን በእኛ የዝግጅትና የአቅም ማነስ፤ በችግሩ የፖለቲካ ትርፍ /የፖለቲካ ቁማር / አስልተው የተንቀሳቀሱ ቡድኖች ያስከፈሉን ዋጋ ሌላው አስከፊ ገጽታ ነው።

ይህ ጥቁር ታሪክ የፈጠረውን የልብ ስብራትም ሆነ ዓለም አቀፍ ትርክት ለመለወጥ እንደ ሀገር ከፍ ባለ ቁርጠኝነት መንቀሳቀስ በጀመርንበት ማግስት፤ ከተረጂነት ወጥተን በምግብ እህል ራሳችንን ለመቻል ያለንን አቅም እያሰባሰብን ባለበት አሁን ዛሬ ላይ ተመሳሳይ የድርቅ አደጋ በቦረና ዞን ተከስቶ በወገኖቻችን ላይ ከባድ አደጋ ደቅኖ ይገኛል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ፤ በዞኑ ባለፉት ሦስት ዓመታት ለተከታታይ አምስት ዙር ዝናብ ሳያገኝ ቆይቷል። በዚህም የተነሳ በዞኑ የሚገኙ 13 ወረዳዎች በድርቅ ተጠቅተዋል፤ በድርቁ ከሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ በላይ እንስሳት ሞተዋል፤ 807 ሺህ ሰው ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ከእነዚህም ውስጥ 167 ሺህ የሚሆኑ ደግሞ አስቸኳይና ተከታታይ ድጋፍ የሚፈልጉ ናቸው።

መንግሥት በአንድ ዙር ብቻ ከ600 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ከ90 ሺህ ስድስት መቶ ኩንታል በላይ ስንዴ፣ ሁለት ሺህ 66 ሊትር ዘይት እና 22 የውሃ ቦቴዎች ርዳታ አቅርቧል፡ ከመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና አጋር አካላት ወደ 750 ሚሊዮን የሚጠጋ ገንዘብ ተገኝቷል። ይህም ሆኖ ግን እየቀረበ ያለው ርዳታ ከችግሩ ስፋት አንጻር በቂ አይደለም፤ እንደ ሀገር ፈጥነን መንቀሳቀስ ካልቻልን ሊያስከፍለን የሚችለው ዋጋ የከፋ ሊሆን እንደሚችል መገመት የሚከብድ አይደለም።

በርግጥ አሁንም ቢሆን እንደ ሀገር በቦረና እንስሳት ላይ የደረሰው ጥፋት፤ ከቦረና እንስሳት የዝርያ ተፈላጊነት አንጻር በቀላሉ የሚሰላ አይደለም። የተቀሩትን ለመታደግ ሊኖር የሚችለውን አማራጭ ሁሉ መጠቀምን የሚጠይቅ ነው። የአካባቢው ማኅበረሰብ አርብቶ አደር ከመሆኑም አንፃርም እንስሳቱን መታደግ ማለት ነገዎቹን ከዛሬ ጽልመት አላቆ የብርሃን ተስፋ ማልበስ ያህል ነው።

ለዚህ ደግሞ መንግስት እንደ መንግስት ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያደርገው ጥረት የሚበረታታ፤ ከፍ ባለ ደረጃ ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባ ነው። በተለይም የአስቸኳይ ጊዜ ርዳታዎችን በማቅረብም ምንም አይነት ሰብዓዊ ቀውስ እንዳይፈጠር በትኩረት መስራት ይኖርበታል።

በተለይም የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ለመላው ሕዝባችንንና ለዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ በማሳወቅ፤ በችግሩ ዙሪያ ያሉ ብዥታዎችን ማጥራትና የርዳታ አቅርቦቶች በስፋት ለተረጂዎች የሚደርሱበትን አስቸኳይ ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል።

መላው ሕዝባችንም ያጋጠመን ችግር ከእኛ አቅም በላይ ያልሆነ፤ በኃላፊነት መንፈስ በአንድነት መንቀሳቀስ ከቻልን በቀላሉ ፈጥነን ልንቆጣጠረው የምንችለው መሆኑን በመረዳት "ለወገን ደራሽ ወገን ነው" በሚል መርህ ማዘጋጀት ይኖርበታል። በዚህም ራሱን ከታሪክ እና ከትውልዶች ተወቃሽነት መታደግ ይችላል!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

እፕድ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ልጓም ሊበጅለት የሚገባው የጫኝና አውራጆች ጉዳይ

ትንሳኤ አበራ

ሰሞኑን እኔ ወደ ምኖርበት ኮንዶሚኒየም አንድ ጓደኛችን ቤት ሊቀይር እንደሆነ ነግሮኝ ነበር። ወደ አካባቢው በመምጣት የሚከራየውን ቤት አይቶ በዋጋ ከተስማማ በኋላ ኪራዩን ከፍሎ ቁልፍ ተቀብሎ ነገ እቃዬ ይዤ እመጣለሁ ብሎ ይሄዳል። ሆኖም ግን በዚያው ዕለት ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት አካባቢ ሲሆን ጓደኛችን እቃውን በመኪና አስጭኖ በመምጣት እንድናግዘው ስልክ ሲደውል በጣም ነበር የተደናገጥኩት።

በብርሃን ወደ ተከራየው ቤት መግባት እየቻለ እንደሌባ በሌሊት እቃውን ለማጓጓዝ መሞከሩ ቢገርመኝ ሌሊት የሚያስኬድ ምን ጉድ መጣ ስል ጠየኩ። እሱም እቃውን ከመኪና ላይ ለማውረድ የሚጠየቀው ብር ከአቅሙ በላይ በመሆኑ በጫኝና አውራጆችን የሥራ መስክ የተደራጁ ወጣቶችን ለመሸሽ ጉዞውን በሌሊት ማድረጉን አወጋኝ። ለካ እኔ አላስተዋልኩም እንጂ ማታ ማታ ከምሽት ስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ 12 ሰዓት ባለው ጊዜ ወደፎቅ የሚመላለስ የእግር ኮቴና የእቃ ኳኳታ መበራከት ለዚህ ኖሯል።

ቤቴ ምድር ላይ በመሆኑ አንዳንድ ቀን ከታች ወደላይ ወይም ከላይ ወደታች የሚመላለሰው የሰው ኮቴና የእቃ ኳኳታ ስሰማ የደህንነት ስጋት አሳድሮብኝ እንደነበር አልሸሸገም። ከቤቴ ባልወጣም በመስኮቴ አሻግሬ እንደተመለከትኩት ለግርግሩና ለኳኳታው ምክንያት የሆኑት ከፎቅ ወደ ምድር እቃ የሚያጓጉዙ ሰዎች (ቤት በመልቀቅ ላይ ያሉ) መሆናቸው ተመልክቼ ነበር።

በወቅቱ ግምቴ የነበረው ቤት የሚለቁ ሰዎች እቃቸውን ቀስ ብለው በጥንቃቄ በማውረድ ለመኪናው ቅርብ ወደ ሆነው /የመኪናው ማቆሚያ ቦታ/ፓርኪንግ/ በማስጠጋት በማግስቱ በጠዋት መንገድ ሳይዘጋጋ ለመጫን እንዲመቻቸው አስበው እንደሆነ ነበር። ነገሩ "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" አይነት መሆኑ የገባኝ ግን አሁን ላይ ትንሽ ዘግይቶ ነው። ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ ይባል የለ በጨለማ ጉዞን ከመጣ ጉዳዩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትምና ስለጉዳዩ የሚያወቁ ሰዎች ለማነጋገር ወሰንኩ።

ቤት በመልቀቅ ላይ ያሉ ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ በጨለማ ቤት ለመልቀቅ የተገደዱበት ዋንኛ ምክንያት በጫኝና አውራጅ ተደራጅተው በየሰፈሩ እኛ ካልሆንን ማንም ሰው ይህንን እቃ ከመኪና ላይ ማወረድ አይችልም የሚሉ ጉልበተኞችን ሽሽት እንደሆነ ይናገራሉ። ታዲያ ቢያወርዱስ ምን አለበት ሥራቸው አይደል እንዴ ስል ጠየኩኝ።

ማውረዱን ማን ከልክሎቸው ነገር ግን እቃውን ከመኪና ላይ ለማውረድ የሚጠሩት ዋጋ ሁሉም እቃ ቢገመት የማያወጣውን ነው ይላሉ። አንድ መኪና እቃ ለማውረድ የሚጠይቁት ብር በቀላሉ ከ5ሺ ብር በላይ እንደሆነም ጭምር ነግረውኛል።

እቃውን ከመኪና ለማውረድ እነሱ ከተመኑት ዋጋ ተከራክሮ ለማስቀነስ የማይሞከርና የማይቻል እንደሆነም ያነሳሉ። ምናልባት ልባቸው ራርቶ ቀነስን ካሉ እንኳን ቀነስን ብለው የሚጠሩት ብር ከአራት መቶ እና አምስት መቶ ብር አይበልጥም። ሰውየው የመክፈል አቅም ይኑረውም አይኑረውም እነሱ የሚጠሩትን ዋጋ እስካልከፈለ ድረስ ያንን እቃ ማውረድ ሆነ በሌላ አካል ማስወረድ አልችልም፤ ኧረ እንዲያውም አይታሰብም።

ግምታዊ ጥሪያቸውን ያልቻለ ሰው ደግሞ ለራሱ በቤተሰብ አባላት ሊያወርድ ቢሞክር እንኳን ጉድ ነው የሚፈላው። እንዴት ይህ ሆነ ብለው በሰው ንብረት ላይ ፈቃጅና ከልካይ ሆነው ለያዥ ለገናዥ አስቸግረው ለግብግብና ለዱላ የሚዳረጉበት ሁኔታዎች የተፈጠሩበት አጋጣሚዎች መኖራቸው የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ።

የኑሮ ውድነቱ ናላው የዞረው የቤት ተከራይ ደግሞ የተሻለ አማራጭ ሲያገኝ ትንሽ ብር ትርፍ አገኘሁ ብሎ ተደስቶ ቤት ለቆ ሌላ ቦታ ሲገባ ካለበት ሲለቅም ሆነ ወደሌላ ቦታ ሲገባ የጫኝና አውራጅ የሚጠየቀው ሁለት ጊዜ ነው። ከነበረበት አካባቢ ሲለቅ ሆነ ወደ አዲሱ ሠፈር ሲገባ ንብረቱ ወደ መኪና ለማስጫንም ሆነ ለማስወረድ የቤቱን የአንድ ወር ኪራይ ክፍያ የሚበልጥ ወጪ ለእቃ መጠየቁ አይቀሬ ነው።

በፊት የነበረበት የከፈለ ሰው እንኳን እዚያ ከፍዬ ነው ያስጫንኩት ቢል ሰሚ የለውም። ሰውየው መክፈል አልችልም እባካችሁ በአቅሜ መጠን ይህንን ያህል ልክፈል ብሎ ስቅስቅ ብሎ ቢያለቅስ እንባው ከማበስ ይልቅ የጉልበት ጨዋታ ይጀመራል። ባስ ሲል ደግሞ የሕግ ያለህ ብሎ ቢጮህ እንኳን ጩኸቱ ሰሚ አልባ ነው።

በአካባቢው ያሉ የጸጥታ አካላትን ቢያመለክት ጫኝና አውራጅ ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት በሕግ የተደራጁ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው መሆናቸውን አስረግጠው በመንገር ተስማሙ ከማለት በዘለለ የሚሰጡት መፍትሔ የለም።

በጫኝና አውራጅ የተደራጁ አካላት የጭነት አገልግሎት የሚሰጡ መኪናዎች ወደ ኮንደሚኒየም ውስጥ የሚያስገባው መንገድ ሲጎዙ ካዩ ከየት መጡ ሳይባል መኪናውን በቁጥጥር ሥር ያውሉታል ። "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ ከኑሮ ውድነት የተነሳ ሰው የእለት ጎሮሮውን እንኳን ለመሸፈን እየተናነቀው ባለበት በዚህ ጊዜ ደግሞ በሰበብ አስባብ ኪሳቸውን ለማዳበር የሚፈልጉ ሊያውም በመንግሥት አካላት በሕግ የተደራጁ አካላት እየፈጸሙት ያለው ተግባር አስነዋሪ ነው።

ምክንያቱም እነሱን ሽሽት ሰዎች ከሚያደርጉት የጨለማ ጉዞ ጋር ተያይዞ ሌላ ተደራራቢ ችግር ሊያመጣ ይችላልና በደንቡ መታየት የሚገባ ጉዳይ ነው። እነዚህ አካላት ከሰው ተፈጥሮ ምንም ሰብዓዊነት ሳይሰማቸው ሰው ላይ የሚጭኑት የዋጋ ክምር ግን በእጅጉ የሰውን ሞራል የሚጎዳ ነው።

ይህ በሕጋዊነት ያደራጃቸው አካላት በጫኝና አውራጅ በሚል ወጣቶችን አደራጅተው የሥራ እድል ከመፍጠር በዘለለ ሥራቸውን በምን አግባብ እያከናወኑ እንደሆነ ክትትልና ቁጥጥር እንደማይደረግ አመላካች ነው። የመንግሥት አካላትም የህብረተሱን እሮሮ ሳያውቁት ቀርተው ሳይሆን እየሰሙ እንዳልሰሙ በመምሰል በግዴለሽነት እያለፉት ይመስለኛል።

ትንሽ ቀዳዳን ተጠቅሞ በዚያ ውስጥ በመሹለክ ለማስፋት የሚሞክሩትን አካላት አደብ ማስያዝ በሁለቱም በኩል የሚመለከታቸው አካላት ጉዳዩን በጥሞና ተመልክተው ሊያስተካክሉት በሕግ አግባብ የሚመሩበት ሁኔታ ሊፈጥር የግድ ይላል። በሕጋዊነት ቢደራጁም በምን ሁኔታ መሥራት እንዳለባቸው ግልጽ የሆነ አሰራር ተዘርግቶ ህብረተሰቡም ይህንን የሚያወቅበት ሁኔታ ከተፈጠረ በተበጀው ሕጋዊ መስመር መሠረት ችግሮች ሊፈቱ የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል።

ሕብረተሰቡ በጨለማ አዩኝ አላዩኝ በሚል ፍራቻ የወለደው ድብብቆሽ ወጥቶ በነጻነት መብቱን አክብሮና አስከብሮ የሚሄድበት ሁኔታ ሊኖር ይገባል። ሕብረተሰቡ ደግሞ ዋጋቸው ተመጣጣኝ ከሆነ በሌሊት ጨለማ ከመደነባበር በፀሐይ ብርሃን ወደ ፈለገው ቦታ ለመጓጓዝ ይችላል። ይህ ዛሬ እንደቀላል እያየን የምናልፈው ችግር ነገ መልኩን ቀይሮ ሌላ ትልቅ ችግር ሊፈጥር ይችላልና ባይ ነኝ። የነገ ሰው ይበለን፤፤ ቸር እንሰንብት።

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብሰው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተሳምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታተሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብሰን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፣^እስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍሳችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# የአልጋ ኪራይ-ከኬሻ በጠረባ እስከ G+8

ጽጌረዳ ጫንያለው

« … አረቄ ቤት ቺርስና ዲጄ የለም። 32 እና 34ን አያውቋቸውም? ጉጃም በረንዳን አልፈው፤ በሜይ ዴይ ትምህርት ቤት ገባ ብሎ ያሉት መንደሮች። ወይንም ከአዲስ ከተማ ትምህርት ቤት ጀርባ። 32 ቀበሌና 34 ቀበሌ ይባላሉ። ወዳጄ፤ በዚህ መንደር ያሉት ቤቶች ፍቅረኛሞች ይመስላሉ። እፍግፍግ ብለው፤ ትስርስር ያሉ ፍቅረኛሞች። ፍቅራቸው ግድግዳ እስከ መጋራት የሚዘል የምስኪኖች መኖሪያ። መንደሩን ሾፍ ሲያደርጉ እነዚህ ቤቶች በዓይንዎ መቅረፀ ምስል ላይ እርፍ ይላሉ። ድንገት ሣት ብልዎት ብረት ጊቢ ሊያዩ ይችላሉ። ፐ! የሀብታም ቤት ካሉ ተሳስተዋል። ብረት በሩ ሽፋን ነው። በሩን ተሻግረው ሲገቡ ነፍ ማዘር ቤቶች፣ አረቄ ቤቶች፣ ማደሪያ ቤቶች…ያገኛሉ።

ቤቶቹ በጠቅላላ ማለት ይቻላል G+1 ናቸው። መቼም በእርሶ ቤት G+1 ማለት ቤት በቤት ላይ የተደረበበት ነው። ለመንደሩ ግን ይሄ አይደለም - ሌላ ነው። አራት በአራት የሆነች ጠባብ ቤት በጣውላ ወይም በአጣና ለሁለት ተከፍላ ላይዋ ቆጥ፣ ታቿ ሣሎን ማለት እኮ ነው - G+1። …እያንዳንዱን ሙድ እነሆ:- ድንገት እግር ጥልዎት ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት በኋላ 32 እና 34 ቢመጡ በየሁለት ሜትር ርቀት “አልጋ አለ … አልጋ ትፈልጋለህ … ንፁህ አልጋ … ክፍል ለብቻ…ንፁህ ፍራሽ አለ…ወለል ትፈልጋለህ…” የሚልዎት ልጅ እግር፣ ሴቶችና እናቶች ያጋጥምዎታል።

መሄጃ ከሌለዎትና በኪስዎ ውስጥ ያለው ብር ከተመናመነ አልጋ በአስራ ሁለት ብር፣ ክፍል ለብቻ ብለው ተነጋግረው ወደ መኝታዎ (አልጋዎ) ይሄዳሉ። ልክ ቤቱን ሲያዩ ክው ይላሉ። ጠባብ ቤት፤ 2በ2 ወይም ከሰፋ 3በ2 የሆነ። ቆይ አልጋዎን ላሣይዎት ብላ ያመጣችዎት ልጅ በመሠላል ወደ ቆጥ ወጥታ ክፍል ለብቻው ያለችዎትን ቤት ታስረክብዎታለች። ክፍል ለብቻው ያለችዎ'ኮ ቆጥ ላይ/ምድር (ሣሎን) ውስጥ ስድስት ሰባት አልጋ ተደርድሮ አልጋዎቹ በመጋረጃ ወይም በካርቱን የተከፈሉትን ነው።

ንድድ ይሉና መቼስ ምን ይደረጋል ብለው ብርድ ልብሱን ገልጠው አረፍ እንዳሉ፤ “የእንኳን ደህና መጣህ” አቀባበል የሚያደርጉልዎ የደለቡ ትኋኖች ናቸው። ገና ከማረፍዎ አፍታ እንኳን ሳይቆዩ ውርር ያደርግዎታል። አከክ አከክ ቢያረጉም እነሱ አይቀንሱም። ንድድ ብለው ብርድልብስዎትን ቢገልጡ ሰውነትዎ ሁላ በተባይ ተሞልቷል። ብሽቅ ብለው እዚህ አላድርም፣ የፈለገ ነገር ይምጣ ይሉና ሱሪዎትን ታጥቀው እግርዎትን መሬት ሊያስረግጡ ቢሞክሩ መሬት ይናፍቅዎታል። አልጋ ስሩና ወለሉ በጠቅላላ “በኬሻ በጠረባ” ተከራዮች ተወሯል። (ኬሻ በጠረባ - ወለል ላይ ኬሻ ተነጥፎ እሚተኛበት ነው።) ይቅርታ ጠይቀው… ተለማምጠው …የተረፈረፈውን ሰው እንዳይረግጡ እየተጠነቀቁ ተራምደው እንደምንም ቤቱን ለቀው ላጥ!» ይላል ፒያሳ ሙሀሙድ ጋር ጠብቂኝ የሚለው መጻሐፍ ደራሲ መሃመድ ሰልማን ስለ አልጋ ቤቶቹ ምንነትና ማንነት ሲያስረዳ።

ወደኛ ባለታሪኮች ስንመጣ ደግሞ ይህንኑ የሚደግሙልን በርካቶች ናቸው። በክፉ አጋጣሚ አዲስ አበባን የተቀላቀለው ማስረሻ አያሌው አንዱ ሲሆን፤ የእነዚህ መኝታ ቤቶች ጉዳይ እጅግ ከፈተኑትና የየቀን ሮሮ ከሆኑበት መካከል ነው። ማደሪያ አጥተው ከተቸገሩትና ውሎ አዳራቸውን በኬሻበጠረባ ካደረጉት ሰዎች መካከል ስለሆነም ስለመኝታዎቹ ምንነት ስለ ሰፈሩ ሁኔታ ጥንቅቅ አድርጎ ያውቃል።

ማስረሻ ገና በልጅነቱ በምች ምክንያት የዓይን ብርሃኑን አጥቷል። ይባስ ብሎ በሰሜኑ በነበረው ጦርነት ጦስ ይኖርበት የነበረውን ቀዬና ምኞት ትቶ እንዲወጣ ተገዷል። ኑሮው በሰሜን ወሎ ዞን፣ ዳውንት ወረዳ ነበር። የነገ ተስፋውን ለማለምለም በቤተሰብ እገዛም ሲማር ቆይቷል። አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ ግን ሁሉ ነገር አልጋ



በአልጋ ሊሆንለት አልቻለም። የማያውቀውን አካባቢና ኑሮ በቀላሉ ሊለምደው አልቻለም። ምክንያቱም ዛሬም አካል ጉዳቱ ከ ኑሮ ደረጃው ጋር ተዳምሮ ከጦርነት ያልተናነሰ ህይወት እንዲገፋ አድርጎታል።

አዲስ አበባ ሲመጣ የሚያርፍበትም ሆነ የሚጠጋበት ዘመድ የለውም። የአይነስውራን ማህበር ድጎማ ቢያደርግለትም ለቀን ቤት ኪራዩ እንኳን አይበቃውም። ስለዚህ ምርጫው አንድና አንድ ብቻ ነው። የእናት ቤት (ኬሻ በጠረባ) የሚባሉትን ማደርያዎች ተከራይቶ ቀን እስኪያልፍ ህይወትን መግፋትና የጀመረውን ትምህርት ማጠናቀቅ ዋነኛው ህልሙ ነው።

የኬሻ በጠረባ ቤቶች ለማስረሻ ቤቶቹ ተስፋ ሰጪዎች ቢሆኑም ስቃዩም ናቸው። ኬሻ በጠረባ የሚባሉት ማደርያዎች በቱሃን፤ በቁንጫ፤ ቅማልና ሌሎች ተባዮች የተሞሉ ከመሆናቸውም በላይ እነርሱን ተቋቋምኩ ሲል ሌላ ፈተና ያመጡበታል። ይህም የተከራዩዎች እንቅስቃሴና ማንኮራፋት እረፍት ይነሳዋል። አናት የሚበጠብጥ የጫማና የላብ መጥፎ ጠረንም የነዚህ ቤቶች ዋነኛ መለያዎች ናቸው። በዚያ ላይ ደግሞ ለማደር የሚገቡት ሰዎች ባህሪ የተለያየ በመሆኑ ጨኸቱ እንደአይነስውርነቱ እንኳን በመቅረጸ ድምጹ የቀዳውን ትምህርት ለማዳመጥ አያስችለውም። የቤት ሥራም እንዲሁ እንዲሰራ እድሉ የለውም። ምክንያቱም እያነበበለት የሚያሰራው ሰው አያገኝም። ይህ አልተሳካም ብሎ እንኳን እንቅልፍ ልተኛ ቢል አይችልም።

ቤቱ ሰካራም አለያም ወንበዴን መርጦ የሚያሳድር ባለመሆኑ የተነሳም ሁልጊዜ ንብረቱን በእጁ አቅፎ እንዲተኛ ያስገድደዋል። አስቀምጦ የሚሄድበትም ቤት ስላልሆነ ንብረቱን በሻንጣው ተሸክሞ ትምህርት ቤት እንዲመላለስ ያደርገዋል። ይህም ሆኖ ግን ንብረቱን ማትረፍ አልቻለም። በተደጋጋሚ ትራንስፖርት ላይ ተወስዶበታል። ዩኒፎርሙ ሳይቀር ተዘርፏል። ትምህርት ቤቱ መልካም ፈቃዱን ባይቸረው ኖሮ ዛሬ ትምህርቱን አቋርጦ ነበር። የ12ኛ ክፍል ተማሪም ለመሆን አይበቃም ነበር።

የኬሻ በጠረባ ኪራይ ጉዳይ ይህ ብቻ አይደለም። ኬሻ በጠረባ ተከራይቶ እንደልብ መገላበጥ ማርና ወተት እንደመጠጣት የሚናፈቅ ነው። ኬሻ በጠረባዎች በሰው ስለሚሞሉ ወለሉ ሁሉ መኝታ ይሆናል። ስለዚህም በአንድ ጎን ከተኙ ሳይገላበጡ ማንጋት ግድ ነው። ለሌላኛው መገላበጫ ቦታ የለም። አንዱን ከነኩ ድብድብ መግጠምዎ አይቀርም። ስለዚህም ምርጫዎ የሚሆነው እግሮት እንደታጠፈ አለያም እንደተዘረጋ ማንጋት ብቻ ነው። በዚህም አይነስውሩ ማስረሻም ምንም እንኳን ባያያቸውም እረግጣቸዋለሁ በሚል ስጋት ከተቀመጠበት ሳይንቀሳቀስ ነው ቀናትን፣ ወራትን አሳልፏል። አሁንም በዚህ ሁኔታ እያደረ ነው የ12ኛ ክፍል ትምህርቱን እየተማረ ያለው።

እነርሱ ግን እንደፈለጋቸው ይረጋግጡታል። በተለይ አልፈውት አልጋ የተከራዩት ሲመጡ አንድም ቀን ሳይረግጡትና ሳይጨፈልቁት አይሻገሩም። በዚያ ላይ ደግሞ አንዳንድ ቤቶች መብራት የላቸውምና ስቃዩ ይበረታበታል። መብራቱ ለእርሱ ሳይሆን ወደ ቆጡ አለያም ወደ ኬሻ በጠረባው ላይ የሚያርፉትን እንዲተያዩ ያግዛልና ቢያንስ መረገጡን ይቀንስለታል። እናም ዛሬ የመረጠው ደህና ቢሆን ነገ ደግሞ አዳሩ ሰቆቃ የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው።

የኬሻ በጠረባ ነገር ሲነሳ በጣም የሚገርመው በሰፈሩ ያሉት ልጆች ጉዳይ ነው። ቀን ከትምህርት መልስ ይተኛሉ። ሌት አልጋቸው ስለሚከራይባቸው ሰፈሩን በጨዋታ ሲያቀልጡት ያድራሉ። ከዚያም አልፈው ቤታቸው እንዲከራይላቸው “አልጋ አለ…ክፍል ለብቻ አልጋ አለ…ወንድም አልጋ ትፈልጋለህ…”» እያሉ ሲጮሁ ያነጋሉ። ቀን ቀን ትምህርት ቤት እየተማሩ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ የሚወስዳቸው በርካቶች ናቸው።

ወደ ሌላኛዋ ባለታሪካችን ስንገባ ደግሞ ከማስረሻ የተለየ ነገር ያላቸው ናቸው። እንደእርሱ ተከራይ አይደሉም። አከራይ እንጂ። ስለዚህም ይህ ሥራ ለእርሳቸው ልዩ ትርጉም ያለው ነው። የኑሯቸው ምሶሶና የችግራቸው መውጫ ነው። እናም በልዩ ፍቅር ነው የሚሰሩት። ስራው ግን አድካሚና ከብዙዎች ጋርም ለጭቅጭቅና ለዱላ የሚዳርግ ነው። በእርግጥ ሥራውን የገቡበት በአጋጣሚ ነው። ባለቤታቸው ሲሞት፣ ከቋሚ ሥራቸው ሲቀነሱና ልጆቻቸው ታመው ማሳከሚያ ሲያጡ ዘው ብለው አልጋ ማከራየት ውስጥ ገቡ።

የቤት ኪራዩ ልክ እንደአውቶቢስ ተራ ኬሻ በጠረባ የሚባል ነገር የለበትም። ቦታው በተለምዶ ሀዲድ እየተባለ የሚጠራው አካባቢ ላይ ያለ ሲሆን፤ የአልጋ ኪራይ ብቻ ነው ያለው። ስለዚህም በዝቅተኛ ዋጋ ማለትም በ30 ብር አንድ ሰው አንድ አልጋ ይዞ ማደር ይችላል። ተደራራቢ ቆጡ በG+8 ድረስ ያለ ሲሆን፤ ክፍያው እንደ ከፍታው ይለያያል። እንደኮንደሚኒየሙ አይነት ግን እዳይመስላችሁ። ምክንያቱም ኮንደሚኒየም ውሃ ከፍ ያለ ቦታ ላይ መውጣት ስለማይችልና ሰዎችም በከፍታው ምክንያት ስለሚሰቃዩ ላይኛው ላይ ያለው ተከራይ ዋጋ ይቀነስለታል። በእነዚህ ቤቶች ግን ከፍ ካለው ቆጥ ላይ የሚተኛ ሰው ከፍ ያለ ዋጋ መክፈል ይጠበቅበታል። ምክንያቱም ለመሰረቅ፣ አደጋ ውስጥ ለመግባት ቶሎ አይጋለጥም። ሁሉ ነገሩ ሴፍ ነው።

ወይዘሮ ገበያነሽ አልጋ ሲያከራዩ መራጭ ናቸው። ልክ በትላልቅ ሆቴሎች እንደሚደረገው ዕቃዬ ይሰረቃል የሚል ስጋት ያለው ሰው ንብረቱን ለሪስፕሽን እንደሚያስረክበው በሃዲድ መንደርም ስጋት የገባው ሰው ንብረቱን ለወ/ሮ ገበያነሽ አስረክቦ ያለስጋት እንቅልፉን መለጠጥ ይችላል። ከዚያ ባሻገር የእነ ወይዘሮ ገበያነሽ ቤት ተከራይ ሌሎች መልካም እድሎችም አሉት። ለምሳሌ በዓል ሲሆን አብሮ ማሳለፍና ያለውን አብሮ መቋደስ ይፈቀድለታል። በሃዲድ መንደር አልጋ ተከራይ ማለት ቤተሰብ ነው።

‹‹እነዚህ ቤቶች የአከራዮች የእለት ጉርስ የተከራዮቻቸው ደግሞ የደከመ ጎን ማሳረፊያ ናቸው። መውደቂያ ላጡ ምስኪኖች ደግሞ መደጋገፊያ ይሆናሉ። ምክንያቱም ለድሆች የቀን እፎይታቸው የሌሊት ረፍታቸው ናቸው። በድካም የዛለ ሰውነታቸውን ያሳርፉባቸዋል።›› የሚሉት ወይዘሮዋ፤ ይህን ሥራ ልክ እንደልጃቸው ያዩታል። ምክንያቱም የሞቱባቸው ልጆቻቸውን ባይድኑም አሳክመውበታል። በዚያ ላይ የልጃቸው ማስታወሻ ነው። እርሷ በሕይወት በነበረችበት ወቅት ልጆቿን ተንከባክባበታለች። ዛሬም ቢሆን ለልጅልጆቻቸው ሕይወት መቀጠል ጭምር ዋነኛው ምሰሶ የዚህ ሥራ ገቢ ነው። እናም ደንበኞች ክቡር ናቸውና መደረግ ያለበት ሁሉ መደረግ ይኖርበታል ብለው ያምናሉ፤ ያደርጉታልም።

አሁን ላይ በላይ ክፍል ሰርተው የሚያከራዩት ቤት በለስ ቀንቷቸው በደርግ ጊዜ ቀበሌ የሰጣቸው ቤት ነው። እናም አነስተኛ ክፍያ ለመንግሰት እየከፈሉ መኝታ ክፍል ሳያምራቸው ሳሎናቸውን መኝታ አድርገው የገቢ ምንጭ የሚሆናቸውን ተደራራቢ አልጋ በአንዱ ክፍል ውስጥ በማስቀመጥ የገቢ ምንጫቸውን ፈጥረዋል። ቤቱ ለደህንነታቸው ሲባል በግርግዳ የተለየ ሲሆን፤ የራሱ የሆነ በር አለው። ክፍሉ ግን እጅግ ጠባብ ነው። በአንዱ ክፍል የሚሰራው በሌላው ክፍል በቀላሉ ይሰማልና እንቅልፍ ይናፍቃል። ከዚያም ከፍ ሲል አዳሪዎቹ የተለያዩ ሰዎች በመሆናቸው መጥፎ ጠረኖች አይጠፉም። ሆኖም እርሳቸው ይህ እንዳይከሰት የቻሉትን ያህል ያደርጋሉ። ለአብነት ውሃ በገፍ ያቀርባሉ፤ ካልሲያቸውን የሚያጥቡበት፤ እግራቸውን የሚታጠቡበት ሳሙናም እንዲሁ ይሰጧቸዋል።

አልጋ ተከራዮቹ የሚመጡበት ሰዓት የተወሰነ ሲሆን፤ ወደ አልጋ የመግቢያ ሰዓት እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ የሚመጣ ሰው ቦታ የለውም። በዚህም መጀመሪያ የተከራዮቹን ከዚያም የራሳቸውን በር ዘግተው ይተኛሉ። ጠዋት 12 ሰዓት በር ይከፍታሉ። ከዚያም ቀደም ብሎ መውጣት የሚፈልግ ካለ አይከለክሉትም። ላርፍድ ያለ ሰውም እንዲሁ እስከ ሁለት ሰዓት እንዲተኛ ይፈቀድለታል። ለሁሉም ወጪዎች ቀድመው በመነሳት እንደተለመደው ውሃና ሳሙና በር ላይ ያስቀምጣሉ። ይህንን በማድረጋቸው ቋሚ አዳሪዎችን ጭምር የፈጠሩበት እድል መኖሩን ያነሳሉ።

‹‹መልካምነት ይከፍላል፤ ከገንዘብ በላይ ቤተሰባዊነት ይበልጣል። ኑሮን ጎዶሎን ለመሙላት ሲባል እንጂ ሰውን ሁሉ በነጻ ማሳደር ይቻል ነበር። ምክንያቱም ቤት የእግዚአብሔር ነው። ግን ወቅቱ ይህንን አይፈቅድም። አሁን ባለው ሁኔታ ሰዎችን አምኖ በራሱ ማሳደር ትልቅ መልካምነት ነው።›› ይላሉ ያለውን የሥራ ሁኔታ ሲያስረዱ። ምክንያቱም እርሳቸውን ባይገጥማቸውም በዚህ ስራ የሚተዳደሩ ሰዎች በመጥፎ ሰዎች ድርጊት ቤተሰባቸው፤ ኑሯቸውና ማንነታቸው ተነጥቀዋል። እናም ሥራው መልካምም መጥፎም ስጦታ አለው ይላሉ።

# ስፖርት




# አትሌት ሰንበሬ ተፈሪ ዕውቅና ተሰጣት

**አስማየሁ ግዛው**

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ለመካከለኛና ረጅም ርቀት ጀግናዋ አትሌት ሰንበሬ ተፈሪ በመድረኩ ላስመዘገበቻቸው አንጸባራቂ ድሎቿና አርያነቷ ዕውቅና አበርክቶላታል። አትሌቷ ዕውቅናው የተሰጣት ከትላንት በስትያ በአያት ሬጀንሲ የ2015 ዓ.ም ሳፋሪኮም ቅድሚያ ለሴቶች የ5 ኪሎ ሜትር ውድድር ምዝገባ ማስጀመሪያ ስነስርዓት ላይ ነው።

በአፍሪካ ቀዳሚ የሆነው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በርካታ አትሌቶችን ለዓለም አቀፍ ዕውቅና በማብቃት ይታወቃል፡፡ በመድረኩ የተሻለ ተሳትፎና ውጤት ያላቸውንም የሚያበረታታ ሲሆን፤ አትሌት ሰንበሬ ተፈሪ ከእነዚህ መካከል አንዷ ሆናለች፡፡ አትሌቷ በሶስት ተከታታይ የቅድሚያ ለሴቶች 5 ኪሎ ሜትር ውድድሮች ያለ ጣልቃ ገብነት ክብረወሰኖችን መሰባበሯ ለዕውቅና አብቅቷታል። ቅድሚያ ለሴቶች የ5 ኪሎ ሜትር ውድድር እአአ ከ2004 ከተጀመረ አንስቶ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ከሰንበሬ ተፈሪ ውጪ ያሸነፈ አትሌት እንደሌለም በመድረኩ ተገልጿል። ይህም አትሌቷ ለሴቶች የመቻል ምልክት ሆና ላበረከተችው ትልቅ አስተዋጽኦ በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የዕውቅና ሽልማት እንዲበረከትላት አስችሏል፡፡

ሽልማቱ የተሰጣት ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በየዓመቱ በሚያዘጋጀው የቅድሚያ ለሴቶች ሩጫ የ2015 ዓ.ም ምዝገባ ማስጀመሪያና 20ኛ ዓመት ክበረ በዓልን ምክንያት በማድረግ መሆኑም ተጠቁሟል። ለአትሌቷ ዕውቅናውን ያበረከቱትም በክብር እንግድነት የተገኙትና በዚህ መድረክ ድልን መቀዳጀት የቻሉት አትሌት ብርሃኔ አደሬ እና አትሌት አሰለፈች መርጊያ ናቸው፡፡




**ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ለአትሌት ሰንበሬ ተፈሪ በመድረኩ ላስመዘገበችው ድልና ለአርያነቷ ዕውቅና ሰጥቷታል፣**

በመድረኩ እውቅና ከመስጠትም ባሻገር የ2015 ዓ.ም የሳፋሪኮም ቅድሚያ ለሴቶች 5ኪ.ሜ የጎዳና ላይ ሩጫ የምዝገባ ቀንና ቦታም ይፋ ተደርጓል። ተሳታፊዎች ምዝገባውን ከመጪው ሰኞ የካቲት 20/2015 ዓ.ም ጀምሮ በዳሸን ባንክ እንዲሁም በአሞሌ ሞባይል መተግበርያ አማካኝነት 450 ብር በመክፈል መመዝገብ እንደሚችሉ ተጠቁሟል። ውድድሩ መጋቢት 17/2015 ዓ.ም የሚካሄድ ሲሆን፤ 15ሺ ተሳታፊዎች እንደሚካፈሉበትም ተጠቁሟል። ውድድሩ እንደተለመደው መነሻና መድረሻውን ቦሌ አትላስ አድርጎ እንደሚካሄድ ተገልጿል።

የምዝገባውን መጀመርም የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ስራ አስኪያጅ ወይዘሮ ዳግማዊት አማረ በይፋ አብስረዋል። ‹‹ሳፋሪኮም ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ወዲህ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ጠንክሮ እየሰራ ይገኛል፤ ለዚህም ከነሱ ጋር አብረን በአጋርነት መስራት ጥሩ አጋጣሚ ነው። እንደዚህ ያለ የስያሜ አጋር በማግኘታችንም ደስተኞች ነን›› ሲሉም ወይዘሮ ዳግማዊት ሃሳባቸውን አጋርተዋል።

የሩጫው መልዕክት ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጋር በመተባበር ‹‹ቦታዬ፣ መብቴ፣ ድምጿ›› የሚል እንደሚሆንም ተገልጿል። የ20ኛ ዓመት ቅድሚያ ለሴቶች ክብረ በዓልና የ2015 ዓ.ም መክፈቻ ዝግጅት ላይም በክብር እንግድነት ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴን ጨምሮ የውድድሩ አምባሳደር አትሌት መሰረት ደፋርና የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ህጻናት ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሃና የሺንጉስ መታደም ችለዋል።

የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ መስራች ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ በውድድሩ ትልቅ የሆነ ለውጥ መምጣቱን ገልጾ፤ ‹‹ለሴቶች የምንሰጠው ክብር ለቤተሰባችን የምንሰጠው ክብር ነው›› በማለት ተናግሯል። አክሎም ‹‹ለሴቶች ሩጫ ማወዳደር ብቻ ሳይሆን ቀጥሬ በማሰራው መስሪያ ቤት ውስጥም 60 በመቶ ሰራተኞች ሴቶች በመሆናቸው ለሴቶች በሚሰጠው ልዩ ትኩረት ለሌሎች እንደተሞክሮ ሊወሰዱ ይገባልም›› በማለት አሳስቧል። አትሌት መሰረት ደፋር በበኩሏ ሴት ሆኖ አትሌት መሆን ልምምድ ስለሚያስፈልግ እነዚህን ነገሮች በማድረግ ውጤታማ ስለሆንኩ ኩራት ይሰማኛል በማለት ስሜቷን ገልጻለች። በቀጣይም ውድድሩን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ድርሻዋን እንደምትወጣ ቃል ገብታለች።

የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ራዕይ የሆነውን ‹‹ሩጫን የአኗኗር ዘይቤያችን እናድርግ›› ለማጉላት ከውድድሩ በፊት ለ4 ሳምንት የሚቆይ የአካል ብቃት ልምምድ በተለይም በሩጫው ለመሳተፍ ለተዘጋጁ እና የታላቁ ሩጫ አባላት ለሆኑ የስልጠና መርሃ ግብር መዘጋጀቱም ተጠቅሷል። ይህም በነገው ዕለት የካቲት 19/2015 ዓ.ም እንደሚጀመርም ተነግሯል።

የታላቁ ሩጫ የሴቶች ውድድር እአአ በ2004 መካሄድ የጀመረ ሲሆን፤ በ4ሺ500 ሴት ተሳታፊ አትሌቶች ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ቁጥሩ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሮ በዘንድሮው ውድድር 15ሺ ሴቶች እንደሚሳተፉም ይጠበቃል።


## የጨረታ ማስታወቂያ
## የግዥ መለያ ቁጥር 003/2015

የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ስራ አስኪያጅ ፑል የአስተዳደርና ፋይናንስ ጽ/ቤት በ2015 የበጀት ዓመት ለመሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት ላተራል ፋይል ካቢኔት ህጋዊ ተጫራቾችን አወዳድሮ ግዥ መፈጸም ይፈልጋል፡፡

**በዚህም መሰረት፤**

*** ሎት 1 ላተራል ፋይል ካቢኔት ባለሃዲድ**

በጨረታ መሳተፍ የሚፈልጉ ማንኛውም ህጋዊ ተጫራቾች የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልተው በጨረታው መወዳደር ይችላሉ።

1. የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ።
2. የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፊኬት እና ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ።
3. ከወጣው ጨረታ ውስጥ ብር 100,000.00 / አንድ መቶ ሺህ ብር/ በላይ ዋጋ በማቅረብ በጨረታው የሚሳተፍ ማንኛውም የአገር ውስጥ ተጫራች የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ወረቀት ኮፒ ማያያዝ ይኖርበታል።
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በስራ ሰዓት ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ በስራ አስኪያጅ ፑል የአስተዳደርና ፋይናንስ ጽ/ቤት የመንግስት ግዥ አስተዳደር ቡድን 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 504 የጨረታ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 10 የስራ ቀናት ውስጥ ለእያንዳንዱ ሎት የማይመለስ ብር 200.00/ ሁለት መቶ / በመክፈል መውሰድ ይችላሉ።
5. የጨረታ ሰነዱ በሁለት ኤንቨሎፕ የሚቀርብ ሆኖ የቴክኒክ ዶክመንትና የፋይናንሻል ዶክመንት በታሸገ ኤንቨሎፕ ለየብቻ ሆኖ በአንድ ፖስታ በማጠቃለል እንዲሁም የቴክኒክና የፋይናንሻል ዶክመንት ዋናውና ቅጅው ከአንድ አንድ ኮፒ ጋር ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል ::
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ ) በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ (CPO) ብቻ **ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት** በሚል በማዘጋጀት ማስያዝ ይኖርባቸዋል ::
7. ተጫራቾች በስራ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት የተደራጁ ከሆነ ከተደራጁበት ተቋም የዋስትና ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው::
8. ተጫራቾች ላተራል ባለሀዲድ ባለ 3 ሃዲድ ናሙናውን ከመሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት የማህደር ክፍል ድረስ በመምጣት ማየትና ጨረታውን ካሸነፉ በኋላ ድርጅቱ በሚያሳየው ቦታ በማድረስና በመግጠም ለስራ ምቹ አድርገው ማስረከብ አለባቸው::
9. ጨረታው በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በዚያው ቀን ጠዋት 3:30 የሚከፈት ሲሆን ነገር ግን 11ኛው ቀን የስራ ቀን ካልሆነ ጨረታው በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት የሚከፈት ይሆናል፡፡
10. መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ::
11. ማንኛውም ተጫራች የሚያቀርበው ጨረታ ሰነድ ስርዝ ድልዝ ኖሮት ካልተፈረመ ወይም ፍሉድ ተጠቅሞ በጉልህ የማይነበብ ከሆነ ከውድድር ወጪ ይሆናል::
12. ተጫራቾች ሙሉ specification ከጨረታው ሰነድ ጋር ሞልተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
13. የጨረታውን አካሄድ ለማዛባት የሚሞክሩ ተጫራቾች ከጨረታው ውጪ እንደሚሆኑ፤ ለወደፊትም በመንግስት ግዥ እንዳይሳተፉ እና ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደሚወረስ ማወቅ አለባቸው::

**አድራሻችን:- ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢ/ቁ 504**

**በስራ አስኪያጅ ፑል የአስተዳደርና ፋይናንስ ጽ/ቤት**

**የበለጠ መረጃ - 011-835 -88 - 99 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል።**

## የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማት ማኔጅመንት ፑል
## አስተዳደርና ፋይናንስ ጽ/ቤት